ኢ'ተ:ነል -ቅ- ዘለዓለማዊ ፣ መጨ'ረሻ የሌ'ለው

ethical
'ኤፒክል -ቅ- ግብረ ገ'ባዊ (ለጠባይ) ፣ ከግብረ ገ'ብ'ነት ጋር ግን'ኙ'ነት ያ'ለው

ethics
ኤ፬ክስ -ስ- የግብረ ገ'ብ'ነት ጥናት

Ethiopia
ኢ፬'ዮውፒያ -ስ- ኢትዮ'ጵያ

Ethiopian
ኢ፬'የውፒየን -ቅ- ኢትዮ'ጵያዊ

eucalyptus
ዩከ'ሊፕተስ -ስ- ባሕር ዛፍ

Eucharist
'ዩ:ከሪስት -ስ- ሥጋ ወደሙ ፣ ቁርባን

eunuch
'ዩነክ -ስ- ጃንደረባ ፣ ስልቀ

European
ዩሪ'ፒየን -ቅ- አውሮ'ጳዊ

evade
ኢ'ቬይድ -ግ- ማምለጥ [አመ'ለጠ] ፣ ገለል ማለት [አለ] ፣ መልስ ለመስጠት አለመፈ'ለግ [-ፈለ'ገ]

evacuate
ኢ'ቫክዩዌይት -ግ- ማስለ'ቀቅ [አስለ'ቀቀ] (ሕዝብ ከሀገር)

evaluate
ኢ'ቫልዩዌይት -ግ- መገ'መት [ገ'መተ]

evaporate
ኢ'ቫፖሬይት -ግ- መትነን [ተ'ነነ]

evasive
ኢ'ቬይዚቭ -ቅ- ማምለጫ ፡ ካንድ ውናቴ መራቅያ (መልስ ወዘተ)

eve
'ኢይቭ -ስ- ዋዜማ

even
'ኢይቨን -ተግ- እንኳን ፣ ፀ . . . ም -ቅ- ለ'ጥ ያለ ፣ የተቡ'ክለ ፣ የተመ ዛ'ዘነ ፣ ለውለ'ት በትክ'ክል ሊ'ከ'ፈል የ'ሚ'ቻል

evening
'ኢይቭኒንግ -ስ- ም'ሽት

event
ኢ'ቬንት -ስ- ድር'ጊት ፣ ሁናቴ

eventful
ኢ'ቬንትፉል -ቅ- አዳ'ዲስ ነገር ያ'ስ'በት ፣ አስደ'ሳች

ever
'ኤቭ -ተግ- መ'ቸም ፣ ምንጊዜም ፣ ሁል ጊዜ

everlasting
ኤቭ'ላ:ስቲንግ -ቅ- መ'ጨ'ረሻ የሌ'ለው ፣ ዘለዓለማዊ

every
'ኤቭሪ -ቅ- እ'ያንዳንዱ

everybody
'ኤቭሪባዲ -ስ- እ'ያንዳንዱ ሰው

everyday
ኤቭሪ'ዴይ -ቅ- በ'የቀኑ ፡ የ'የቀኑ

everyone
'ኤቭሪወን -ስ- እ'ያንዳንዱ ሰው

everything
'ኤቭሪሲንግ -ስ- ማ'ን'ኛው'ም ነገር ፣ ሁ'ሉ'ም ነገር

everywhere
'ኤቭሪዌየ -ተግ- የት'ም

evict
ኢ'ቪክት -ግ- ማስወ'ገድ [አስወ'ገደ] (በሕ'ግ) ፣ መንቀል [ን'ቀለ] (ሰውን ከርስት)

evidence
'ኤቭደንስ -ስ- ማስረ'ጃ

evil
'ኢይቭል -ስ- ክፋት

ewe
'ዮው -ስ- ሴት በግ

exact
ኤግ'ዛክት -ቅ- በትክ'ክል ፣ ል'ክ

exactly
ኤግ'ዛክትሊ -ተግ- በትክ'ክል -ቃኤ- ል'ክ እንደ'ዚህ

exaggerate
ኤግ'ዛጀሬይት -ግ- ማ'ጋነን [አ'ጋ'ነነ] ፣ ከ'ሚ'ገ'ባ በላይ ስለእንድ ነገር መ'ናገር [ተና'ገረ]

examination
ኤግዛመ'ኔይሽን -ስ- ፈተና

examine
ኤግዛመን -ኅ- መፈ'ተን [ፈ'ተነ] ፣ መመር መር [መረ'መረ]
example
ኤግዛ'ምፐል -ስ- ም'ሳሌ ፣ ማስረ'ጃ
excavate
'ኤክስከቬይት -ኅ- መቆ'ፈር [ቆ'ፈረ] (የተደ'በቀ ነገር ለማግኘት)
exceed
ኤክ'ሲይድ -ኅ- መብለጥ [በ'ለጠ] ፣ መላቅ [ላቀ]
excellent
'ኤክለለንት -ቅ- በጣም ጥ'ሩ ፣ እ'ጅግ የላቀ
except
ኤክ'ሴፕት -ተኅ- ከ . . . በስተቀር
exception
ኤክ'ሴፕሽን -ስ- ያልተለ'መደ ነገር ፣ ሁናቴ ፣ እ'ጠቃላይ ሕ'ግን የማይ'ከ'ተል ነገር ፣ ሁናቴ
exceptional
ኤክ'ሴፕሽነል -ቅ- ያልተለ'መደ ፣ በጣም ጥሩ
excerpt
'ኤክሰ:ፕት -ስ- አስተዋፅኦ ፣ አ'ጭር ምን ባብ (የመጽሐፍ ፣ የፊልም ፣ የቴያትር ወዘተ)
excess
ኤክ'ሴስ -ስ- ከል'ክ ማ'ለፍ ፣ ማትረፍ ፣ ማትረፍረፍ
excessive
ኤክ'ሴሲቭ -ቅ- ከል'ክ ያ'ለፈ ፣ የተትረፈ'ረፈ
exchange
ኤክስ'ቼይንጅ -ኅ- መ'ለዋወጥ [ተለዋ'ወጠ]
excise
'ኤክሳይዝ -ኅ- መቅረጥ [ቆ'ረጠ] (በአገር ውስጥ የ'ሚ'ሸጡ ዕቃዎች'ችን)
tax
-ስ- ቀረጥ (በአገር ውስጥ በ'ሚ'ሸጡ ዕቃዎች ላይ የ'ሚ'ጣል)
take out
-ኅ- መቁረጥ [ቆ'ረጠ] (ከመጽሐፍ አን ዱን ክፍል)
excite
ኤክ'ሳይት -ኅ- ማስደ'ሰት [አስደ'ሰተ] ፣ ስ'ሜ ትን መቀስቀስ [ቀስ'ቀሰ]
excitement
ኤክ'ሳይትመንት -ስ- ደ'ስታ ፣ የስ'ሜት ፣ መ'ቀስቀስ

exclaim
ኤክስክ'ሌይም -ኅ- በድንገት መ'ጮኽ [ጮኸ] (ከ'ሥቃይ ፣ ከ'ቁጣ ፣ ከድን'ጋጤ ወዘተ የተ ነ'ሣ)
exclamation
ኤክስክለ'ሜይሽን -ስ- የሣ'ንጎን ጩኸት ፣ የአንክሮ ድምፅ
exclude
ኤክስክ'ሉ:ድ -ኅ- ለ'ይቶ ማስቀ'ረት [አስቀ'ረ]
exclusive
ኤክስክ'ሉ:ሲቭ -ቅ- የተለ'የ ፣ ል'ዩ
excrement
'ኤክስክረመንት -ስ- ዓይነ ምድር ፣ ኩስ
excretion
ኤክስክ'ሪይሽን -ስ- የወ'ጣ ነገር (ከሰው'ነት ፣ አሰር ፣ አር ፣ ላቦት ወዘተ)
excruciating
ኤክስክ'ሩ:ሺዬይቲንግ -ቅ- በጣም የ'ሚያ'ም ፣ የ'ሚያ'ሠቃ'ይ
excursion
ኤክስ'ክ:ሽን -ስ- አ'ጭር የሽ'ርሽ'ር ጉዞ
excuse
ኤክስክ'ዩ:ዝ -ኅ- ይቅር ማለት [አለ] ፣ ስኅተ ትን ች'ል ማለት [አለ]
excuse
ኤክስክ'ዩ:ስ -ስ- ይቅርታ ፣ ምክንያት (የሠ'ሩት ሥራ ል ክ መሆኑን ለማስረ'ዳት)
execute
'ኤክሲክዩ:ት -ኅ- መፈ'ጸም [ፈ'ጸመ] (የተጠ 'የቁትን ፣ የታ'ዘዙትን ነገር)
execution
ኤክሲክ'ዩ:ሽን -ስ- መፈ'ጸም (አንድ ጉ'ዳይ) ፣ መግደል (ሞት የተ'ፈ'ረደ'በትን)
executive
ኤክ'ዜክዩቲቭ -ስ- ባለሥልጣን
exempt
ኤክ'ዜምፕት -ኅ- ከግ'ዴታ ነጻ መሆን [ሆነ] -ቅ- ሕ'ግ የማያስገ'ድደው
exercise
'ኤክሰሳይዝ -ስ- መልመጃ ፣ መ'ለማመጃ -ኅ- መሥራት [ሠ'ራ] ፣ ማድረግ [አደ 'ረገ]
exert
ኤክ'ዝ:ት -ኅ- በጣም መሥራት [ሠ'ራ] ፣ እሥራ ማዋል [አዋለ]

exhale
ኤክስ'ሄይል -ኅ- መተንፈስ [ተነ'ፈሰ] (ወደ ው'ጭ)
exhaust
ኤግ'ዞ:ስት -ኅ- ማድከም [አደ'ከመ] -ስ- የመኪና ጢስ መውጫ ቧም'ቧ
exhibit
ኤግ'ዚቢት -ኅ- ማሳ'የት [አሳ'የ]
exhibition
ኤክሲ'ቢሽን -ስ- ኤክዚቢሽን ፣ ለመ'ታየት የቀ'ረቡ ዕቃዎ'ች ፣ ትርኢት (የዕቃዎ'ች)
exile
'ኤክሳይል -ኅ- ማ'ገዝ [አ'ገዘ] (ለቅጣት) -ስ- ግዞ'ኛ ፣ የግዞት ቦታ
exist
'ኤግ'ዚስት -ኅ- መኖር [ኖረ]
existence
ኤግ'ዚስተንስ -ስ- መኖር ፣ ህ'ላዌ
exit
ኤግዚት -ስ- መውጫ በ'ር
expand
ኤክስ'ፓንድ -ኅ- መ'ለጠጥ [ተለ'ጠጠ] ፣ መ 'ሳብ [ተሳበ]
expect
ኤክስ'ፔክት -ኅ- መ'ጠባበቅ [ተጠባ'በቀ] (አ ንድ ሁናቴ ፣ ነገር ወዘተ እን'ደ'ሚሆን)
expectant
ኤክስ'ፔክተንት -ቅ- በጉ'ጉት በተሰፋ የ'ሚ ጠ'ብቅ
expedition
ኤክስፒ'ዲሽን -ስ- የተናት ፣ የምርመራ ጉዞ ፣ አንድ ዓላማ ያ'ለው ጉዞ
expel
ኤክስ'ፔል -ኅ- ማስወ'ጣት [አስወ'ጣ] ፣ ማስ ወ'ገድ [አስወ'ገደ]
expend
ኤክስ'ፔንድ -ኅ- ገንዘብ ፣ ጊዜ ፣ ጉልበት ወዘተ ላገድ ተግባር ማዋል [አዋለ]
expenditure
ኤክስ'ፔንዲቾ -ስ- ወጭ (የገንዘብ)
expense
ኤክስ'ፔንስ -ስ- ወጭ (የገንዘብ)
expensive
ኤክስ'ፔንሲቭ -ቅ- ው'ድ (ለዋጋ)

experience
ኤክስ'ፒሪየንስ -ስ- የሥራ ልም'ምድ (በማ የት'ና ፣ በመሥራት የተገ'ኘ)
experiment
ኤክስ'ፔሪመንት -ኅ- መፈ'ተን [ፈ'ተነ] (ያን ድ ነገር ሁናቴ ለማጥናት) -ስ- መ'ክሪ (የጥናት)
expert
'ኤክስፐ:ት -ቅ- ዐዋቂ ፣ ባለሙያ
expire
ኤክስ'ፓየ -ኅ- ማለቅ [አ'ለቀ] (ለጊዜ)
explain
ኤክስፕ'ላይን -ኅ- መግለጽ [ገ'ለጸ] ፣ ማስረ 'ዳት [አስረ'ዳ]
explanation
ኤክስፕለ'ይሽን -ስ- አ'ገላለጽ
explode
ኤክስፕ'ሎውድ -ኅ- መፈንዳት [ፈነ'ዳ] ፣ ማፈ ንዳት [አፈነ'ዳ]
exploit
ኤክስፕ'ሎይት -ኅ- ያገር ሀብት እሥራ ላይ ማዋል [አዋለ] ፣ ያለ አግባብ የሰው ጉልበት መብዛት [በ'ላ]
exploit
'ኤክስፕሎይት -ስ- የጉብዝ'ና ሥራ ፣ ተግባር (በጦር'ነት ወዘተ)
explore
ኤክስፐ'ሎ: -ኅ- መርምሮ ማግኘት [አገ'ኘ]
explosion
ኤክስፕ'ሎውዠን -ስ- መፈንዳት
export
'ኤክስፖ:ት -ኅ- የንግድ ዕቃ ወደው'ጭ አገር መላክ [ላከ]
exposed
ኤክስ'ፖውዝድ -ቅ- ግልጽ የሆነ ፣ ያልተሰ 'ወረ
exposure
ኤክስ'ፖውዠር -ስ- ተገልጦ መ'ታየት
expound
ኤክስ'ፓውንድ -ኅ- ማስረ'ዳት [አስረ'ዳ]
express
ኤክስፕ'ሬስ -ኅ- በድር'ጊት በቃላት ፣ በአ'መ ለካከት ማስረ'ዳት [አስረ'ዳ] -ቅ- ፈ'ጣን

expression
አክስፕሬሽን -ስ- መልክ ፣ ፊት ፣ የመልክ ሁናቴ (ቋ'ጣ ፣ ሐዘን ፣ ደ'ስታ ወዘተ)

extend
አክስ'ቴንድ -ግ- መዘርጋት [ዘረ'ጋ] ፣ ማር ዘም [አረ'ዘመ] ፣ ማስረ'ዘም [አስረ'ዘመ]

extension
አክስ'ቴንሽን -ስ- ተጨ'ማሪ ነገር

extensive
አክስ'ቴንሲቭ -ቅ- ት'ልቅ ፣ የተዘረ'ጋ ፣ ሰ'ፊ

extenuate
አክስ'ቴንዩዌይት -ግ- የሠ'ሩትን ጥፋት ቀ'ላል አድርጎ ማሳየ'ት [አሳ'የ] ፣ ጥፋትን ማቅለል [አቀል'ል]

exterior
አክስ'ቲሪየ -ቅ- የውጭ ፣ አፍአዊ

exterminate
አክስ'ተ፡ሚኔይት -ግ- መፍጀት [ፈ'ጀ] ፣ መ ጨ'ረስ [ጨ'ረሰ] ፣ መደምሰስ [ደመ'ሰሰ]

external
አክስ'ተ፡ነል -ቅ- የው'ጭ ፣ አፍአዊ

extinct
አክስ'ቲንክት -ቅ- ያ'ለቀ ፣ የጠ'ፋ ፣ ዘሩ የ'ማ ይ'ገኝ (ለእንስሳት ዓይነት)

extinguish
አክስ'ቲንግዊሽ -ግ- ማጥፋት [አጠ'ፋ] (ለእ ሳት)

extort
አክስ'ቶ፡ት -ግ- በዛ'ቻ ፣ በኀይል መውሰድ [መ 'ሰደ] (ገንዘብ)

extra
'ኤክስትረ -ቅ- ሌላ ፣ ተጨ'ማሪ

extract
ኤክስት'ራክት -ግ- ማውጣት [አወ'ጣ] (በጎ ይል) ፣ መንቀል [ን'ቀለ]

extraordinary
ኤክስት'ሮዲንሪ -ቅ- ያልተለ'መደ ፣ እንግዳ የሆነ

extravagant
ኤክስት'ራቨንት -ቅ- ገንዘብ አባካኝ

extreme
ኤክስት'ሪይም -ቅ- ከባድ (ለሕ'ግ ፣ ለድሀ'ነት ወዘተ) ፣ ወደ አንድ ወገን ፈ'ጽሞ ያደ'ላ

exult
ኤክ'ዘልት -ግ- በጣም መ'ደሰት [ተደ'ሰተ]

eye
'አይ -ስ- ዓይን

eyebrow
'አይብራው -ስ- ቅንድብ

eyeglasses
'አይግላሲዝ -ስ- መነ'ጥር ፣ መነ'ጽር

eyelash
'አይላሽ -ስ- ሽፋሽፍት ፣ ሽፋል

eyelid
'አይሊድ -ስ- ያይን ቆብ

eyesight
'አይሳይት -ስ- ያይን ብርሃን

eye witness
'አይዊትነስ -ስ- ምስ'ክር ፣ ያይን ምስ'ክር

F

fable
'ፈይበል -ስ- ተረት

fabric
'ፋብሪክ -ስ- አካል ፣ ቅርፅ (ያንድ ነገር) ፣ ጨርቃ ጨርቅ ፣ ድር'ና ማግ (የጨርቅ)

fabricate
'ፋብሪኬይት -ግ- መሥራት [መ'ራ] (ዕቃ) ፣ ፈጥሮ ማውጣት [አወ'ጣ]

face
'ፈይስ -ግ- መግጠም [ገ'ጠመ] (ዓይን ለዓ ይን)
-ስ- ፊት ፣ መልክ

facetious
ፈ'ሺሽስ -ቅ- ፈዝ የ'ሚያበዛ (ያለበታው)

facilitate
ፈ'ሲሊቴይት -ግ- ቀ'ላል ማድረግ [አደ'ረገ] ፣ ች'ግር ማ'ቃለል [አ'ቃ'ለለ]

facility
ፈ'ሲሊቲ -ስ- ሥራ የ'ሚያ'ቀላ'ጥፍ መ'ሣ ሪያ ፣ አገልግሎት ወዘተ ፤ ሥራ ፣ ትምህርት ለማ'ከናወን የ'ሚረዳ ዘዴ

fact
'ፋክት -ስ- እውነት ፣ እርግጠ'ኛ ነገር

factor
'ፋክተ -ስ- ምክንያት ፣ የተለ'የ ው'ጤት ለማስገ'ንት የነ'በረ ሁናቴ

factory
'ፋክትሪ -ስ- ፋብሪካ

faculty
'ፋካልቲ -ስ- ል'ዩ ስጦታ ፣ ተውህቦ ፣ ችሎታ፤ በዩኒቨርስቲ ውስጥ ል'ዩ የትምህርት ክፍል ፤ የዩኒቨርስቲ መምህራን

fade
'ፈይድ -ግ- መደብዘዝ ፣ [ደበ'ዘዘ] ፣ ቀለም መልቀቅ [ለ'ቀቀ]

fail
'ፈይል -ግ- መውደቅ [መ'ደቀ]፣ (ፈተና ወዘተ)፣ ማቃተ [አቃተ] (አንድ ሥራ ፣ መ'ከራ)

faint
'ፈይንት -ግ- መዝለፍለፍ [ተዝለፈ'ለፈ]
-ቅ- ጉልህ ያልሆነ ፣ ደካማ

fair
'ፈየ -ቅ- ነጣ ያለ ፣ አድልዎ የሌ'ለ'በት ፣ የ'ማያ'ዳ'ላ ፤ ደረቅ'ና ጥሩ (ለአ'የር)

faith
'ፈይስ -ስ- እምነት

faithful
'ፈይትፉል -ቅ- ታ'ማኝ ፣ እመን

fake
'ፈይክ -ስ- እውነተ'ኛ ያልሆነ ፣ ማስመ'ሰያ ነገር

fall
'ፎ፡ል -ግ- መውደቅ [መ'ደቀ]

fallacy
'ፋለሲ -ስ- ውሸት

fallow
'ፋለው -ቅ- ታ'ርሶ ያ'ደረ መፈት

false
'ፎልስ -ስ- ውሸት ፣ የተሳሳተ (ለንግ'ግር)

falter
'ፎ፡ልተ -ግ- ፈ'ራ ተ'ባ ማለት [አለ] (በንግ 'ግር ፣ በርም'ጃ ፣ በሥራ ወዘተ)

fame
'ፈይም -ስ- ዝ'ና ፣ ጥሩ ስም

familiar
ፈ'ሚልየ -ቅ- የታ'ወቀ ፣ የተለ'መደ ፣ ብዙ ጊዜ ያ'ዩት ፣ የሰ'ሙት ወዘተ

family
'ፋሙሊ -ስ- ቤተ ሰብ

famine
'ፋሚን -ስ- ረኀብ (በገ'ድ አገር) ፣ ቀጠና

famous
'ፈይመስ -ቅ- ዝ'ነኛ ፣ ስመ ጥሩ ፣ ስመ ጥር

fan
'ፋን -ስ- ማ'ራገቢያ

fanatic
ፈ'ናቲክ -ቅ- አንድ ነገር ፣ ሐ'ሳብ በመደ'ጋፍ ፣ በመ'ቃወም የ'ሚ'መና'ኝክ ሰው ፣ እምነቱን (ሐ'ሳቡን) አለቅጥ የ'ሚያጤን ሰው

fancy
'ፋንሲ -ስ- ከእውነት የራቀ እምነት ፣ ሐ'ሳብ

fangs
'ፋንግዝ -ስ- የው'ሻ ከራንቻ ፤ አባብ መር ዙን የ'ሚያስተላ'ልፍ'በት ጥርስ

fantastic
ፋን'ታስቲክ -ቅ- ድንቅ ፣ ሊመሩት የ'ማይ 'ቻል (ዕ'ቅድ ፣ ሐ'ሳብ)

fantasy
'ፋንተሲ -ስ- ከእውነት የራቀ እምነት ፣ በሐ 'ሳብ እንጂ እሥራ ላይ ሊውል የ'ማይችል ነገር

far
'ፋ፡ -ቅ- ሩቅ

fare
'ፈየ -ስ- የጉዞ ዋጋ
food
-ስ- ምግብ

farewell
ፈ'ዌል -ቃለ- ደኅና ይሁኑ (ሁን)

farm
'ፋ፡ም -ስ- እርሻ (በታ)

farmer
'ፋ፡መ -ስ- ገበፊ ፣ እሬሻ

farther
'ፋ፡ዝ -ቅ- የራቀ ፣ ሩቅ

fascinate
'ፋሲኔይት -ግ- ማስደ'ነቅ [አስደ'ነቀ]

fashion
'ፋሽን -ግ- መቅረፅ [ቀ'ረፀ]
style
-ስ- ሞድ
fast
'ፋ፡ስት -ግ- መጦም [ጠመ] ፣ መጾም [ጸመ]
-ስ- ጦም ፣ ጾም
fast
ፋ፡ስት -ቅ- ፈ'ጣን ፣ የተጣ'በቀ ፣ በተ'ላሉ የ ግ ይ'ንቃን'ቅ
fasten
'ፋ፡ሰን -ግ- ማጥበቅ [አጠ'በቀ]
fastener
'ፋ፡ስነ -ስ- ማጥበቂያ
fat
'ፋት -ቅ- ወፍራም
of meat
-ስ- ስብ
fatal
'ኤይተል -ቅ- ሞት የ'ሚያስከ'ትል ፣ እደ'ኛ
fate
'ኤይት -ስ- ዕ'ድል ፣ እጣ
father
'ፋ፡ዝ -ስ- አ'ባት
father-in-law
-ስ- አማት (ለወንድ)
fatigue
ፈ'ቲይግ -ስ- የሰው'ነት ዝለት ፣ መድከም (በሥራ ምክን,ያት)
fatten
'ፋተን -ግ- ማ'ደፈር [አወ'ፈረ] ፣ መቀ'ለብ [ቀ'ለበ] (ለማስባት)
fault
'ፎልት -ስ- ስ'ነተት
faultless
'ፎልትሌስ -ቅ- እንከን የሌ'ለው
faulty
'ፎልቲ -ቅ- ስሕተት የመ'ላ'በት
favour
'ኤይቨ -ግ- መውደድ [ወ'ደደ]
-ስ- ውለታ
favourable
'ኤይቨረበል -ቅ- ጥሩ ፣ ተስማሚ
favourite
'ኤይቨሪት -ቅ- ተስማሚ ፣ አብልጠው የ'ሚ ወ'ዱት
fawn
'ፎ፡ን -ግ- ጅራት መቁላት [ቆ'ላ] (ለውሻ') ፣ ማ'ቆላመጥ [አ'ቆለ'መጠ]
colour
-ቅ- ግራ'ጫ
fear
'ኤየ -ስ- ፍርሃት
fearful
'ኤየፉል -ቅ- ፈሪ ፣ አስፈሪ
fearless
'ኤየለስ -ቅ- የ'ማይፈራ ፣ ደ'ፋር
feasible
'ኤይዘበል -ቅ- እሥራ ላይ ሊውል የ'ሚችል
feast
'ኤይስት -ግ- በዓል ማክበር [አከ'በረ]
-ስ- በዓል
feat
'ኤይት -ስ- ጀብዱ ፣ ከል'ክ ያ'ለፈ የጉብዝ'ና ሥራ
feather
'ፈዝ -ስ- ላባ (የወፍ ፣ የዶሮ ወዘተ)
features
'ኤይቸዝ -ስ- መልክ ፣ ያንድ ነገር የተለ'የ ጠባይ
February
'ፈብሩወሪ -ስ- የ'ካቲት
federation
ፈደ'ሬይሽን -ስ- ፈዴራሲዮን ፣ ባንድ ጠቅ ላይ አ'ገዛዝ የ'ሚ'ገ'ኙ ነጻ የውስጥ ደምብ ያ'ላቸው ያንድ መንግሥት አገር'ች
fee
'ኤይ -ስ- ለማኅበር'ኝ'ነት ፣ ለትምህርት'ለሕ 'ክም'ና ወዘተ የ'ሚ'ከ'ፈል ያገልግሎት ዋጋ
feeble
'ኤይበል -ቅ- ደካማ
feed
'ኤይድ -ግ- መመ'ገብ [መ'ገበ] ፣ ማብላት [አበ'ላ]
feeder
'ኤይደ -ስ- መ'ጋቢ (እንሰሳት ፣ እትክልጎ ተከባካቢ ፣ መ'ጋቢ (መንገድ)

feel
'ፊይል -ግ- መዳሰስ [ዳ'ሰሰ]
emotion
-ግ- መ'ሰማት [ተሰ'ማ] (ለስ'ሜት)
felicity
ፈ'ሊሲቲ -ስ- ደ'ስታ ፣ ሐ'ሤት
feline
'ፊይላይን -ቅ- የድመት ወገን
fell
'ፈል -ግ- መቁረጥ [ቆ'ረጠ] (ለዛፍ) ፣ መጣል [ጣለ]
fellow
'ፈለው -ስ- ጓ'ደ'ኛ ፣ ሰው
fellowship
'ፈለውሺፕ -ስ- ጓ'ደ'ኝ'ነት ፣ ማኅበር
felon
'ፈለን -ስ- ወንጀለ'ኛ (ከ'ባድ)
felony
'ፈለኒ -ስ- ከ'ባድ ወንጀል
felt
'ፈልት -ስ- ወፍራም ጨርቅ
female
'ፊይሚይል -ቅ- እንስት
feminine
'ፈመኒን -ቅ- እነስታዎ
fen
'ፈን -ስ- ረግረግ ፣ ጨቀጨቅ
fence
'ፈንስ -ስ- አጥር
ferment
ፈ'ሜንት -ስ- ብ'ብ'ብ ፣ ህውከት (የፖ'ሊቲክ)
ferment
'ፈ'ሜንት -ግ- መፍላት [ፈ'ላ] (ለዋንስስ) ፣ መቧከት [ቦ'ከ] (ለቡቡ ፣ ለሊጥ)
ferocious
ፈ'ሮውሽስ -ቅ- ጨ'ካኝ ፣ ጎይለ'ኛ ፣ አውሬ
fertile
'ፈ፡ታይል -ቅ- ለም (ለመሬት)
fertility
ፈ'ቲሊቲ -ስ- የመሬት ልማት ፣ መ'ሬባት (ለሰው ፣ ለእንስሳ)
fertilizer
'ፈ፡ቲላይዘ -ስ- የመሬት ማጻበሪያ

fertilize
'ፈ፡ቲላይዝ -ግ- እንዲ'ሬ'ባ ማድረግ [አደ'ረገ]
fervour
'ፈ፡ቨ -ስ- ጥልቅ ስ'ሜት ፣ ታ'ላቅ ፍ'ላጎት ፣ የመንፈስ መ'ታጠል
fester
'ፈስተ -ግ- መነፍረቅ [ነፈ'ረቀ] (ለቁስል)
festival
'ፈስቲቫል -ስ- በዓል ፣ ክብረ በዓል
fetch
'ፈች -ግ- ሄዶ ማምጣት [አመ'ጣ]
feud
ፍ'ዩ:ድ -ስ- ከ'ባድ የ'ቆየ ጥል (በሁለ'ት ቤተ ሰብ ፣ ሰዎ'ች መካ'ከል)
fever
'ፊይቨ -ስ- ት'ኩሳት (ሕመም)
few
ፍ'የው -ቅ- ጥቂት
fiance
ፊ'ያንሴ -ስ- እጮ'ኛ
fickle
'ፊከል -ቅ- እምነት የ'ማይ'ጣል'በት ፣ ከ'ዳ ተ'ኛ ፣ ተለዋዋጭ
fiction
'ፊክሽን -ስ- ል'ብ ወ'ለድ ታሪክ
fiddle
'ፊደል -ግ- መ'ጫወት [ተ'ጫ'ወተ] (አንድ ነገር በእ'ጅ ይዞ ባለማስተዋል)
cheat
-ግ- ማጭበርበር [አጭበረ'በረ]
fidget
'ፊጀት -ግ- መቁነጥነጥ [ተቁነጠ'ነጠ]
field
'ፊይልድ -ስ- ሜዳ ፣ መስክ ፣ የተመ'ሰ'ዩት ምህርት ዓይነት
fiend
'ፊይንድ -ስ- ሰይጣን ፣ ርኩስ መንፈስ ፣ በጣም ክፉ'ና ጨ'ካኝ ሰው
fierce
'ፊየስ -ቅ- አውሬ ፣ ጨ'ካኝ ፣ ጎይለ'ኛ
fifteen
ፊፍ'ቲይን -ቅ- ዐሥራ አ'ምስት
fifteenth
ፊፍ'ቲንስ -ቅ- ዐሥራ አ'ምስተ'ኛ

fifth
ʾፌፍቧ -ቅ- እ'ምስተ'ኛ
fiftieth
ʾፌፍቲየቧ -ቅ- እምሳ'ኛ
fifty
ʾፌፍቲ -ቅ- እምሳ
fig
ʾፌግ -ስ- የበለስ ፍሬ
fight
ʾፋይት -ግ- መ'ዋጋት [ተዋ'ጋ] ፣ መ'ታገል [ታ'ገለ]
-ስ- ው'ጊያ ፣ ትግል
figure
ʾፌገ -ስ- ቅርፅ ፣ መልክ ፣ አኳዃ
file
ʾፋይል -ስ- ሞረድ ፣ ፋይል ፣ የሰልፍ መሥመር
filings
ʾፋይሊንግዝ -ስ- ሙ'ሪጅ ፣ ብ'ናኛ
fill
ʾፌል -ግ- መሙላት [ሞ'ላ]
filling
ʾፌሊንግ -ስ- በተሰ'ቡረ ጥርስ ውስጥ የ'ሚ'ሞ'ላ ነገር
filly
ʾፌሊ -ስ- ያልተጠ'ቃ'ች ፈረስ
film
ʾፌልም -ስ- ፊልም
layer
-ስ- ሥሥ ሽፋን
filter
ʾፌልተ -ግ- ማ'ጣራት [አ'ጣ'ራ] (ለፈሳሽ)
-ስ- ማ'ጣሪያ
filth
ʾፌልፀ -ስ- ተውሳክ ፣ እድፍ ፣ ቁሻሻ
filthy
ʾፌልፂ -ቅ- እድፋም ፣ ቁሻሻ
filtration
ፊልት'ሬይሽን -ስ- ማ'ጣራት
fin
ʾፌን -ስ- የዐሣ ክንፍ
final
ʾፋይነል -ቅ- የመጨ'ረሻ
finance
ፊይ'ናንስ -ግ- በንንዘብ መርዳት [ረ'ዳ] ፣ ለአንድ ዕ'ቅድ ንንዘብ ማውጣት [አወ'ጣ]
-ስ- የመንግሥት ንንዘብ አስተዳደር
find
ʾፋይንድ -ግ- ማግኘት [አገ'ኘ]
finding
ʾፋይንዲንግ -ስ- ተፈ'ልጎ የተገ'ኘ ነገር ፣ ሕ'ጋዊ ው'ሳኔ(ም'ኾ)
fine
ʾፋይን -ስ- መቅጣት [ቀ'ጣ]
punishment
-ስ- ቅጣት
thin
-ቅ- ረቂቅ ፣ ሥሥ
good
-ቅ- ጥሩ ፣ መልካም
finery
ʾፋይነሪ -ስ- ጌጣ ጌጥ ያ'ለ'በት ልብስ
finger
ʾፌንገ -ስ- ጣት
finger-print
ʾፌንገፕሪንት -ስ- አሻራ
finish
ʾፌኒሽ -ግ- መጨ'ረስ [ጨ'ረሰ]
fir
ʾፌ: -ስ- የዛፍ ዓይነት (አርዘ ሊባኖስ የ'ሚመስል)
fire
ʾፋየ -ስ- እሳት
dismiss
-ግ- ከሥራ ማስወ'ገድ [አስወ'ገደ]
fire brigade
ʾፋየብሪጌይድ -ስ- የሳት አደጋ መ'ከላከያ ድር'ጅት
fireman
ʾፋየመን -ስ- የእሳት አደጋ መ'ከላከያ ወ'ታ'ደር
stoker
-ስ- ማገዶ አቅራቢ (በባቡር ላይ)
fireplace
ʾፋየፕሌይስ -ስ- ምድ'ጃ

fireproof
ʾፋየፕሩ:ፍ -ቅ- እሳት የ'ማያ'ቃ'ጠለው ፣ እሳት የ'ማይነዳው
firewood
ʾፋየውድ -ስ- ማገዶ
fireworks
ʾፋየወ:ክስ -ስ- ር'ችት
firm
ʾፈ:ም -ቅ- ጽኑእ ፣ ጠንካ'ራ
firmament
ʾፈ:መመንት -ስ- ጠፈር ፣ ሰማይ
firmness
ʾፈ:ምነስ -ስ- ጽኑእ'ነት ፣ ጠንካ'ራ'ነት
first
ʾፈ:ስት -ቅ- አንደ'ኛ ፣ የመጀ'መሪያ
firstborn
ʾፈ:ስትቦ:ን -ስ- የበኵር ልጅ
fiscal
ʾፈስከል -ቅ- የመንግሥት (ንንዘብ)
fish
ʾፈሽ -ስ- ዐሣ
fisherman
ʾፈሸመን -ስ- ዐሣ አጥማጅ ፣ ዐሣ አሥጋሪ
fishmonger
ʾፈሽመንገ -ስ- ዐሣ ነ'ጋዴ
fishy
ʾፈሺ -ቅ- ዐሣ ዐሣ የ'ሚሸ'ት
suspicious
-ቅ- የ'ማያ'ጠራ'ጥር (ነገር ፣ ሁናቴ)
fissure
ʾፈሼ -ስ- ስንጥቅ (በደንጊያ ወዘተ)
fist
ʾፈስት -ስ- ቡ'ጢ
fit
ʾፈት -ግ- መስማማት [ተስማ'ማ]
-ስ- የ'ሚጥል በ'ሽታ ፤ ደንገተ'ኛ ቁ'ጣ፥ ቅኖት ወዘተ
fitness
ʾፈትነስ -ስ- መስማማት
fitter
ʾፈተ -ስ- ገጣሚ (ዕቃ ፣ መኪና ወዘተ)
fitting
ʾፈቲንግ -ስ- የ'ሚ'ገ'ጠም ነገር ፣ አቤት ውስጥ የ'ሚገባ ነገር
suitable
-ቅ- የ'ሚስማ'ማ
five
ʾፋይቭ -ቅ- እ'ምስት
fix
ʾፈክስ -ግ- መለ'ጠፍ [ለ'ጠፈ]
mend
-ግ- ማበ'ጀት [አበ'ጀ] ፣ መጠ'ገን [መ'ገነ]
fixed
ʾፈክስት -ቅ- የተለ'ጠፈ
mended
-ቅ- የተበ'ጀ
fizz
ʾፈዝ -ግ- መፍላት [ፈ'ላ] (የታ'ሸገ መጠ'ጥ፣ ሲ'ከ'ፈት)
fizzy
ʾፈዚ -ቅ- የ'ሚፈላ
flabby
ፍ'ላቢ -ቅ- የሚዋ'ልል ፣ ጠንካ'ራ ያልሆነ ፣ ደክማ (ለጡንቻ ሥጋ)
flag
ፍ'ላግ -ስ- ሰን'ደቅ ዐላግ
-ግ- ተስፋ መቁረጥ ፣ [ቆ'ረጠ] ፣ መድ ከም [ደ'ከመ]
flagon
ፍ'ላጎን -ስ- ት'ልቅ ጠርሙዝ (የመጠ'ጥ መ ያዣ)
flagrant
ፍ'ሌይግረንት -ቅ- ደ'ፋር ፣ የ'ማያፍር ፣ ዓይነ ደረቅ
flagstaff
ፍ'ላግስታ:ፍ -ስ- የሰን'ደቅ ዐላግ እንጨት ፣ ሰን'ደቅ
flail
ፍ'ሌይል -ግ- መውቃት [መ'ቃ] (በዘ'ቅር)
-ስ- መውቂያ በ'ቅር
flair
ፍ'ሌየ -ስ- የተፈጥሮ ስጦታ ፣ ተውህቦ
flamboyant
ፍላም'ቦየንት -ቅ- እፉ'ኛ እፀ'ኛ ባይ ፣ ጉ'ረ'ኛ ፣ ጌጣ ጌጥ የበ'ዛ'በት

flame
ፍ'ሌይም -ስ- ነበልባል
flange
ፍ'ላንጅ -ስ- ዘርፍ
flank
ፍ'ላንክ -ስ- ሽንጥ
flannel
ፍ'ላኔል -ስ- ወፈ'ር ያለ የሱፍ ልብስ
flap
ፍ'ላፕ -ግ- መውለብለብ [ተውለበ'ለበ]
-ስ- ክዳን
flare
ፍ'ለየ -ግ- ቡ'ግ ማለት [አለ] (ለጥቂት ጊዜ)
flash
ፍ'ላሽ -ግ- ቡ'ግ ማለት [አለ] ፣ ማብለጭለጭ [አብለጨ'ለጨ]
-ስ- ድንገተ'ኛ ብርሃን
flask
ፍ'ላ፡ስክ -ስ- ኮ'ዳ
flat
ፍ'ላት -ቅ- የተዘረ'ጋ ፣ አሰልቺ
-ስ- በፎት ላይ እንድ መኖሪያ ቤት
tyre
የፈነ'ዳ ፣ የተነ'ፈሰ ጎ'ማ
flatiron
ፍ'ላታየን -ስ- ካውያ
flatten
ፍ'ላተን -ግ- መደመ'ስ [ለ'መመ]
flatter
ፍ'ላተ -ግ- ማ'ቆላመጥ [አ'ቆላ'መመ] ፣ ማስ ደ'ሰት [አስደ'ሰተ]
flattery
ፍ'ላተሪ -ስ- ቁልም'ጫ
flaunt
ፍ'ሎ፡ንት -ግ- በግልጽ አለመ'ታዘዝ [-ታዘ'ዘ]
flavour
ፍ'ሌይቨ -ስ- መዓዛ ፣ ጣዕም ,
flaw
ፍ'ሎ፡ -ስ- እንከን
flaxen
ፍ'ላክሰን -ቅ- የገረ'ጣ (ለጠጉር)
flay
ፍ'ሌይ -ግ- ቆዳ መግፈፍ [ገ'ፈፈ] (ለቅጣት)
flea
ፍ'ሊይ -ስ- ቁን'ጫ
fleck
ፍ'ሌክ -ስ- ነቁጥ ፣ ጉድፍ
flee
ፍ'ሊይ -ግ- መሸሽ [ሸ'ሸ] ፣ መጥፋት [ጠ'ፋ]
fleece
ፍ'ሊይስ -ስ- የበግ ጠጉር
fleet
ፍ'ሊይት -ስ- የጦር መርከቦ'ች
-ቅ- በፍጥነት የ'ሚሮጥ
flesh
ፍ'ሌሽ -ስ- ሥጋ
fleshy
ፍ'ሌሺ -ቅ- ወፍራም
flex
ፍ'ለክስ -ግ- ማጠፍ'ና መዘርጋት [አ'ጠፈ ፣ ዘረ'ጋ]
-ስ- የተሸ'ፈነ ሽቦ
flexibility
ፍሌክሲ'ቢሊቲ -ስ- የመታጠፍ ችሎታ ፣ ግ'ትር አለመሆን ፣ ሐ'ሳብን በቀ'ላሉ የመለ'ወጥ ችሎታ
flexible
ፍ'ለክሲበል -ቅ- መ'ታጠፍ የ'ሚችል ፣ ግ'ትር ያልሆነ ፣ ሐ'ሳቡን በቀ'ላሉ የ'ሚለወ'ጥ
flick
ፍ'ሊክ -ግ- በጣት ማስፈን'ጠር [አስፈነ' ጠረ] ፣ ጣት ማሮ'ሽ [አሮ'ሸ] (ለመጥራት)
flicker
ፍ'ሊክ -ግ- መደብዘዝ [ደበ'ዘዘ] (ጧፍ ፣ ሻማ)
flier
ፍ'ላየ -ስ- በራሪ ፣ አውሮ'ፕላን ነጂ
flight
ፍ'ላይት -ግ- ሽ'ሸት ፣ መብረር
flighty
ፍ'ላይቲ -ቅ- የ'ማይ'ታ'መን
flimsy
ፍ'ሊምዚ -ቅ- በጣም ቀ'ጭ'ን'ና ቀ'ላል ፣ በቀ'ላሉ ሊ'በላ'ሽ ፣ ሊ'ን'ጻ የ'ሚችል
flinch
ፍ'ሊንች -ግ- ወደኋላ ማፈግፈግ [አፈገ'ፈገ] (ከፍርሃት ፣ ከስ'ቅር የተነ'ሣ)

fling
ፍ'ሊንግ -ግ- መወርወር [ወረ'ወረ]
flint
ፍ'ሊንት -ስ- ደን'ጊያ (የሊጃራ ማ'ቀጣጠያ ወ ዘተ)
flippant
ፍ'ሊፕንት -ቅ- የ'ማይገ'ደው ፣ ደንታ ቢስ
flirt
ፍ'ለ፡ት -ግ- ማሽኮርመም [አሽኮረ'መመ]
flirtation
ፍለ'ቴይሽን -ስ- ማሽኮርመም
flit
ፍ'ሊት -ግ- ብ'ር ብ'ር ማለት [አለ]
float
ፍ'ለውት -ግ- መንሳፈፍ [ተንሳ'ፈፈ]
flock
ፍ'ሎክ -ስ- መንጋ (የበግ)
floe
ፍ'ለው -ስ- የ'ሚንሳ'ፈፍ የበረዶ ቀ'ራጭ
flog
ፍ'ሎግ -ግ- መግረፍ [ገ'ረፈ]
flood
ፍ'ለድ -ስ- ጎርፍ
floodlight
ፍ'ለድላይት -ስ- ት'ልቅ መብራት (በቤት ው'ጭ)
floor
ፍ'ሎ፡ -ግ- መጣል [ጣለ] (መ'ቶ)
-ስ- ወለል
storey
-ስ- ፎቅ ፡ ደርብ
floral
ፍ'ሎ፡ረል -ቅ- የአበባ
florid
ፍ'ሎሪድ -ቅ- የቀ'ላ (ለመልክ) ፣ በጣም ያጌጠ
florist
ፍ'ሎሪስት -ስ- አበባ ሻጭ
flotsam
ፍ'ሎትሰም -ስ- በወሃ ላይ የተንሳ'ፈፈ ነገር (ቆሻሻ ፣ የመርከብ ስ'ባሪ ወዘተ)
flour
ፍ'ላወ -ስ- ዱቄት
flourish
ፍ'ለሪሽ -ግ- ግግር [አግረ] ፣ መሥመር [ሠ'መረ]
flow
ፍ'ለው -ግ- መፍሰስ [ፈ'ሰሰ]
flower
ፍ'ላወ -ስ- አበባ
fluctuate
ፍ'ለክቹዌይት -ግ- መ'ለዋወጥ [ተለዋ'ወጠ] (ለእንቅስ'ቃሴ) ፣ መድከም [ደ'ከመ] ፣ መበር ታት [በረ'ታ]
flue
ፍ'ሉ፡ -ስ- የጢስ መውጫ (በቤት ውስጥ)
fluent
ፍ'ሉወንት -ቅ- አንደበተ ቀ'ና
fluff
ፍ'ለፍ -ስ- የተጠቀ'ለለ የሱፍ የጥጥ ወዘተ ብ'ናኝ
fluid
ፍ'ሉዊድ -ስ- ፈሳሽ (ውሃ ፣ ወተት ፣ ወዘተ)
fluke
ፍ'ሉ፡ክ -ስ- አ'ጋጣሚ ፅ'ድል
flurry
ፍ'ለሪ -ስ- ድንገተ'ኛ ሩ'ጫ ፣ መበርገግ ፣ ድንገተ'ኛ የነፋስ ሽ'ውታ
flush
ፍ'ለሽ -ግ- መቅላት [ቀ'ላ] (ቀለም)
wash away
-ግ- ጠርጎ መሄድ [ሄደ]
fluster
ፍ'ለስተ -ግ- ግ'ደናበር [አ'ደና'በረ] ፣ ግ'ደ ናገር [አ'ደና'ገረ]
flute
ፍ'ሉ፡ት -ስ- ዋሽንት
flutter
ፍ'ለተ -ግ- ብ'ር ብ'ር ማለት [አለ]
fly
ፍ'ላይ -ግ- መብረር [በ'ረረ]
-ስ- ዝምብ
foal
'ፎውል -ስ- የፈረስ ግልገል ፣ የአህ'ያ ውር ንጫ ፣ ውርንጭ'ላ

foam
'ልውም -ግ- አረፋ መድፈቅ [ደ'ፈቀ]
-ስ- አረፋ ፣ ኮረፋ
fodder
'ደፎ -ስ- የደ'ረቀ የእንስሳት ምግብ (ድርቆሽ፣ ገለባ ወዘተ)
foe
'ፈው -ስ- ጠላት ፣ ባላንጋራ
foetus
'ፈተስ -ስ- ሺል
fog
'ፎግ -ስ- ጉም ፣ ጭጋግ
foggy
'ፎጊ -ቅ- ጭጋጋም
foil
'ፎይል -ግ- ወንጀል እንዳይሠራ ማቆም [አ ቆመ]
tin-
-ስ- የብ'ር መልክ ያ'ለው ወረቀት
fold
'ፎልድ -ግ- ማጠፍ [አጠ'ፈ]
folder
'ፎልደ -ስ- ጾሴ
foliage
'ፈውሊያጅ -ስ- ቅጠላ ቅጠል
folk
'ፈውክ -ስ- ሕዝብ
folk-lore
'ፈውክሎ፡ -ስ- ያ'ባቶ'ች ተረት ፣ እምነት ፣ ባህል (ጥናት)
follow
'ፎለው -ግ- መ'ከተል [ተከ'ተለ]
follower
'ፎለው -ቅ- ተከ'ታይ ፣ ደ'ጋፊ (የእምነት ወዘተ)
folly
'ፎሊ -ስ- ቂል'ነት ፣ ጅል'ነት
foment
ፈ'ሜንት -ግ- መፍላት [ፈ'ላ] (ጥንስስ) ፤ ብጥ ብጥ ማንሣት [አነ'ሣ]
fond
'ፎንድ -ቅ- አፍቃሪ ፣ የ'ሚወ'ድ
fondle
'ፎንደል -ግ- ማሻሸት [አሻ'ሸ] ፣ መደባበስ [ደባ'በሰ]
font
'ፎንት -ስ- ማጥመቂያ ገበታ (በቤተ ክርስቲ ያን ውስጥ)
food
'ፉ:ድ -ስ- ምግብ
fool
'ፉ:ል -ስ- ቂል ሰው ፣ ሞ'ኝ ሰው
-ግ- ማ'ታለል [አ'ታ'ለለ] ፣ ማቂል [አቂለ]
foolish
'ፉ:ሊሽ -ቅ- ቂል ፣ ሞ'ኝ
foot
'ፉት -ስ- እግር
foothold
'ፉትሆውልድ -ስ- የእግር መቆንጠጫ ፣ መ'ቆ ናጠጫ ቦታ
footman
'ፉትመን -ስ- አ'ጃቢ (ፈረስ'ኛን ወዘተ) ፣ እገ ልጋይ (እንግዳ በማስገ'ባት'ና በማስተናገድ)
footpath
'ፉትፓ:ስ -ስ- የግር መንገድ
footprint
'ፉትፕሪንት -ስ- ዱካ
for
'ፎ: -መዋ- ለ . . .
-መፃ- ስለ
forage
'ፎሪጅ -ግ- ቀ'ለብ መሰብሰብ
-ስ- የእንስሳት ምግብ ፣ መ'ኖ
forbear
ፎ'ቤየ -ግ- አንድ ነገር ከመሥራት ራስን መግታት [ገ'ታ]
forbear
'ፎቤየ -ስ- አያት ቅድም አያት
forbid
ፈ'ቢድ -ግ- መከልከል [ከለ'ከለ]
force
'ፎ:ስ -ግ- ማስገ'ደድ [አስገ'ደደ]
-ስ- ኀይል
forceps
'ፎ:ሴፕስ -ስ- ወረንጦ

ford
'ፎ:ድ -ግ- ጥልቅ ባልሆነ ቦታ ወንዝ መ'ሻገር [ተሻ'ገረ]
-ስ- ወንዝ መ'ሻገሪያ ቦታ
forearm
'ፎ:ራ:ም -ስ- ክንድ
foreboding
ፈ'በውዲንግ -ስ- ፍርሃት (ለ'ሚመጣ ሁናቴ)
forecast
'ፎ:ካስት -ግ- መ'ነበይ [ተነ'በየ] ፣ ወደፊት የ'ሚሆነውን ነገር መ'ናገር [ተና'ገረ]
forefather
'ፎ:ፋ:ዜ -ስ- አያት ቅድም አያት
forefinger
'ፎ:ፊንገ -ስ- ሴባ ጣት
forehead
'ፎረድ -ስ- ግንባር ፣ ግምባር
foreigner
'ፎሪነ -ስ- የው'ጭ አገር ሰው
foreman
'ፎ:መን -ስ- ሞያተ'ኞ'ች ተቆጣጣሪ ፣ አለቃ
foremost
'ፎ:መውስት -ቅ- የመጀ'መሪያ ፣ በጣም አስ ፈ'ላጊ
forenoon
'ፎ:ኑ:ን -ስ- ጧት ፣ ከቀትር በፊት
forerunner
'ፎ:ሩነ -ስ- መንገድ ጠራጊ (አንድ ነገር መም ጣቱን የ'ሚነገር)
foresee
ፎ'ሲ -ግ- የ'ሚመጣውን ማወቅ [ዐ'ወቀ] ፣ ወደፊት ለ'ሚመጣው ሁናቴ መ'ዘጋጀት [ተዘ ጋ'ጀ]
foreshadow
ፎ'ሻደው -ግ- ቀድሞ ማስጠንቀቅ [አስጠ ነ'ቀቀ] ፣ ማመልከት [አመለ'ከተ]
foresight
'ፎ:ሳይት -ስ- ለ'ሚመጣ ች'ግር አስቀ'ድሞ ማ'ሰብ ፣ ሁናቴዎ'ችን ቀድሞ የማየት ተግባር
forest
'ፎረስት -ስ- ደ'ን ፣ ጫር
forestall
ፎስ'ቶ:ል -ግ- አንድ ነገር ቀድሞ በመሥ ራት ሌላው እንዳይሠራው ማድረግ [አደረ'ገ]
forester
'ፎረስተ -ስ- ደ'ን ጠባቂ
forestry
'ፎረስትሪ -ስ- የደ'ን አ'ያያዝ ትምህርት
forewarn
ፎ'ዎ:ን -ግ- በቅድሚያ ማስጠንቀቅ [አስጠ ነ'ቀቀ]
foreword
'ፎወ:ድ -ስ- የመጽሐፍ መቅድም (ብዙውን ጊዜ ከደራሲው ያልሆነ)
forfeit
'ፎፌት -ግ- በቅጣት መልክ አንድ ነገር ማጣት [አ'ጣ] (በሕ'ግ ፣ በስፖርት)
-ስ- ቃል የገ'ቡበትን ነገር ለመፈ'ጸም መያዣ ገንዘብ ፣ የዋስት'ና ገንዘብ
forge
'ፎ:ጅ -ግ- ብረት መቀጥቀጥ [ቀጠ'ቀጠ] (ቅር ፅ ለመስጠት) ፣ ለማ'ታለል አስመ'ስሎ መሥ ራት [መ'ራ] (ፈርማ ፣ ገንዘብ)
forgery
'ፎ:ጀሪ -ስ- ሕ'ጎ ወ'ጥ ገንዘብ መሥራት ፣ ማስረ'ጃ ፣ መዝገብ ወዘተ ማ'ታወስ (ለማጭ በርበር)
forget
ፈ'ጌት -ግ- መርሳት
forgive
ፈ'ጊቭ -ግ- ይቅር ማለት [አለ]
forgo
ፎ'ጎው -ግ- መተው [ተወ]
fork
'ፎ:ክ -ስ- ሹ'ካ ፣ ባ'ላ
pitch-
-ስ- መንሽ
forlorn
ፈ'ሎ:ን -ቅ- ያ'ዘነ ፣ የተ'ከዘ ፣ የከ'ፋው
form
'ፎ:ም -ስ- ቅርፅ
formal
'ፎ:መል -ቅ- የተወ'ሰነ ሕ'ግ የተከ'ተለ ፣ ሥነ ሥርዓታ'ዊ ፣ ጠባቡ የ'ማያ'ወላ'ውል
formality
ፎ'ማሉቲ -ስ- ሥነ ሥርዓት ፣ ወግ
former
'ፎ:መ -ቅ- የቀድሞ

formerly
'ፎ:መሊ ·ተ፦ ባ'ለፈው ጊዜ\
formidable
'ፎ:ሚደበል ·ቅ· አስቸ'ጋሪ ፣ ጎይለ'ኛ ፣ መሰ ናክል የበ'ዛ'በት
formulate
'ፎ:መዩሌይት ·ግ· መሥራት [ሠ'ራ] (ዕ'ቅድ)
forsake
ፈ'ሴይክ ·ግ· መክድ [ካደ] ፣ መተው [ተመ]
forthcoming
ፎ:ዝ'ኩሚንግ ·ቅ· ወደፊት የ'ሚመጣ
fortification
ፎ:ቲፈ'ኬይሽን ·ስ· ም'ሽግ
fortify
'ፎ:ቲፋይ ·ግ· መመ'ሸግ [መ'ሸገ]
fortitude
'ፎ:ቲትዩ:ድ ·ስ· ጀግን'ነት ፣ ለች'ግር ለመ'ቃይ አለመ'ባነር
fortnight
'ፎ:ትናይት ·ስ· ሁለ'ት ሳም'ንት
fortress
'ፎ:ትረስ ·ስ· ም'ሽግ ፣ አምባ
fortunate
'ፎ:ችኑትን ·ቅ· ዕ'ድለ'ኛ
fortune
'ፎ:ችዩን ·ስ· ዕ'ድል ፣ ሀብት ፣ ብዕል
forty
'ፎ:ቲ ·ቅ· አርባ
forward
'ፎወድ ·ተ፦ ወደፊት
fossil
'ፎሰል ·ስ· እመራት ላይ የ'ሚ'ገኝ የቀድሞ ታሪክ ምል'ክት (የጀ'ሪቁ ሕይወት የነ'በራ 'የው ፍጥረቶች)
foster
'ፎስተ ·ግ· ማ'በረታ'ታት [አ'በረታ'ታ] ፣ ማላ'ያዝ [አላ'ያዘ]
foster-father
'ፎስተ፦ዛ ·ስ· የጡት አ'ባት
foster-mother
'ፎስተ፦ሙ ·ስ· የጡት እ'ናት
foul
'ፋውል ·ቅ· በጣም የቆ'ሸሸ ፣ አስቀ'ያሚ ፣ መጥፎ ሽ'ታ'ና ጣዕም ያ'ለው ፣ ሽ'ረ'ኛ
sport
·ስ· ስሕተት ፣ ጥፋት
found
'ፋውንድ ·ግ· መመ'ሠረት [መሠ'ረተ]
foundation
ፋውን'ዴይሽን ·ስ· መሠረት
founder
'ፋውንደ ·ስ· መሥራች
foundling
'ፋውንድሊንግ ·ስ· ወድቆ የተ'ገ'ኘ ሕፃን
foundry
'ፋውንድሪ ·ስ· የብረት ማቅለጫ
fount
'ፋውንት ·ስ· ምንጭ (የውሃ)
fountain
'ፋውንተን ·ስ· ምንጭ (የውሃ)
four
'ፎ: ·ቅ· አራ'ት
fourteen
ፎ:'ቲይን ·ቅ· ዐሥራ አራ'ት
fourteenth
ፎ:'ቲይንዝ ·ቅ· ዐሥራ አራ'ተ'ኛ
fourth
'ፎ:ዝ ·ቅ· አራ'ተ'ኛ
fowl
'ፈውል ·ስ· ወፍ ፣ ዶሮ
fox
'ፎክስ ·ስ· ቀበሮ
fraction
ፍ'ራክሽን ·ስ· ስ'ባሪ ፣ ያንድ ሙሉ ነገር ክፍል (ሌሌ.ሳብ)
fracture
ፍ'ራክቸ ·ስ· ስ'ብራት (የዐጥንት)
fragile
ፍ'ራጃይል ·ቅ· በቶ'ላሉ የ'ሚ'ሰ'በር
fragment
ፍ'ራግመንት ·ስ· ስ'ባሪ
fragrance
ፍ'ራይግረንስ ·ስ· መዓዛ ፣ ጥሩ ሽ'ታ

fragrant
ፍ'ሬይግረንት ·ቅ· ጥሩ ሽ'ታ ያ'ለው ፣ ሽ'ታው የ'ጣ'ም'ኖር
frail
ፍ'ሬይል ·ቅ· ደ'ካማ (በሰው'ነተ ጠባይ) ፣ በተ'ላሉ የ'ሚ'ሰ'በር
frame
ፍ'ሬይም ·ቅ· ከፈ'ዘ ፣ ሰው'ነት ፣ አካል
framework
ፍ'ሬይምወ'ክ ·ስ· ቅርፅ በመስጠት ፣ ድ'ጋፍ በመሠ'ረ የ'ሚያ'ገለ መ'ሣሪያ ፣ ሥርዓት ፣ መሠረት (ለመንግሥት ፣ ለዕ'ቅድ መዘተ)
franchise
ፍ'ራንች'ይዝ ·ስ· የመ'ረተ መ'ሉ መብት (የ ሕዝቡን እንደራሴዎች መም'ረጥ)
frank
ፍ'ራንክ ·ቅ· ግልጽ ፣ እመ'ኑ'ኛ ፣ ቀ'ጥ'ተ'ኛ (ነገር የ'ማያ'ወላ'ዝል)
frantic
ፍ'ራንቲክ ·ቅ· የተደና'ገ'ረ (ከሥ'ቃይ ፣ ከፀ ሩፈት መዘተ የተነ'ሣ)
fraternal
ፍ'ተ'ንል ·ቅ· የወን'ድ'ም'ነት
fraternity
ፍ'ተ'ንቲቲ ·ስ· ወን'ድ'ም'ነት
fraternize
ፍ'ተ፦ናይዝ ·ግ· መ'ወዳጀት [ተመ'ሠ]
fraud
ፍ'ሮ:ድ ·ስ· ማጭበርበር (ለገንዘብ)
fray
ፍ'ሬይ ·ግ· መ'ጣ'ላ [ጣ'ለ]
fight
·ስ· ፕል : ውጊ'ያ
freak
ፍ'ሪ:ክ\ ·ስ· ያል'ተ'ለመ'ደ ቅርፅ : መልክ ፣ ጀል ሉ'ሳዊ ያ'ልሆ ሰው
freckles
ፍ'ሬክለዝ ·ስ· በሰው'ነት ቆዳ ዋጀ'ቁር ምል'ክቶ'ች
free
ፍ'ሪይ ·ግ· ነጻ ማውጣት [አወ'ጣ]
without payment
·ቅ· ነጻ : ያለ ዋ.ጋ

freedom
ፍ'ሪይደም ·ስ· ነጻ'ነት
freeze
ፍ'ሪይዝ ·ግ· ወደ በረ'ዶ'ነት መ'ለወጥ [ተቀ'መ] ፣ ወደ በረ'ዶ'ነት መ'ለወጥ [አ'መመ]
freight
ፍ'ሬይት ·ስ· በየብስ ፣ በመርከብ ፣ ዓውሮ'ፕላን የ'ሚ'ላክ ዋጋ'ኑ ፣ ለጭነት የ'ሚከ'ፈል ክ'ፍያ
French
ፍ'ረንች ·ቅ· ፈረንሳይ
language
·ስ· ፈረንሳይ'ኛ
frenzy
ፍ'ሬንዚ ·ስ· የእብድ'ነት ሥ'ራ
frequent
ፍ'ሪኩ'ወንት ·ግ· ማመ'ላለ'ስ [አመ'ላለ'ሰ]
ፍ'ሪኩወንት ·ተ፦ ውል ጊዜ
fresh
ፍ'ሬሽ ·ቅ· ቀ'ዝ'ቃ ፣ ቀዝ'ፃ (ለነፋስ)
freshman
ፍ'ሬሽ፦ን ·ስ· በዩኒቨርሲቲ ያገ'ኛ'ኛ ዓመት ተማሪ
fret
ፍ'ሬት ·ግ· ልቅ'ነቱ ነገር መጨ'ነቅ [ተጨ'ነቀ]
fretful
ፍ'ሬትፉል ·ቅ· ያለተ'ስተ'ሰተ : ቅ'ር ያለው
friar
ፍ'ሪየ ·ስ· መ'ነኩሴ (የተለ'የ ሥርዓት ወገ የሆነ)
friction
ፍ'ሪክሽን ·ስ· ሠ'ፋተ'ግ
trouble
·ስ· አለመ'ግባባት : በሌ'ላ ላይ መ'ለያ የት
Friday
ፍ'ሪይዲይ ·ስ· ዓር'ብ
friend
ፍ'ሬንድ ·ስ· ወዳጅ ፣ ጓ'ደ'ኛ ፣ ረ'ዳት
friendship
ፍ'ሬንድሺፕ ·ስ· ወዳ'ጅ'ነት
fright
ፍ'ራይት ·ስ· ፍ.ርኃት (ትልቅ'ና ደንገተ'ኛ)

frightful
ፍ'ሬይትፉል ፦ ስ. በጣም የ'ሚያስፈ'ራ ፣ የ'ሚ ያስደነ'ግጥ
frigid
ፍ'ሪጂድ ፦ ስ. የቀዘ'ቀዘ (ለወላጅ'ነት)
women
፦ ቀዝቃ'ዛ (ለአ'የር ፣ ለስ'ሜት)
frill
ፍ'ሪል ፦ ሰ. የልብስ ጌጥ (የጨርቅ ፣ ተጭ'ብ ርቦ የተሠ'ራ)
fringe
ፍ'ሪንጅ ፦ ሰ. ዘርፍ ፣ መርጫ (የልብስ)
frisky
ፍ'ሰክ. ፦ ቁ. ጨ'ፋራ ፣ ፈንጣዥ
fritter
ፍ'ሪተ' ፦ ግ. መሰባበር [ሰባ'በረ] ፣ ማድቀቅ [አደ'ቀቀ] ፣ ተስ በቀ'ስ ማባከን [አባ'ከነ] (ለገ ንዘብ ለጊዜ ወዘተ)
frivolous
ፍ'ሪቮለስ ፦ ቅ. ዋጋ ቢስ ፣ እርባን የሌ'ለው ፣ ሞ'ኝ ፣ ባዶ አንጉል
frock
ፍ'ርክ ፦ ሰ. መ'ጐናጸፊያ ፣ ቀሚስ
frog
ፍ'ሮግ ፦ ሰ. እንቁራሪት
frolic
ፍ'ሮለክ ፦ ግ. መፈንጠዝ [ፈን'ጠዘ]
from
ፍ'ሮም ፦ ኅ. ከ . . .
front
ፍ'ረንት ፦ ሰ. ፊት
frontier
ፍ'ረንቲየ ፦ ሰ. ያገር መሰን
frost
ፍ'ሮስት ፦ ሰ. ውርጭ
froth
ፍ'ሮ፬ ፦ ሰ. አረፋ
frown
ፍ'ራውን ፦ ግ. ፊት ማ'ኰሳተር [አ'ኰሳ'ተረ]
frozen
ፍ'ረውዘን ፦ ቅ. ወደ በረዶ'ነት የተለ'ወጠ
frugal
ፍ'ሩጎል ፦ ቅ. ገንዘብ ቆ'ጣቢ (ለምግብ)
fruit
ፍ'ሩ'ት ፦ ሰ. ፍሬፍሬ
fruitful
ፍ'ሩ'ትፉል ፦ ቅ. ፍሬ የ'ሚሰጥ ፣ ሲመልድ የ'ሚችል ፣ ዋጋ ያ'ለው
fruition
ፍሩ'ዊሽን ፦ ሰ. ፍሬ ማፍሪያ ጊዜ ፣ መ'ከናወን (ያ'ቀዱት ዕ'ቅድ) ፣ የ'ሥራ ከን'ውን
fruitless
ፍ'ሩ'ትለስ ፦ ቅ. ፍሬ የ'ማይሰጥ
frustrate
ፍረስት'ሬይት ፦ ግ. ማ'ደናቀፍ [አ'ደና'ቀፈ] ፣ (ለሥራ ፣ ለዕ'ቅድ) ፣ ማ'ሣቀቅ [አ'ሣ'ቀቀ] ፣ ማ'ጨናገፍ [አ'ጨና'ገፈ]
frustration
ፍረስት'ሬይሽን ፦ ሰ. ተስፋ መቁረጥ ፣ መ'ደና ቀፍ ፣ መ'ሣቀቅ
fry
ፍ'ራይ ፦ ግ. መጥበስ [መ'በሰ]
frying-pan
ፍ'ራይንግ ፓን ፦ ሰ. መጥበሻ
fuel
ፍ'ዌል ፦ ሰ. ማገዶ ፣ ነዳጅ
fugitive
ፍ'ዩጂቲቭ ፦ ሰ. የተ'ደደ ፣ የተባ'ረረ ሰው ፣ ኮብላይ
fulfil
ፉል'ፊል ፦ ግ. ፉል ማከበር [አከ'በረ] ፣ ዕ'ቅ ድ አ'ሥራ ላይ ማዋል [አዋ'ለ]
fulfillment
ፉል'ፊልመንት ፦ ሰ. መፈ'ጸም (ተስፋ ፣ ግ'ዴ ጅ ወዘተ) ፣ መ'ፈጸም (ያ'ሰቡት ፣ የተመ'ኙት)
full
'ፉል ፦ ቅ. ሙሉ
fully
'ፉሊ ፦ ተ. በሙሉ
fumble
'ፈምበል ፦ ግ. መደባበስ [ደባ'በሰ] (አንድ ነገር ለመፈ'ለግ) ፣ አንድ ነገር ደጋና አድርጎ በእ'ጅ መያዝ አለመቻል [-ቻ'ል]
fume
ፍ'ዩም ፦ ሰ. ጢስ (ማ'ነ'ሻው'ም ዓይነት)
fumigate
ፍ'ዩመጌይት ፦ ግ. በጢስ ማጠን [አ'ጠነ] (ተ ባዩ ለመግደል)

fun
'ፈን ፦ ሰ. ደ'ስታ ፣ ጨዋታ ፣ ቀልድ
function
'ፈንክሽን ፦ ሰ. ሥራ ፣ ተግባር
fund
'ፈንድ ፦ ሰ. የተሰበ'ሰበ ገንዘብ (ላንድ ተግባር እንዲውል) ፣ በብዛት የ'ሚ'ገ'ኝ ነገር
fundament
'ፈንደመንት ፦ ሰ. መሠረት ፣ ቢጋር
fundamental
ፈንደ'ሜንተል ፦ ቅ. መሠረታዊ
funeral
ፍ'ዩ፦ነረል ፦ ሰ. ሥርዓተ ቀብር
fungus
'ፈንገስ ፦ ቅ. የእንጉዳይ ዓይነት ተክል
funnel
'ፈነል ፦ ሰ. የጢስ መውጫ (የመርከብ ፣ የባ ቡር)፡ማንቆርቆርያ (የድፍ ዋንጫ ቅርፅ ያ'ለው)
funny
'ፈኒ ፦ ቅ. የ'ሚያ'ሥቅ
strange
፦ የ'ሚያስገ'ርም
fur
'ፈ: ፦ ሰ. ለምድ ፣ ደበሎ
furious
ፍዮ:ሪየስ ፦ ቁ. ቱ'ሩ
furl
'ፈ:ል ፦ ግ. መጠቅለል [ጠቀ'ለለ] (ለሰን'ደቅ ዓላማ ወዘተ)
furnace
'ፈ:ነስ ፦ ሰ. እቶን ፣ ከውር
furnish
'ፈ:ኒሽ ፦ ግ. ቤት በዕቃ መመላት [ሞ'ላ]
provide
፦ ማቅረብ [አቀ'ረበ]
furniture
'ፈ:ኒቸ ፦ ሰ. የቤት ዕቃ
furrow
'ፈረው ፦ ሰ. ትልም ፣ ፈር
further
'ፈ:ዘ ፦ ተ. ተጨ'ማሪ ፣ ራ'ቅ ያለ
ፈተግ ከ'ዚህ በላይ ፣ ደግሞ
furtive
'ፈ:ቲቭ ፦ ቅ. ተንኰለ'ኛ ፣ የ'ሚያደርገውን የ 'ሚደ'ብቅ
fury
ፍ'ዩ:ሪ ፦ ሰ. ቁ'ጣ ፣ ኃይለ'ኛ ን'ዴት
fuse
ፍ:ዩዝ ፦ ሰ. ዥልቾላ (የኤሌክትሪክ)
fuss
'ፈስ ፦ ግ. ለተ'ቻችን ነገር በማም መ'ጨነቅ [ተጨ'ነቀ]
fussy
'ፈሲ ፦ ቅ. በጣም ጠንቃ'ቃ (ለተ'ቻችን ነገር)
fusty
'ፈስቲ ፦ ቅ. መጥፎ ሽ'ታ ያ'ለው
futile
ፍ'ዩ:ታይል ፦ ቅ. እርባን የሌ'ለው ፣ ጥቅመ ቢስ
future
ፍ'ዩቸ ፦ ስ. ተምኔት ፣ የ'ሚመጣ ጊዜ ፣ የወ ደፊ'ቱ
fuzzy
'ፈዚ ፦ ቅ. በአ'ጭር ጠጉር የተሸ'ፈነ ፣ ጠጉረ ከርዳ'ዳ ፣ ግልጽ ያልሆነ

G

gabble
'ጋበል ፦ ግ. መለፍለፍ [ለፈ'ለፈ] ፣ መቀባ ጠር [ቀባ'ጠረ]
gadget
'ጋጀት ፦ ሰ. ት'ንሽ መ'ሣሪያ ወይን'ም የመ ሣሪያ መለ'ወጫ
gag
'ጋግ ፦ ግ. አፍ መ'ለጐም [አ'ጐመ] (እንዳ ይናገሩ)
gaiety
'ጌየቲ ፦ ሰ. በደ'ስታ መፈንደቅ

guily
ጊሊቲ ተጉ ብኽ.ስታ ፡ በ'ሚያስኽ'ስት ው ናቱ
gain
'ጌይን ጉ ማትረፍ [አተ'ረፈ]
ብ ትርፍ
gait
'ጌይት ብ ያረ'ግዱ ወናቱ ፡ ያ'ደርጉ መሥ'ቱ
galaxy
'ጋልክሲ ብ ዋንኛ'ነት የተስመ'ሰው ከሞክዘ ት ፡ የከዋክብት ከምችት
gale
'ጌይል ብ በጣም ጠንካ'ረ ነፋስ
gall
'ጎ:ል ጉ ማቁሰል [ሉቆ'ሰል] ፡ ማስቆ'ጣት [አስቆ'መ] ፡ ማ'ናደድ [አ'ና'ደደ]
bile
ብ ሐሞት
gallant
'ጎለንት ቅ ጎበዝ ፡ ጀግና ፡ ወኖ ፡ ያማረ (ልመ'ከተ)
gall-bladder
'ጎ:ል ብ'ላደ ብ የሐሞት ከረጢት
gallery
'ጋለሪ ብ በርቅ ላይ ያ'ል ሰገ'ነት
picture-
ብ የሥ'ዕል ማሳ'ያ አ'ዳራ'ቤ
galley
'ጋለ. ብ በመርከብ ውስተ ያ'ል ወተ ቤት
gallon
'ጋለን ብ ጋሎን (የፈሳሽ መል'ኪያ)
gallop
'ጋለፕ ጉ መጋለብ [ጋ'ለበ]
gallows
'ጋለውስ ብ ለሙ መስቀያ ፅንጨት
galore
ጋ'ኮ: ተጉ በመትረፍረፍ ፡ በብዛት
gamble
'ጋምበል ጉ ቁማር መ'ጫወት [ተጫ'ወተ]
gambler
'ጋምብለ ብ ቁማርተ'ኛ

gambol
'ጋምበል ጉ መዝናወት [ዘና'ጨ] ፡ ፀደ'ስታ መዝለል [ዘ'ለለ] ፡ መፃ'ረቅ [ፅ'ረቀ]
game
'ጌይም ብ ጨዋታ
gander
'ጋንደ ብ ወንድ ጳ'ክ'የ
gang
'ጋንግ ብ ወ'ርዝ'ል ፡ ወገ፬ደ,ዎች
gangster
'ጋንግስተ ብ ጎይል'ኛ ወንጀል መሪ (መ'ጎ ሪያ ኖያ)
gangway
'ጋንጉዌይ ብ መ'ዳ፬ መ'ተላለፊያ
gaol
'ጄይል ብ እ'ሥር ፬ት
gaoler
'ጄይለ ብ የመ'ሪ ፬ት ፡ ጠ'ባ ፡ የመ'ሪ ፬ት ጥ'ባ'ፊ
gap
'ጋፕ ብ ክፍት ቦታ (በፉ፬'ት ነገር'ች መ'ካ ያ'ል)
gape
'ጌይፕ ጉ አፍ ክፍቶ ማየት [አ'የ] (ፎ ያ'ነት)
garage
'ጋራ:ዥ ብ ጋራ'ዥ ፡ ተ'ሽከርካሪዎ'ች የ'ሚ ያርፉ'በት ቦታ
garb
'ጋ:ብ ብ የለብስ ስሊት ዓይነት ፡ ለብስ
garbage
'ጋ:ቢጅ ብ ው'ጭቂ ነገር ፡ ቁሻሻ ፡ ተ'ራጊ
garden
'ጋ:ደን ብ ያትክልት ቦታ ፡ ፀደ
gargle
'ጋ:ገል ጉ ጉር'ጉን ፡ አፍን ፀመዋ መ፡መዋ መዋ [ተ፡መ'መ]
garland
'ጋ:ልንድ ብ ያዝዛ ጌጥ
garlic
'ጋ:ሊክ ብ ነ'ጭ ሽን'ኩርት
garment
'ጋ:መንት ብ ለብስ

garnish
'ጋ:ኒሽ ጉ ማስዋ፫ [አስ'ጌ፬] ፡ ምግብ ውስጥ ቅመማ ቅመም መጨ'መር [ጨ'መረ] ፡ መክ 'ሸን [ከ'ሸን]
garrison
'ጋሪሰን ብ አንድ ከተማ ወይን'ም ም'ሽግ የ'ሚ'ፀፋ ወ'ታ'ደ'ሮች
garrulous
'ጋሪለስ ቅ ለየለሊ ፡ ስለተ'ንን ነገር መዘ ላደር የ'ሚ'ል'ድ
garter
'ጋ:ተ ብ የጉር ጅ'ሪ፬ መ'ወሪያ ላስቲክ (የለ'ች)
gas
'ጋስ ብ ጋዝ ፡ ኑ'-
gaseous
'ጌይሲየስ ቅ ጋዝ የ'ሚ'ሰል
gasoline
'ጋሰሊይን ብ ቤንዚን
gash
'ጋሽ ብ ጥልቀት ያ'ለው ቁስል ፡ የሰ'ነት ቁ፬ት
gasp
'ጋ:ስፐ ጉ መጸለይ መጸለይ መተንፈስ
gastric
'ጋስትሪክ ቅ የሆድ
gate
'ጌይት ብ ፅ'ር
gather
'ጋ፱ ጉ መሰብሰብ [ሰበ'ሰበ]
think
ጉ ማ'ሰብ [አ'ሰበ]
gauge
'ጌይጅ ጉ ፀተን'ቃቄ መ፡ክት [አ'ካ]
measure
ብ መ፡'ኪያ
gaunt
'ጎ:ንት ቅ ፀጣም ቀ'ጭን ፡ ከ'ሲ'ታ ፡ ማስ መ'ሎ
gauze
'ጎ:ዝ ብ የሕ'ክም'ና ጥጥ
gay
'ጌይ ቅ ደ'ስተ'ኛ ፡ የተደ'ሰተ

gaze
'ጌይዝ ጉ እተ'ከር መ'መልከት [ተመ ከተ]
gazelle
ገ'ዜል ብ ሪቆ
gear
'ጊየ ብ ማርች ፡ ፍጥነት መለ'ወጫ (የመ ኪና)
gearbox
'ጊየቦክስ ብ ካምቢዮ ፡ የፍጥነት መል'ወጫ መ'ተሪያ ያ'ል'በት ማዘን (በመኪና ዋቅር ውስጥ)
gem
'ጄም ብ ዕንቁ ፡ የተከ'በረ ያንጊያ (የተመለ መ'ና'ና የተቆ'ረመ) ፡ ከ'ፍ ያል ዋጋ ያ'ለው ዕፅ
gender
'ጄንደ ብ ጾታ
general
'ጄንረል ቅ ሐቅ'ላ
military
ብ ጀ'ኔራል (ያ'ጀዘማች ፡ ሊታወራሪ)
generally
'ጄንረል ተተ በጠቅ'ላላው
usually
ተተ ውል ጊዜ
generate
'ጄነሬይት ጉ ማመንጨት [አመ'ጫ] ፡ ኃሌመ ናር ወደ መ'ር ማምጣት [አመ'ጫ]
generation
ጄነ'ሬይሽን ብ ትውል'ድ
generosity
ጄነ'ሮሲቲ ብ አ'ገሥ'ና ፡ ችርቻ
generous
'ጄንረስ ቅ ለ'ጋሥ ፡ ችር
genesis
'ጄነሲስ ብ ፍጥረት ፡ አየት ፡ እረት ጀፍተ ረት
genial
'ጂይኒየል ቅ ፈገግተ'ኛ ፡ ርኅራኄ ፡ ገራገር ፡ ደ'ጋ'ግ ፡ ተፃፃፊ
genius
'ጂይኒየስ ብ የላቀ የአእምሮ ፡ የክሊ ግበብ ስመታ ፡ የተፈጥሮ ተውህ

ethiopicdictionary.com

gentle
ˈጂንተል -ቅ- ጨዋ ፣ የተከ'በረ ፣ ርኅሩኅ ፣ ተ ወ'ዳጅ

genuflect
ˈጂንፍሌክት -ግ- ለጸሎት መንበርከክ [ተን በረ'ከከ]

genuine
ˈጂንዩወን -ቅ- እውነተ'ኛ ፣ መ'ሳሳት የሌ'ለ 'በት ፣ የታ'መነ

geography
ጂ'ዮግረፊ -ስ- መልክዐ ምድር

geology
ጂ'ዮለጂ -ስ- ጂኦሎጂ (የመሬት ሁናቴ'ና ጠባይ ጥናት)

germ
ˈጀ:ም -ስ- ጀርም ፣ በ'ሽታ የ'ሚያመጡ ጥቃ 'ቅን ፍጥረቶ'ች

germicide
ˈጀ:ሚሳይድ -ስ- የተባይ መግደያ መድኃኒት

germinate
ˈጀ:ሚኔይት -ግ- ማቆንጉል [አቆነ'ጉለ] ፣ መብቀል [በ'ቀለ]

gesticulate
ጄስ'ቲከለይት -ግ- ሲ'ና'ጎሩ እ'ጅን ፣ አካ ልን ማ'ወዛወዝ [አ'ወዛ'ወዘ]

gesture
ˈጀስቸ -ስ- የሰው'ነት የእ'ጅ ንቅ'ናቄ (ሐ'ሳ ብ ለመግለጽ)

get
ˈጌት -ግ- ማምጣት [አመ'ጣ]
obtain
-ግ- ማግ'ኘት [አገ'ኘ]

geyser
ˈጊይዘ -ስ- ፍልውሃ (ከመሬት የ'ሚፈልቅ)

ghastly
ˈጋ:ስትሊ -ቅ- አስፈ'ሪ ፣ አስደንጋጭ

ghost
ˈገውስት -ስ- የሙ'ታን መንፈስ (ለሕያዋን የ'ሚ'ታ'ይ) ፣ መንፈስ

giant
ˈጃየንት -ስ- በጣም ረ'ጅም ፍጡር ፣ ከሰው ቁመት የላቀ ርዝመት ያ'ለው ሰው ፣ ወይን'ም ሌላ ት'ልቅ ፍጡር

giblet
ˈጂብለት -ስ- የዶሮ ወይን'ም የሌሎ'ች አዕ ዋፍ ሆድቃ (የ'ሚ'በ'ላው ክፍል)

giddy
ˈጊዲ -ቅ- ራሱን የ'ሚያዞረው ፣ የ'ሚያዋ ለ'ውለው ፣ ጎላፊ'ነት የ'ማይ'ሰማው

gift
ˈጊፍት -ስ- ስጦታ ፣ ሽ'ልማት

gifted
ˈጊፍተድ -ቅ- ተውህቦ ያ'ለው

gigantic
ጃይ'ጋንቲክ -ቅ- ጎ'ያል (ሰው ፣ ከመጠን በላይ የሆነ ፍጡር)

giggle
ˈጊገል -ግ- እ'የተሽከረ'መሙ መሣቅ [ሣቀ]

gill
ˈጊል -ስ- የዐሣ መተንፈሻ (ሳምባ)

gilt
ˈጊልት -ቅ- ወርቅ ቅብ

gimlet
ˈጊምለት -ስ- መሠርሠሪያ (መ'ሣሪያ)

gin
ˈጂን -ስ- ጅ'ን (መጠ'ጥ) ፣ የጥጥ መፈልቀ ቂያ መኪና

ginger
ˈጂንጀ -ስ- ዝንጅብ'ል

gipsy
ˈጂፕሲ -ስ- በዙሪት የ'ሚኖር አንድ ነገድ (በአውሮ'ጳ ውስጥ) ፤ ዘዋሪ ፣ ቤት የ'ለሽ ፣ ከርታ'ታ

giraffe
ጂ'ራፍ -ስ- ቀ'ጭኔ

girder
ˈገ:ደ -ስ- ጠንካ'ራ የብረት ፡ የእንጨት ዘንግ

girdle
ˈገ:ደል -ግ- መ'ታጠቅ [ታጠ'ተ] (በመ'ታጠ ቂያ)
-ስ- መ'ታጠቂያ

girl
ˈገ:ል -ስ- ልጃገረድ

girth
ˈገ:ፀ -ስ- መቀ'ነቻ (የሞንት ፣ የኮር'ቻ)

gist
ˈጂስት -ስ- ዋ'ና ሐ'ሳብ (የከር'ክር)

give
ˈጊቭ -ግ- መስጠት [ሰ'ጠ]

glacier
ግ'ላሲየ -ስ- የበረዶ ወንዝ

glad
ግ'ላድ -ቅ- ደ'ስታ

glade
ግ'ለይድ -ስ- በደ'ን መካ'ከል ያ'ል ገላጣ ቦታ

glamour
ግ'ላመ -ስ- የ'ሚማ'ርክ ቁንጅ'ና ፣ ደማም'ነት

glance
ግ'ላንስ -ግ- መልከ'ት ማድረግ

gland
ግ'ላንድ -ስ- እጢ

glare
ግ'ለየ -ግ- እፍ'ጮ መ'መልከት [ተመል'ከተ] (በቁ'ጣ)
strong light
-ስ- ኀይን የ'ሚያሞ'ቁር'ቁር (የ'ሚ ያሞቁረ'ቁር) ብርሃን

glass
ግ'ላ:ስ -ስ- ብርጭ'ቆ
material
-ስ- መስተዋት

gleam
ግ'ሊይም -ስ- ት'ንሽ የብርሃን ጭላንጭል ፣ የ'ሚያብለጨ'ልጭ ብርሃን (በተለ'ይ ብ'ል'ጭ ድር'ግ'ም የ'ሚል)

glean
ግ'ሊይን -ግ- መቃረም [ቃ'ረመ]

glee
ግ'ሊይ -ግ- ደ ስታ ፣ ፈንጠ'ዝያ

glen
ግ'ሌን -ስ- በተራራ መ'ከል ያ'ለ ጠ'ባብ ሸለቆ

glib
ግ'ሊብ -ቅ- ቋንቋው የ'ሚገራ'ለት (ነገር ግን የ'ሚለው የ'ማይ'ታ'መን)

glide
ግ'ላይድ -ግ- መንሸራተት [ተንሸራ'ተተ]

glimmer
ግ'ሊመ -ግ- ጭ'ል ጭ'ል ማለት [አለ]
-ስ- ጭላንጭ'ል

glimpse
ግ'ሊምስ -ግ- ማየት [አ'የ] (ነገር ግን የታ' የው ነገር ቶሎ ሊጠፋ)
-ስ- መ'አብታ

glisten
ግ'ሊሰን -ግ- ማንጸባረቅ [አንጸባ'ረቀ] (ለውሃ)

glitter
ግ'ሊተ -ግ- ማንጸባረቅ [አንጸባ'ረቀ] ፣ መን ቆጥቆጥ [ተንቆጠ'ቆጠ] (ለጌጣጌጥ)

gloat
ግ'ሎውት -ግ- በሰው ሥቃይ መ'ደሰት [ተደ 'ሰተ]

globe
ግ'ለውብ -ስ- ድቡልቡል የሆነ ነገር ፣ መሬትን ሉል (መልክዐ ምድር)

globular
ግ'ሎብዩለ -ቅ- ድቡልቡል

globule
ግ'ሎብዩ:ል -ስ- ጠ'ብታ (የውሃ ፣ የደም ወዘተ)

gloom
ግ'ሉ:ም -ስ- ጨለም'ም ማለት ፣ ደብዘ'ዝ ማለት
sadness
-ስ- ሐዘን ፣ እለመ'ደሰት ፣ መ'ከፋት

gloomy
ግ'ሉ:ሚ -ቅ- ደብዛ'ዛ ፣ ጨለ'ም ያለ
sad
-ቅ- ያልተደ'ሰተ ፣ ያዘነ ፣ የተከ'ፋ ፣ ቁጭ'ተ'ያለው

glory
ግ'ሎሪ -ስ- ክብር ፣ ስብሐት

glorious
ግ'ሎሪየስ -ቅ- ባለክብር ፣ ክቡር ፣ ሰመ ጥር

gloss
ግ'ሎስ -ስ- የ'ሚያበራ የ'ሚያንጸባ'ርቅ ነገር

glossy
ግ'ሎሲ -ቅ- የ'ሚያበራ ፣ የ'ሚያንጸባ'ርቅ

glove
ግ'ለቭ -ስ- የእ'ጅ ጅ'ራብ ፣ ጉዋንቲ

glow
ግ'ለው -ግ- መፋም [ፋመ]

glow-worm
ግ'ለው:ም -ስ- የ'ሚያበራ ትል ፣ ትል'ራ

gloss
ማዳፉ: ተ- መጣፊት ፣ ማ'ጣፊደያ መቅ ፣ ማ'ጽ ጊያ
glove
ማለም ቅ- ያ'ወነ ፣ የተሰ'ፋ
glut
ማይት ተ- የተትረፈ'ረፈ ነገር
glutton
ማይተን ተ- ሆላም ሰው ፣ ከመጠን ፀላይ የ'ሚይላ ሰው
gnash
'ናፀ ግ- ጥርስ መቆርጨም [ቆረ'ጨመ] ፣ ጥርስን ማ'ፋጨት [አ'ፋ'ጨ] (በቁ'ጣ)
gnat
'ናት ተ- ይቻቢ ፣ የወፃ ትን'ኝ
gnaw
'ና: ግ- መኮርኮም [ነ'ረ'ጾመ]
go
'ኑ ግ- መሄድ [ሄደ]
good
'ነውድ ጥ- መ•ልክ•ል [ከ•ለ'ከ•ል] (ለደረስ መጠ)
ተ- ከፀት መገኘ ል'ም'ጭ
goal
'ነውል ተ- ግብ ፣ ፅላማ
goat
'ነውት ተ- ፍ'የል
gobble
'ነፀል ግ- በሻ'ክላ መፀላት [በፅ] ፣ መጠ ብተ [ተበዝ'ገ] (ለምግብ)
go-between
'ነውፀትየይን ተ- አ'ታላሪ (ይት) ፣ እስታ ራቂ
goblet
'ነፀለት ተ- የጉጣ
god
'ነድ ተ- አምላክ
God
'ነድ ተ- እግዚአብሔር
godchild
'ነድ ቻይልድ ተ- የክርስት'ና ልጅ
goddess
'ነደስ ተ- እንስት አምላክ
godfather
'ነ:ድፋ'ዝ ተ- የክርስት'ና አ'ፃት
godmother
'ነድመ'ዝ ተ- የክርስት'ና እ'ናት
godsend
'ነድሰንድ ተ- ደንገተ'ኛ ፅ'ድል
goggles
'ነገለ'ዝ ተ- የጉፋይ ፣ የአይሪ መ'ነር (ፀተ ለ'ይ ፀለእሱት ነጂዎ'ች ያ'ሚያርጉት)
goitre
'ነይተ ተ- እንቅርት
gold
'ነውልድ ተ- ወርቅ
colour
ት- ቀሚ
goldsmith
'ነውልድስ'ሚ ተ- ወርቅ እንጣሪ ፣ ወርቅ መሪ
good
'ነድ ት- ጥሩ ፣ መልካም
good-bye
ጉድ'ባይ -ቃኩ- ደኅና ይውጉ (ውን)
goods
'ነድ፡ዝ ተ- ጀቱ፣ ጀቱተ
goodwill
ጉድ'ዊል ተ- ፀ'ን ፈቃድ
goose
'ነ:ስ ተ- ዝ'ፃ
gore
'ነ: ግ- መውጋት [መ'ጋ] (በቀንድ)
ተ- የ'ሚፈ'ስ ደም
gorge
'ነ:ጅ ግ- እ'የተቀንዘ'ገው መፀላት [ፀ'ላ]
ተ- ገፀፅ (በውሃ'ት ገደል መ'ከል ያ'ል)
gorgeous
'ነ:ጀስ ት- ውጣም የ'ሚያምር ፣ ፀቀለም ያዘ ዘ'ረፀ
gospel
'ነፅፐል ተ- ወንጌል
gossamer
'ነፅመ ተ- የጀሪሪቅ ድር

gossip
'ነሲፕ ግ- ያልተረጋ'ገጠ ወሬ ማ'ዋራት [አ ዋ'ራ]
ተ- ሐሜት ፣ ያልተረጋ'ገጠ ወሬ ፣ ጭም ጭምታ
gouge
'ጋውጅ ግ- መቦርቦር [በ፫'ቦ፫] ፣ መሰርሰር [ሰ፫'ሰ፫]
gourmand
'ጎ፡መንድ ቅ- ሆላም
govern
'ገዘን ግ- መግዛት [ገዛ] (በሥልጣን)
government
'ገዘንመንት ተ- ግዛት ፣ መንግሥት
governor
'ገዘነ ተ- ገዥ
gown
'ጋውን ተ- ረ'ጅም ቀሚስ
grab
ግ'ራብ ግ- አ፫'ፍ አድርጎ መያዝ [ያዘ] ፣ ጠ'ፍር መያዝ [ያዘ] ፣ መገጠት [ነ'ጠቀ]
grace
ግ'ሬይስ ተ- ረድኤት ፣ ውበት ፣ ያ'ረማመድ ግማር
prayer
ተ- ከማፅ'ድ በፊት'ና በኋላ የ'ሚ'ጸ'ለ ይ ጸሎት
graceful
ግ'ሬይስ'ፉል ቅ- ረድኤት ያ'ለው ፣ ሲ'ራ 'መድ የ'ሚያምር'በት ፣ ዝር'ጋ'ላ
gracious
ግ'ሬይሸስ ቅ- ቸር ፣ ለ'ጋሥ
grade
ግ'ሬይድ ተ- ማዕረግ ፣ ደረጃ
gradient
ግ'ሬይዲ'ኮ ተ- ቁልቁለት'ኑት ያ'ለው ቦታ
gradual
ግ'ራጁ'ል ቅ- ዝ'ግተ'ኛ ፣ ቀ'ስ በቀ'ስ የ'ሚ 'ደረግ
graduate
ግ'ራጁ'ዌይት ግ- መ'መረቅ [ተመ'ረቀ] (በት ምህርት)
graft
ግ'ራፍት ግ- መከተብ [ከ'ተበ] (ለእትከሌት)
grain
ግ'ሬይን ተ- እህል ፣ ጥራጥሬ ፣ ትን'ሣት
grammar
ግ'ራመ ተ- ሰዋስው
granary
ግ'ራነሪ ተ- የእህል ጎተራ
grand
ግ'ራንድ ቅ- ት'ልቅ ፣ አስደ'ናቂ
grandeur
ግ'ራንድ'ዩ ተ- ት'ልቅ'ነት ፣ ገናና'ነት
grandfather
ግ'ራንድፋ:ዝ ተ- ወንድ አያት
grandmother
ግ'ራንድመ'ዝ ተ- ሴት አያት
grange
ግ'ሬይንጅ ተ- በትናንን'ሽ ቤቶ'ች የተከ'በበ የባለቤቱ መኖሪያ (በባላገር) ፣ የእህል ጎተራ
granite
ግ'ራኒት ተ- ጥቁር ደንጊያ
grape
ግ'ሬይፐ ተ- ወይን
grant
ግ'ራ:ንት ግ- መስጠት [ሰ'ጠ] (የ'ጠ'የቁትን)
graphic
ግ'ራፊክ ቅ- አ'ንሳለጹ ሕያው የሆነ ፣ በ'ሚ 'ታዩ ም'ክ'ች የተ'ሰለ ፣ የጽሑፍ ፣ የሥ ዕል ወዘተ
grapple
ግ'ራፕል ግ- ጨ'ብጠ መያዝ [ያዘ] ፣ ለቀ'ም ግድረግ [እደ'ረገ] ፣ መ'ታገል [ታገለ]
grasp
ግ'ራስፕ ግ- መያዝ [ያዘ] ፣ መጨ'በተ [ጨ 'በጠ]
understand
ግ- መ'ረዳት [ተረ'ዳ]
grasping
ግ'ራስፒ'ንግ ቅ- ሥ'ሥታም (የነንዘብ) ፣ ለሥ ልጣን ፣ ለገንዘብ ትርፍ የ'ሚጸ'ጓ
grass
ግ'ራ:ስ ተ- ሣር
grasshopper
ግ'ራ:ሰሆፐ ተ- ፈንጣ

grate
ግሬይት ግ· መፋቅ [ፋቀ] (ምሳሌ፦ርግጃ) -ስ· እሳት የ'ሚነ'ድበት ፍርግርግ ብረት
grateful
ግሬይትፉል ቅ· ባለውለታ
grater
ግሬይተ ·ስ· መፋቂያ ፡ መፈርፈሪያ (መ'ሣሪያ)
gratify
ግሬቲፋይ ግ· የፈ'ለጉትን መስጠት [ሰ'ጠ] ማስደ'ሰት [አስደ'ሰተ]
gratitude
ግሬቲትዩ፡ድ ·ስ· ምስጋና (ለተደ'ረገ'ለት ውለታ የ'ሚ'ደ'ረግ)
gratuity
ግ'ራትዩዊቲ ·ስ· ጉርሻ ፡ ስጦታ ፡ ያገልግሎት ገንዘብ (ለመ'ታ'ደር'ኞ ያገልግሎታ'ቸው ጊዜ ሲ'ፈ'ጽም የ'ሚ'ሰ'ጥ)
grave
ግ'ሬይቭ ·ስ· መቃብር
serious
-ቅ· ከ'ባድ ፡ አ'ዋኪ
gravedigger
ግ'ሬይቭዲገ' ·ስ· መቃብር ቆ'ፋሪ
gravel
ግ'ራቭል ·ስ· ጠጠር
gravestone
ግ'ሬይቭስተውን ·ስ· የመቃብር ደንጊያ (ጽሑፍ የ'ሚ'ጻፍ'በት)
graveyard
ግ'ሬይቭያ፡ድ ·ስ· የመቃብር ቦታ
gravity
ግ'ራቪቲ ·ስ· የመሳብ ጎ'ይል ፤ አስቸ'ጋሪ'ነት
gravy
ግ'ሬይቪ ·ስ· ቅባት (የተጠ'በሰ ሥጋ)
gray
ግ'ሬይ ·ቅ· ግራ'ጫ ፡ አመድ'ማ
graze
ግ'ሬይዝ ግ· መጋጥ [ጋጠ] (ለእንሰሳት)
wound
-ስ· ጭረት (ለቁስል)
grease
ግ'ሪይስ ·ስ· የቀ'ለጠ ሞራ ፡ ቅባት
greasy
ግ'ሪይሲ ·ቅ· ቅባታም ፡ አጻላጭ
great
ግ'ሬይት ·ቅ· ት'ልቅ ፡ ታ'ላቅ
greatcoat
ግ'ሬይትኮውት ·ስ· ካ'ፖርት (ከበ'ድ ያለ)
greatly
ግ'ሬይትሊ ·ተግ· በጣም ፡ በብልጫ
greatness
ግ'ሬይትነስ ·ስ· ት'ልቅ'ነት
greed
ግ'ሪይድ ·ስ· ሥ'ሥት (ለምግብ ፡ ለገንዘብ)
greedy
ግ'ሪይዲ ·ቅ· ቅ'ትታም ፡ ሥ'ሥታም (ለምግብ ፡ ለገንዘብ ወዘተ)
green
ግ'ሪይን ·ቅ· አረንጓዴ ፡ ገና ያልበ'ሰለ ፡ ሮቤታ (ለእትክልት)
greet
ግ'ሪይት ግ· ሰላምታ መስጠት [ሰ'ጠ]
greeting
ግ'ሪይቲንግ ·ስ· ሰላምታ
grenade
ግሪ'ኔይድ ·ስ· የእ'ጅ ቦምብ
grey
ግ'ሬይ ·ቅ· ግራ'ጫ ፡ አመድ'ማ
grid
ግ'ሪድ ·ስ· የወንፊት መልክ ያ'ለው የብረት መ'ሣሪያ
grief
ግ'ሪይፍ ·ስ· ሐዘን
grievance
ግ'ሪይቨንስ ·ስ· የአቤቱታ ምክንያት ፡ አቤ'ቱታ
grieve
ግ'ሪይቭ ግ· ማዘን [አ'ዘነ]
grievous
ግ'ሪይቩስ ·ቅ· አሳ'ዛኝ ፡ ከ'ባድ
grill
ግ'ሪል ·ስ· ጥብስ ሥጋ ፡ መጥበሻ ፡ የወንፊት መልክ ያ'ለው የብረት መ'ሣሪያ (ለሥጋ መጥበሻ)
grim
ግ'ሪም ·ቅ· የጨ'ለማው ፡ ጥላ'ቻ ያ'ደረ'በት

grimace
ግ'ሪመስ ·ግ· ፊትን በጥላ'ቻ ማ'ኮፋተር [አ'ኮ ፋ'ተረ] ፡ መ'ከሳተር [ተከሳ'ተረ]
grime
ግ'ራይም ·ስ· እንቭቅ ፡ እድፍ
grin
ግ'ሪን ·ግ· ፈገ'ግ ማለት [አለ]
grind
ግ'ራይንድ ·ግ· መፍጨት [ፈ'ጨ]
grindstone
ግ'ራይንድስተውን ·ስ· የወፍጮ ደንጊያ
grip
ግ'ሪፕ ·ግ· መጨ'በተ [ጨ'በጠ] ፡ መያዝ [ያዘ]
gripe
ግ'ራይፕ ·ስ· የሆድ ቁርጠት
gristle
ግ'ሪስል ·ስ· አንጀ ት)
grit
ግ'ሪት ·ስ· የደ'ቀቀ ጠጠር
groan
ግ'ሮውን ·ግ· መጓጐር [ጓ'ጐረ] ፡ ማቃሰት [አቃ'ሰተ]
grocer
ግ'ሮውሰ ·ስ· የምግብ ሽቀጥ ነ'ጋዴ
grocery
ግ'ሮውሰሪ ·ስ· የምግብ ሽቀጥ ሱቅ
groggy
ግ'ሮጊ ·ቅ· ተንገዳጋጅ ፡ ተንገዳጋጅ ፡ ለመ ውደቅ የደ'ረሰ
groin
ግ'ሮይን ·ስ· ሙላ
groom
ግ'ሩ፡ም ·ግ· መዋረግ [ዘ'ረገ] (ፈረስን)
servant
-ስ· ፈረስ አጣቢ
well-ed
ልብሱ ያማረ'በትና ጠጉሩ'ም በደምብ የተ ዘ'መረ
groove
ግ'ሩ፡ቭ ·ስ· በንጥት

grope
ግ'ሮውፕ ·ስ· መላበስ [ላ'በሰ] (እንደ ዕ'ውር ወዘተ)
-ቅ· ደፈደፍ ፡ ወፍራም
gross
ግ'ሮውስ ·ቅ· ባለጌ ፡ ያልታ'ረመ ፡ ደ'ደብ
number
-ስ· ዐሥራ ሁ'ለት ደርዘን
ground
ግ'ራውንድ ·ስ· መሬት
groundless
ግ'ራውንድለስ ·ቅ· መሠረተ ቢስ ፡ በቂ ምክ ንያት የሌ'ለው
group
'ግሩ፡ፕ ·ስ· የተሰበ'ሰበ (ሰው)
grouse
ግ'ራውስ ·ግ· ማጉረምረም [አጉረመ'ረመ]
grove
ግ'ሮውቭ ·ስ· እነስተ'ኛ ደ'ን
grovel
ግ'ሮቨል ·ግ· ራስን ዝ'ቅ ማድረግ [አደ'ረገ] (በትሕት'ና)
grow
ግ'ሮው ·ግ· ማደግ [አ'ደገ]
make-
-ግ· መትከል[ተ'ከለ] ፡ መዝራት [ዘ'ራ]
growl
ግ'ራውል ·ግ· መጓጐር [ጓ'ጐረ] ፡ መጮኽ [ጮኸ]
growth
ግ'ሮውዟ ·ስ· እድገት
grub
ግ'ረብ ·ስ· ትል (መጻያው የተፈለ'ፈለ)
food
-ስ· ምግብ (ተራ ቃል)
grubby
ግ'ረቢ ·ቅ· ያልጸ'ዳ ፡ ያ'ደፈ
grudge
ግ'ረጅ ·ግ· መ'ቅኘት [ተመቀ'ኘ] ፡ መን ፈግ [ን'ፈገ]
gruel
ግ'ሩ፡ወል ·ስ· ሙቅ ፡ እጥሚት

gruesome
ግሩ፡ሰም ቅ- አስቀ'ያሚ ፣ ለማየት የ'ሚያ
'ሠቅት
gruff
ግ'ሪፍ -ስ- ሸካራ'ነት ፣ ንጭና'ሜ'ነት ፣ እሙ
ለቢስ'ነት
grumble
ግ'ረምበል -ግ- ማጉረምረም [አጉረመ'ረመ]
grunt
ግ'ረንት -ስ- ማኩረፍ (በተለ'ይ ለወጣፃ ድ
ምፅ)
guarantee
ጋረን'ቲ፡ -ግ- ተያዥ መሆን [ሆነ] ፣ ዋስ መሆን
[ሆነ]
-ስ- ዋስት'ና ፣ ተያዥ'ነት
guarantor
'ጋረንቶ፡ -ስ- ዋስ ፣ ተያዥ ፣ ዋቢ
guard
'ጋ፡ድ -ግ- መጠ'በቅ [መ'በቀ] (እንጻያመልጥ)
-ስ- ጠ'ባቂ ፣ ዘበ'ኛ
guardian
'ጋ፡ድየን -ስ- አሳ'ዳጊ ፣ ጎላፊ (ለሕፃን)
guerilla
ገ'ሬለ -ስ- የደፈጣ ጦር'ነት ፣ በደፈጣ የ'ሚ'ዋ
'ጉ ሰዎ'ች
guess
'ገስ -ግ- ግ'ሰብ [እ'ሰበ] (በግ'ምት) ፣ መገ
ምገም [ገመ'ገመ]
-ስ- የግ'ምት ሐ'ሳብ
guest
'ገስት -ስ- እንግዳ (ሰው)
guidance
'ጋይደንስ -ስ- እ'መራር ፣ የመምራት ሥራ
guide
'ጋይድ -ግ- መምራት [መ'ራ]
person
-ስ- መሪ
guile
'ጋይል -ስ- ሙ'ሉ'ነት ፣ እ'ታላይ'ነት
guilt
'ጊልት -ስ- ጥፋት ፣ ሕ'ግን የመጣስ ውናቴ ፣
ሰ'ሜት
guinea fowl
'ጊኒፋውል -ስ- ጅግራ

guinea-pig
'ጊኒ'ፒግ -ስ- መድኃኒት ወዘተ መረ'ትኖ (ሰ
ውንእንስሳ ወዘተ)
guise
'ጋይዝ -ስ- ያልሆኑትን መስሎ መ'ታየት ፣
የልብስ ጎይነት ቅ'ድ ፣ ሞድ
gulf
'ገልፍ -ስ- የዓልፍ ሠ'ላጤ
gullet
'ጎለት -ስ- የምግብ መ'ተላለፊያ ቧንቧ (ከጉ
ሮ'ሮ እስከ ሆድ ያ'ለው)
gullible
'ጎለበል -ቅ- የ'ዋህ ፣ በቀ'ላሉ የ'ሚ'ሞ'ኝ
gulp
'ጎልፕ -ግ- መ'ጉንጨት [ተጉ'ጨ]
-ስ- ጉንጭ ሙሉ
gum
'ጎም -ስ- ድ'ድ
adhesive
-ስ- መጣበቅ ፣ ግ'ጣበቂያ ፣ ግ'ዠኒያ
of a tree
-ስ- ሙ'ጫ
gumboil
'ጎምቦይል -ስ- የድ'ድ እብጠት
gun
'ጎን -ስ- ጠበንጃ (መ'ሣጃ)
gunner
'ጎነ -ቅ- መድፈ'ኛ
gunpowder
'ጎንፓውደ -ስ- ባሩድ
gunsmith
'ጎንስሚዺ -ስ- ጠበንጃ ሠሪ
gurgle
'ጎ፡ንል -ስ- የውሃ ድምፅ (መ'ባባ እፍ ከ'ለው
ጠርሙዝ ሲ'ቅ'ዳ) ፣ መንደቅደቅ
gush
'ጎሽ -ግ- በብዛት መፍሰስ [ፈ'ሰሰ] ፣ መጉረፍ
[ጎ'ረፈ]
gust
'ጎስት -ስ- የነፋስ ኀ'ውታ
gut
'ጎት -ስ- እንጀት
cat-
-ስ- የከ'ረረ ጀ'ማት!ጀማን'ነት።ጉብዝ'ና

gutter
'ጎተ -ስ- የወፃ መ'ተላለፊያ (በመንገድ ዳር) ፣
የወፃ መውረጃ ቧን'ቧ (ከግራ ላይ)
guttural
'ጎተረል -ቅ- የጉሮ'ሮ (ፊደል ወዘተ) ፣ የጎብ
ጉርጎ
guy
'ጋይ -ስ- ሰው

guzzle
'ገዘል -ግ- መ'ጠም [ገ'ጠመ] (ለመጠ'ጥ)
gymnastics
ጂም'ናስቲክስ -ስ- የሰው'ነት ማጠንከሪያ እን
ቅስ'ቃሴ ፣ ጂምናስቲክ

H

habit
'ሀቢት -ስ- ልማድ
dress
-ስ- የመነኮሳት ል'ዩ ል'ዩ ልብስ
habitable
'ሀቢተብል -ቅ- በውስጡ ሊኖሩ'በት የ'ሚ
ቻል
habitation
ሀቢ'ቴይሽን -ስ- መኖሪያ ቤት
habitual
ሀ'ቢቹውል -ቅ- የተል'መደ!በልማድ የተሠ'ራ
hack
'ሀክ -ግ- መቆራረጥ [ቆራ'ረጠ] ፣ መተፍ
ተፍ [ተፈ'ተፈ]
horse
-ስ- ያረ'ጀ ፈረስ ፣ ጌ'ኛ፣ የ'ሚ'ከራ'ይ
ፈረስ
hackneyed
'ሀክኒይድ -ቅ- የተል'መደ ፣ ተራ (ለንግ'ግር ፣
ለጽሑፍ)
haemorrhage
'ሄመሪጅ -ስ- የደም ሥር መ'በጠስ'ና የደም
በሰው'ነት መፍሰስ
haft
'ሀ፡ፍት -ስ- እ'ጀታ (የቢ'ለዋ ወዘተ)
haggard
'ሀጎድ -ቅ- የጠመ'ሰ ፣ የደ'ከመው (ለሰው)
hail
'ሄይል -ግ- መ'ጣራት [ተጣ'ራ] (ሰው ሰላ
ምታ ለመስጠት)
-ስ- በረዶ (የሠናብ)

hailstone
'ሄይልስተውን -ስ- በረዶ (እንጂ ጠጠር)
hair
'ሄየ -ስ- ጠጉር
hairdresser
'ሄድረሰ -ስ- ጠጉር እስተካካይ ፣ ጠጉር ቆራጭ
hairy
'ሄሪ -ቅ- ጠጉራም
hale
'ሄይል -ቅ- ጤና'ማ
half
'ሀ፡ፍ -ስ- ግ'ማሽ ፣ እ'ኩል
hall
'ሆ፡ል -ስ- አ'ዳራሽ
hallmark
'ሆ፡ልማክ -ስ- የወርቅ'ነት'ና የብር'ነት ማ
'ረጋገጫ ምል'ክት (እንጣሪው የ'ሚጽፈው
ጽሑፍ)
hallo
ሆ'ለው -ቃአ- እንዴት ነዎት (ነህ)
halo
'ሄለው -ስ- በራስ ዙሪያ የ'ሚ'ታ'ይየት'ዴላን
ምል'ክት
halt
'ሆልት -ግ- መቆም [ቆመ] ፣ ማቆም [አቆመ]
halve
'ሀ፡ቭ -ግ- ለሁለ'ት መቆረጥ [ቆረጠ] ፣ ለሁ
ለ'ት መገምል [ገ'መለ]
-ቅ- ለሁለ'ት የተከ'ፈለ ፣ የተገ'መለ

ham
ʾሀም -ስ- በጢስ የደ'ረቀ'ና ጨው ያ'ለ'በት ያጣማ ወርች ሥጋ
hamlet
ʾሀምለት -ስ- ት'ንሽ መንደር
hammer
ʾሀመ -ስ- መዶሻ
hammock
ʾሀመክ -ስ- በዛፍ'ና በዛፍ መካ'ከል የ'ሚን ጠለ'ጠል የ'ሚ'ተ'ኛ'በት ጨርቅ (እንደ አልጋ)
hamper
ʾሀም፫ -ስ- ት'ልቅ ቅርጫት
handicap
-ግ- መሣታት [ን'ታ] ፣ እንዳይንቀሳ'ቀስ ማድረግ [አደ'ረገ]
hand
ʾሀንድ -ስ- እ'ጅ
handbill
ʾሀንድቢል -ስ- ለሕዝብ የ'ሚ'በ'ተን የንግድ ማስታወቂያ ወረቀት
handbook
ʾሀንድቡክ -ስ- መምሪያ መጽሐፍ
handcuff
ʾሀንድኩፍ -ስ- የእ'ጅ እግር ብረት
handicap
ʾሀንዲካፕ -ስ- እንቅፋት ፣ መሰናክል
handicraft
ʾሀንዲክራፍት -ስ- የእ'ጅ ሥራ
handkerchief
ʾሀንከቺፍ -ስ- መሐ'ረብ
handle
ʾሀንደል -ግ- መያዝ [ያዘ] ፣ መ'ቆጣጠር መቻል [ቻለ]
-ስ- ማንጠልጠያ ፣ ጆሮ (የዕቃ)
handsome
ʾሀንሰም -ቅ- ያማረ ፣ የተዋበ (ለወንድ)
handwriting
ʾሀንድራይቲንግ -ስ- የእ'ጅ ጽሕፈት
handy
ʾሀንዲ -ቅ- ተስማሚ ፣ ቅልጥ'ፍ ያለ (ለዕቃ)
hang
ʾሀንግ -ግ- መስቀል [ሰ'ቀለ] ፣ ማንጠልጠል [እንጠለ'ጠለ]
hangar
ʾሀንገ -ስ- ያውሮ'ፕላን ጋራ'ዥ
hanger
ʾሀንገ -ስ- የልብስ መስቀያ
hangman
ʾሀንግመን -ስ- ሰቃይ (የተፈ'ረደ'በትን ሰው)
hank
ʾሀንክ -ስ- ጥ'ቅል ገመድ ፣ ጥ'ቅል ሱፍ ፣ ድር
hanker
ʾሀንክ -ግ- መ'መኘት [ተመ'ኘ]
haphazard
ሆፕ'ሃዘድ -ቅ- በድንገት የሆነ፡ሳያ'ስ'ቡት የተ ደ'ረገ
happen
ʾሀፐን -ግ- መሆን [ሆነ]
happiness
ʾሀፒነስ -ስ- ደ'ስታ ፣ ፍ'ሥሐ
happy
ʾሀፒ -ቅ- ደ'ስተ'ኛ ፣ ተደ'ሳች
harlot
ʾሀ፡ለት -ስ- ሴተ'ኛ አዳሪ
harrass
ʾሀረስ -ግ- በ'የጊዜው ማስፈራራት [አስፈ ራ'ራ] ፣ መንከነክ [ነከ'ነከ] ፣ ማልፋት [አል'ፋ]
harbour
ʾሀ፡በ -ስ- ወደብ (የመርከብ ማቆሚያ)
hard
ʾሀ፡ድ -ቅ- ጠንካ'ራ
harden
ʾሀ፡ደን -ግ- ማጠንከር [አጠ'ከረ]
hardly
ʾሀ፡ድሊ -ተግ- በችግር ፣ በመ'ቸገር
hardship
ʾሀ፡ድሺፕ -ስ- መከራ ፣ ችግር
hardware
ʾሀ፡ድዌየ -ስ- የውጥ ቤት ቁሳቁስ (ብረታብረት)
hardy
ʾሀ፡ዲ -ቅ- መከራ ቻይ ፣ ጀግና
hare
ʾሄየ -ስ- ዋንቾል (የሜዳ)
harelip
ʾሄየሊፕ -ስ- የተከ'ፈለ የላይ'ኛው ከንፈር

hark
ʾሀክ -ስ- ማ'ዳመጥ [አ'ዳ'መጠ]
harm
ʾሀ፡ም -ግ- መጉዳት [ን'ዳ]
harmonious
ሀ፡መውኒየስ -ቅ- ሲሰሙት የ'ሚያስደ'ስት ፣ ጣዕመ ዜማ ያ'ለው ፣ ስምም'ነት ያ'ለው
harness
ʾሀ፡ነስ -ስ- የፈረስ ዕቃ
harp
ʾሀ፡፫ -ስ- በገና
harrow
ʾሀረው -ስ- አፈር መከስከሻ መ'ሣሪያ (የእ ርሻ)
harsh
ሀ፡ሽ ʾ-ቅ- ሻካራ ፣ ያልተስማ'ማ ፣ ጎይል'ኛ (ለጠባይ)
sound
-ቅ- ሻካራ ድምፅ ፣ ጨ'ካኝ
harvest
ʾሀ፡ቨስት -ግ- ማምረት [አመ'ረተ] ፣ ሰብል መሰብሰብ [ሰበ'ሰበ[
-ስ- ምርት
hasp
ʾሀ፡ስፕ -ስ- ማሠሪያ (ለበ'ር ፣ ለሻንጣ ፣ ለማ ጥን ወዘተ)
haste
ʾሄይስት -ስ- ፍጥነት ፣ ች'ኩል'ነት ፣
-ግ- ማ'ጣደፍ [አ'ጣ'ደፈ] ፣ መቸ'ኩል [ቸ'ኩለ]
hat
ʾሀት -ስ- ባርኔጣ
hatch
ʾሀች -ስ- የመርከብ ክዳን (የዕቃ መጫ'ኛውን ክፍል የ'ሚከድነው)
-ግ- መፈልፈል [ፈል'ፈለ] ፣ መ'ፈል 'ፈል [ተፈለ'ፈለ] (የዕንቁላል)
hatchet
ʾሀቸት -ስ- ጥ'ልቆ ፣ ት'ንሽ መጥረቢያ
hate
ʾሄይት -ግ- መጥላት [ጠ'ላ]
haughty
ʾሆ፡ቲ -ስ- ከሩ ፣ ሰው ናቂ ፣ ደ'ፋር (በን ግ'ግር)
haul
ʾሆ፡ል -ግ- መሳ'ተት [ን'ተተ]
haunch
ʾሆ፡ንች -ስ- ዳ'ሌ
haunt
ʾሆ፡ንት -ግ- በርኩስ መንፈስ መ'ባረር [ተባ 'ረረ]
-ስ- ሁልጊዜ የ'ሚሄዱ'በት ቦታ ፣ ቤት
have
ʾሀቭ -ግ- መ'ዛናዘብ [ተዛና'ዘበ] ፣ መኖር [አ'ለ]
haven
ʾሄይቨን -ስ- የረ'ጋ ወደብ ፣ መ'ጠጊያ ቦታ
havoc
ʾሀቮክ -ስ- ብተ'ብተ ፣ ሽ'ብር
hawk
ʾሆ፡ክ -ስ- ጭል'ፊ'ት
-ግ- ከቦታ ቦታ እ'የተዘዋ'ወሩ ዕቃ መ'ነገድ [ን'ገደ]
hay
ʾሄይ -ስ- ድርቆሽ
haystack
ʾሄይስታክ -ስ- የድርቆሽ ክ'ምር
hazard
ʾሀዘድ -ስ- አደ'ጋ ፣ ዕ'ድል
hazardous
ʾሀዘዱስ -ቅ- አደ'ገኛ
haze
ʾሄይዝ -ስ- ብርሃን የ'ሚሸ'ፍን ቀለ'ል ያለ ደ'መና ፣ ጭጋግ
he
ʾሂይ -ተስ- እርሱ ፣ እርሳ'ቸው ፣ እ'ሱ ፣ እ'ሳ ቸው
head
ʾሄድ -ስ- ራስ
chief
-ስ- አለቃ ፣ ሹም
headache
ʾሄዲይክ -ስ- ራስ ምታት
headland
ʾሄድላንድ -ስ- ወደ ባሕር ውስጥ ገባ ያለ ገደል

headlight
ˈሄድላይት -ስ- የመኪና የፊት መብራት ፣ በመርከብ እናት ላይ ያለ መብራት
headmaster
ሄድ'ማ፡ስተ -ስ- የትምህርት ቤት ዲሬክተር
headquarters
ሄድክ'ዎ፡ተዝ -ስ- ጠቅላይ መምሪያ (የወ'ታ'ደር) ፣ ያንድ ድር'ጅት ጠቅላይ መሥሪያ ቤት
headstrong
ˈሄድስትሮንግ -ቅ- በፍ'ላጐቱ የ'ሚ'መ'ራ ፣ ችኮ ፣ መንጆ'ካ
headway
ˈሄድዌይ -ስ- ወደፊት የመሄድ እንቅስ'ቃሴ (በተለ'ይ የመርከብ)
heal
ˈሂይል -ግ- መፈ'ወስ [ፈ'ወሰ] ፣ ማዳን [አዳነ]
health
ˈሄልፀ -ስ- ጤና
healthy
ˈሄልፒ -ቅ- ጤና'ማ
heap
ˈሂይፕ -ግ- መቆ'ለል [ቆ'ለለ]
-ስ- ቁ'ልል
hear
ˈሂየ -ግ- መስማት [ሰ'ማ]
hearsay
ˈሂየሰይ -ስ- ወሬ (አፈ ታሪክ)
hearse
ˈሸ፡ስ -ስ- የሬሳ መኪና
heart
ˈሀ፡ት -ስ- ል'ብ
good-ed
-ቅ- ርኅሩኅ
heartbeat
ˈሀ፡ትቢይት -ስ- የልብ ት'ርታ
heartburn
ˈሀ፡ትበ፡ን -ስ- ቃር
hearten
ˈሀ፡ተን -ግ- ማጽናናት [አጽና'ና] ፣ ግ'በረ ታታት [አ'በረታ'ታ] ፣ ግ'ደፋፈር [አ'ደፋ'ፈረ]
hearth
ˈሀ፡ፕ -ስ- ምድ'ጃ
heartily
ˈሀ፡ተሊ -ተ- ከል'ብ
heartless
ˈሀ፡ትለስ -ቅ- ጨ'ካኝ ፣ የርኅራኄ ስ'ሜት የሌ'ለው
heat
ˈሂይት -ግ- ማሞቅ [አሞቀ]
-ስ- ሙቀት
heath
ˈሂይፕ -ስ- የክብቶ ግ'ሠማሪያ ቦታ (የማ'ንም ያልሆነ)
heathen
ˈሂይዝን -ቅ- አረመኔ
heave
ˈሂይቭ -ግ- መጎተት [ጎ'ተተ] ፣ ማንሣት [አ ነ'ሣ] ፣ መጣፋት [ጎ'ፋ]
heaven
ˈሄቨን -ስ- ሰማይ
religious
-ስ- መንግሥተ ሰማያት
heavy
ˈሄቪ -ቅ- ከ'ባድ
hectic
ˈሄክቲክ -ቅ- ሥራ የ'ማያስፈ'ታ ፣ ፋታ የ'ማ ይሰጥ ፣ የተፋ'ጠነ
hedge
ˈሄጅ -ስ- በድንበር ዙሪያ የ'ሚ'ገኝ ተክል
heed
ˈሂይድ -ግ- ማስተዋል [አስተዋለ]
-ስ- ጥን'ቃቄ ፣ ማስተዋል
heel
ˈሄይል -ስ- ተረከዝ
hefty
ˈሄፍቲ -ቅ- ወፍራም ፣ ከ'ባድ'ና ጎይለ'ኛ
heifer
ˈሄፈ -ስ- ጊደር
height
ˈሀይት -ቅ- እርዝማኔ
heighten
ˈሀይተን -ግ- የበ'ለጠ ማድረግ [አደ'ረገ] ፣ ከ'ፍ ማድረግ [አደ'ረገ]
heir
ˈኤየ -ስ- ወራሽ (ወንድ)
heiress
ˈኤየረስ -ስ- ወራሽ (ሴት)

hell
ˈሄል -ስ- ሲኦል
helm
ˈሄልም -ስ- የመርከብ መሪ (መ'ሣሪያ) ፣ ተሩር
help
ˈሄልፕ -ግ- መርዳት [ረ'ዳ]
helpful
ˈሄልፕፉል -ቅ- ረጂ ፣ ለመርዳት የተዘጋ'ጀ
helpless
ˈሄልፕለስ -ቅ- ደካማ ፣ ረ'ዳት የሌ'ለው
hem
ˈሄም -ስ- የልብስ ጠርዙ ፣ የልብስ ጠርዝ (በተ ለ'ይ ታጥፎ የተሰ'ፋ)
hemisphere
ˈሄመስፊየ -ስ- የዓለም አ'ጋማሽ
hemp
ˈሄምፕ -ስ- አእምሮ የ'ሚያደነ'ዝዝ መድኃ ኒት የ'ሚወጣ'በት ተክል ፣ ቃ'ጫ የ'ሚወ ጣ'በት ተክል
hen
ˈሄን -ስ- ዶሮ
hence
ˈሄንስ -ተግ- ስለ'ዚህ ፣ ከ'ዚህ የተነ'ሣ
her
ˈሸ፡ -ተስ- እርሷ ፣ የርሷ
herald
ˈሄረልድ -ስ- የንጉሥ መልእክተ'ኛ ፣ ወሞጅ ነጋሪ
herb
ˈሸ፡ብ -ስ- የሚ'በ'ሳ ቅጠላቅጠል ፣ የምግብ ማጣፈጫ ተክል
herd
ˈሸ፡ድ -ስ- መንጋ
herdsman
ˈሸ፡ድዝመን -ስ- ከብት አ'ጋጅ ፣ ከብት ጠ'ባቂ
here
ˈሂየ -ተግ- እ'ዚህ
hereafter
ሂየ'ራፍተ -ተግ- ከ'ዚህ በላይ ፡ ከአንግዲህ ወዲህ ፡ ወደፊት
hereby
ሂየ'ባይ -ተግ- በ'ዚህ
hereditary
ሸ'ሬደትሪ -ቅ- የተወ'ረሰ (ጠባይ ወዘተ)
heresy
ˈሄረሲ -ስ- ጥር'ማሬ (የሃይማኖት) ፣ ሐሬተ ፆ'ነት
herewith
ሂየ'ዊዝ -ተግ- ከ'ዚህ ጋር
heritage
ˈሄረተጅ -ስ- ከ'ባቶ'ች የተወ'ረሰ ነገር
hermit
ˈሸ፡ሚት -ስ- ባሕታዊ
hermaphrodite
ሸ'ማፍሮደላይት -ስ- ፍናፍንት
hernia
ˈሸ፡ኒያ -ስ- እበተ (የሆድ)
hero
ˈሂረው -ቅ- ጀግና (ለወንድ)
heroine
ˈሄሪዊን -ቅ- ጀግና (ለሴት)
heroism
ˈሄሪዊዝም -ስ- ጀግን'ነት
herself
ሸ'ልፍ -ተስ- እርሷ እራ፟ሷ ፡ እ'ሷ ራ፟ሷ
hesitate
ˈሄዝቴይት -ግ- መ'ጠራጠር [ተጠራ'ጠረ] ፣ ፈ'ራ ተ'ባ ማለት [አለ]
hew
ሀ'ዉው -ግ- መፈልፈል [ፈለ'ፈለ] ፡ መጥረብ [ጠ'ረበ] (ለደንጊያ)
hibernate
ˈሃይበነይት -ግ- ማንቀላፋት [አንቀላ'ፋ] (የክ ረምትን ጊዜ ፡ ለእንቁራሪት መዘተ)
hidden
ˈሂደን -ቅ- የተሸ'ሸገ ፡ የተደ'በቀ
hide
ˈሀይድ -ግ- መደ'በቅ [ደ'በቀ]
hideous
ˈሂዲየስ -ቅ- መልክ ጥፉ ፡ ማስጠ'ሉ ፡ እስተ ያ'ማ
high
ˈሀይ -ቅ- ከ'ፍ ያለ
highly
ˈሀይሊ -ተግ- በጥ'ልቁ ፡ በብዙው
highness
ˈሀይነስ -ስ- ልዑል'ነት

highway
ˈሀይዌይ -ስ- አውራ ጎዳና
hike
ˈሃይክ -ግ- በግር ረጅም መንገድ መንሸራ ሸር [ተንሸራ'ሸረ]
hilarious
ሂ'ሌሪየስ -ቅ- በጣም አስደ'ሳች [ጊዜ] ፣ ሣቅ'ና ደ'ስታ የሞ'ላበት
hilarity
ˈሂላሪቲ -ስ- ደ'ስታ
hill
ˈሂል -ስ- ወቀበት ፣ ኮረብታ
hillock
ˈሂለክ -ስ- ጉ'ብታ ፣ ት'ንሽ ኮረብታ
hilt
ˈሂልት -ስ- የጉራዴ ፣ የሠይፍ እ'ጀታ
him
ˈሂም -ተስ- እርሱን ፣ እ'ሱን
himself
ሂም'ሰልፍ -ተስ- እርሱ ራሱ ፣ እ'ሱ ራሱ
hind
ˈሀይንድ -ስ- ኋላ (ጀርባ)
hinder
ˈሂንደ -ግ- ማ'ወክ [አ'ወከ] ፣ መከልከል [ከለ'ከለ]
hindrance
ˈሂንድረንስ -ስ- እንቅፋት ፣ መሰናክል
hinge
ˈሂንጅ -ስ- ማጠፊያ (የበ'ር ፣ የመስኮት ወዘተ)
hint
ˈሂንት -ስ- አ'ሞር ጠቃሚ ምክር
hip
ˈሂፕ -ስ- ዳ'ሌ
hippopotamus
ሂፖ'ፖተመስ -ስ- ጉማ'ሬ
hire
ˈሀየ -ግ- መ'ከራየት [ተከራ'የ]
employ
-ግ- መቅጠር [ቀ'ጠረ]
hireling
ˈሀየሊንግ -ስ- በተንዘብ የተቀ'ጠረ ሞያተ'ኛ፣ ለተንዘብ ሲል የ'ሚ'ሠ'ጋ ወ'ታ'ደር
his
ˈሂዝ -ተስ- የርሱ ፣ የ'ሱ
hiss
ˈሂስ -ስ- እ'ስ ማለት (እንደ እባብ) ፣ አለመስ ማማትን ለመግለጽ "እ'ስ'' ማለት
historian
ሂስ'ቶሪየን -ቅ- ባለታሪክ ፣ ታሪክ ወዋቂ ፣ ታሪክ ጸሓፊ ፣ የታሪክ ሊቅ
historic
ሂስ'ቶሪክ -ቅ- ታሪካዊ
history
ˈሂስተሪ -ስ- ታሪክ
hit
ˈሂት -ግ- መምታት [መ'ታ]
hitch
ˈሂች -ግ- አንድ ነገር ላይ ማሰር [አ'ሰረ] ፣ ወደ ላይ ከ'ፍ ማድረግ [አደ'ረገ]
hitherto
ሂዘ'ቱ፡ -ተግ- እስከሁን ድረስ
hive
ˈሀይቭ -ስ- የንብ ቀፎ
hoard
ˈሆ፡ድ -ግ- ማ'ከማቸት [አ'ከማ'ቸ] ፣ ማድለብ [አደ'ለበ] (ንንዘብ ፣ ምግብ ወዘተ)
hoarse
ˈሆ፡ስ -ቅ- ጎርና'ና (ለድምፅ)
hoax
ˈሻውክስ -ስ- ማሞ'ኘት (በቀልድ'ና በጨዋታ)
hobble
ˈሆበል -ግ- እያ'ከሱ በዝ'ግታ መ'ሬመድ [ተራ'መደ] ፣ መቆ'የድ [ቀ'የደ]
hobby
ˈሆቢ -ስ- የትርፍ ጊዜ ሥራ (ንንዘብ የ'ማይ'ከ 'ፈሉ'በት ለመ'ደሰት፣ የ'ሚሠሩት ሥራ)
hoe
ˈሻው -ስ- መኰትኰቻ
hog
ˈሆግ -ስ- የተከላ'ሸ ሀግማ (ለእርድ የ'ሚ'ተ 'ልብ)
hoist
ˈሆይስት -ስ- እየተንሳ'ንዳ ማንጣት [እን'ጣ]
hold
ˈሻውልድ -ግ- መያዝ [ያዘ]
holder
ˈሻውልደ -ስ- መያዣ

hole
ˈሆውል -ስ- ቀዳዳ ፣ ሽንቁር
holiday
ˈሆለዲይ -ስ- በዓል ፣ የዕረፍት ቀን ፣ ዐውደ ዓመት
hollow
ˈሆለው -ቅ- ውስጡ ባዶ የሆነ ፣ ቡርቡር
holy
ˈሻውሊ -ቅ- ቅ'ዱስ
homage
ˈሆመጅ -ስ- አክብሮት ፣ የበታ'ችነትን ፣ ታ'ዛ ዥ'ነትን መግለጽ
home
ˈሻውም -ስ- መኖሪያ ቤት ፣ የተወ'ለ'ዱበት ቦታ ፣ የትውል'ድ አገር
homeless
ˈሻውምለስ -ቅ- ቤት የሌ'ለው
homely
ˈሻውምሊ -ቅ- እንግዳ ተቀ'ባይ ፣ ብሩሽ ኀ'ጽ
homesick
ˈሻውምሲክ -ቅ- አገሩ የና'ፈቀው
homespun
ˈሻውምስፐን -ቅ- እቤት የተፈ'ተለ ፣ ተራ ፣ ግልጽ
-ስ- እቤት የተፈ'ተለ ጨርቅ
homestead
ˈሻውምስቴድ -ስ- ባለቤቱ የ'ሚያርስው እር ስት ፣ በርሻ ቦታ ላይ ያ'ለ የመኖርያ ቤት
homicide
ˈሆመሳይድ -ስ- ያንድ ሰው በሌላ መ'ገደል ፣ ነፍስ ግ'ላይ
homogenous
ኽ'ሞጂነስ -ቅ- ተመሳሳይ ፣ ከመጀ'መሪያ እስከ መጨ'ረሻ አንድ ዓይነት የሆነ
honest
ˈኦነስት -ቅ- ታ'ማኝ ፣ እውነተ'ኛ
honey
ˈሀኒ -ስ- ማር
honeycomb
ˈሀኒከውም -ስ- የማር እሸት
honeymoon
ˈሀኒሙን -ስ- የጫጉላ ጊዜ ፣ የመ'ሞሸሪያ ጊዜ (ጉሞ ወደሌላ አገር ፣ ከተማ)
honorary
ˈኦነረሪ -ቅ- የ'ማይ'ከ'ፈለው (ያንድ ድር'ጅት አባል) ፣ የክብር አባል ወዘተ
honour
ˈኦነ -ግ- ማክበር [አከ'በረ]
-ስ- ክብር
honourable
ˈኦነረብል -ቅ- የተከ'በረ ፣ ክቡር
hood
ˈሁድ -ስ- ከልብስ ጋር የተያያዘ ሸማ ቆብ
hoodwink
ˈሁድዊንክ -ግ- ማ'ታለል [አ'ታ'ለለ] ፣ ማ'ሳ ሳት [አ'ሳሳተ] ፣ ዓይን መሸ'ፈን [ሸ'ፈነ] (የፈ ረስ)
hoof
ˈሁ፡ፍ -ስ- ኮ'ቴ (እግር)
hook
ˈሁክ -ስ- ሜንጦ
hooligan
ˈሁሊገን -ስ- አ'ዝ'ባሪ ፣ በጥባጭ ፣ ወ'ሮበ'ላ
hoop
ˈሁ፡ፕ -ስ- ከ'ብ ነገር (የብረት ፣ የእንጨት)
hoot
ˈሁ፡ት -ስ- የክላክስ ድምፅ ፣ የመኪና ጥሩምባ ድምፅ
hooter
ˈሁ፡ተ -ስ- ክላክስ (የመኪና ጥሩም'ባ)
hop
ˈሆፕ -ግ- በንድ እግር እ'የዘ'ለሉ መሄድ [ሄደ] ፣ እንጣ'ጥ እንጣ'ጥ ማለት [አለ]
hope
ˈሻውፕ -ግ- መ'መኘት [ተመ'ኘ] ፣ ተስፋ ማድረግ [አደ'ረገ]
-ስ- ም'ኞት ፣ ተስፋ
hopeful
ˈሻውፕፉል -ቅ- ባለም'ኞት ፣ ሙሉ ም'ኞት ያ'ለው ፣ ባለተስፋ
hopeless
ˈሻውፕለስ -ቅ- ዋጋ ቢስ ፣ ተስፋ ቢስ ፣ መድ ኀን የሌ'ለው
horde
ˈሆ፡ድ -ስ- መንጋ ፣ መወት (ም'ሳሌ ፣ የወ'ታ 'ደር መወት)
horizon
ኽ'ራይዘን -ስ- አድማስ

horizontal
ሞረ'ዎንተል ቅ- አግድም ፣ ግድምሽ
horn
'ሆን -ስ- ቀንድ
trumpet
-ስ- ቀንደ መለከት
car-
-ስ- ክላክስ
hornet
'ሆ:ንት -ስ- ተርብ
horrible
'ሆረበል ቅ- አስፈሪ ፣ አስደንጋጭ
horror
'ሆረ -ስ- ፍርሃት ፣ ድን'ጋጤ ፣ መ'ደፍ
horse
'ሆ:ስ -ስ- ፈረስ
horsecloth
'ሆ:ክሎዝ -ስ- ቀሚስ (የፈረስ)
horseman
'ሆ:ስመን -ስ- ፈረስ'ኛ
horseradish
'ሆ:ስራዲሽ -ስ- ፍጅል
horseshoe
'ሆ:ሹ -ስ- የፈረስ ጫ'ማ
horticulture
'ሆ:ቲከልቸ -ስ- ያበባ መትከል ሞያ ፣ ያትክ ልት ቦታ አ'ያያዝ
hose
'ሆውዝ -ስ- ያትከልት ግጠሚ ጉ'ማ ፣ ቧሬ ፣ ፕላስቲክ (ቀ'ጭን ረጅ'ም ውስጡ ባዶ የሆነ ፣ የዓ'ያ ዓይነት)
hospitable
ሆስ'ፒተብል ቅ- እንግዳ ተቀ'ባይ
hospital
'ሆስፒተል -ስ- የሐኪም ቤት ፣ ሆስፒታል
hospitality
ሆስፒ'ታለቲ -ስ- እንግዳ ተቀ'ባይ'ነት
host
'ሸውስት -ስ- አስተናጋጅ ፣ እንግዳ ተቀ'ባይ (ወንድ) ፣ የሰው መዓት (ብዙ ሰው)
host
'ሸውስት -ስ- ጎብስት (ለሥጋ ወደሙ የ'ሚ ቀርብ) ፣ እ'ኩቱት
hostage
'ሆስተጅ -ስ- መያዣ የ'ሚሆን የመር አስረ'ኛ
hostel
'ሆስተል -ስ- በል'ዩ ድር'ጅት የ'ሚ'መ'ራ መኖርያ ቤት (የተማሪዎ'ች ፣ የሠ'ራተ'ኞ'ች ወዘተ)
hostess
'ሀውስተስ -ስ- እንግዳ ተቀ'ባይ (ሴት) ፣ ሴት አስተናጋጅ
hostile
'ሆስታይል ቅ- ጠላት'ነት የ'ሚያሳይ ፣ የጠ ላት
hostility
ሆስ'ቲሊቲ -ስ- ጠላት'ነት
hot
'ሆት ቅ- ሙቅ
hotel
ሀው'ቴል -ስ- ሆቴል
hound
'ሀውንድ -ስ- ው'ሻ (በተለ'ይ የአደን ፣ የሽቅ ድ'ድም)
hour
'አወ -ስ- ሰዓት ፣ ጊዜ
hourly
'አወሲ ተግ- በ'የሰዓቱ (የተደ'ረገ ፣ የሆነ)
house
'ሀውስ -ስ- ቤት
household
'ሀውስሆውልድ -ስ- ቤተሰብ
housekeeper
'ሀውስኪፕ -ስ- ገረድ (በዕድሜ የገ'ፋ'ች)
housemaid
'ሀውስሜይድ -ስ- ገረድ (በዕድሜ አነ'ስ ያለ'ች)
hovel
'ሆቭል -ስ- መ'ኖ'ኛ ት'ንሽ ጉ'ጅ
hover
'ሆቨ -ግ- ማንጎበብ (አንጎ'በበ)
how
'ሀው -ተግ- እንዴት
however
ሆ'ዌቨ -ተግ- ቢሆን'ም ፣ይሁን'ና ፣ በም'ም ሁናቴ ፣ በም'ም መንገድ

howl
'ሀውል -ግ- በከ'ፍተ'ኛ ድምፅ መ-ጮኽ [ጮ'ኸ] (ለው'ሻ ለቀበር)
hub
'ሻብ -ስ- የመንኩራኩር መካ'ከል ክፍል
hubbub
'ሻበብ -ስ- የካታ
huddle
'ሻደል -ግ- መ'ታፈግ [ታ'ፈገ] (እንደበግ) ፣ መ'ዘጋጋግ [ተ'ዘጋ'ገ] (ለመ-ቀት)
hue
ሆ'ዩው -ስ- ቀለም ፣ መልክ (ቀ'ይ ፣ አረንጓዴ ፣ ብጫ'ና ፣ ሰማያዊ)
hug
'ሻግ -ግ- ማቀፍ [አ'ቀፈ]
huge
ሆ'ዩጅ ቅ- በጣም ት'ልቅ
hum
'ሻም -ስ- ድምፅ (እፍን ዘንቶ የ'ሚ'ሰ'ማ) ሀ'ምታ ፣ ማንጉራጉር (ዘፈን)
human
ሆ'ዩ:መን ቅ- ሰብአዊ
-ስ- ሰው
humane
ሀዩ'ሜይን ቅ- ርኅሩኅ ፣ ሰብአዊ
humanity
ሀዩ'ማኑቲ -ስ- ሰብአዊ'ነት ፣ የሰው ልጅ ፣ ርኅራኄ
humble
'ሻምበል ቅ- ትሑት
humdrum
'ሻምድረም ቅ- አሰልቺ ፣ተራ ፣ትርኪምርኪ
humid
ሆ'ዩ:ሚድ ቅ- እርጥብ
humidity
ሀዩ'ሚዲቲ -ስ- እርጥበት
humiliate
ሀዩ'ሚሊ.ዩይት -ግ- ማ'ዋረድ [አ'ዋ'ረደ] ፣ ማሳ'ፈር [አሳ'ፈረ]
humility
ሀዩ'ሚለቲ -ስ- ትሕት'ና
hummock
'ሻመክ -ስ- ት'ንሽ ጉ'ብታ
humour
ሆ'ዩው -ስ- ማት ፣ ቀልድ ፣ ቧልት
humourous
ሆ'ዩመረስ ቅ- ማ'ቲተ'ኛ ፣ ቀልደ'ኛ ፣ ቧል ተ'ኛ ፣ አ'ሥቂ'ኝ
hump
'ሻምፕ -ስ- ኻ'ኛ (የግመል ወዘተ)
humpback
'ሻምፕባክ -ስ- እጀርባው ላይ ጉ'ብታ ያ'ለ 'ባት ሰው
hunch
'ሻንች -ግ- ሰው'ነትን ሽም'ትት ማድረግ [አደ'ረገ] (ከብርድ የተነ'ሣ)
-ስ- ዋር'ጫፊ
hunchback
'ሻንችባክ -ስ- እጀርባው ላይ ጉ'ብታ ያ'ለ'ባ ት ሰው
hundred
'ሻንድረድ ቅ- መቶ
hundredth
'ሻንድረድዝ ቅ- መ'ቶኛ
hunger
'ሻንገ - ስ- ረኀብ
hungry
'ሻንገሪ ቅ- ረኀብተ'ኛ ፣ የራበው
hunt
'ሸ:ንት -ግ- ማ'ደን [አ'ደነ]
hunter
'ሻንተ -ስ- አዳ'ኝ
hurl
'ሸ:ል -ግ- በኀይል መወርወር [መረ'ወረ] ፣ በኀይል መ'ናገር [ተና'ገረ]
hurricane
'ሀሪከን -ስ- በጣም ኀይለ'ኛ ነፋስ (በሰዓት ከፀጀ ኪ.ሜ በላይ ፍጥነት ያ'ለው)
hurry
'ሻሪ -ግ- መፍጠን [ፈ'ጠነ]
hurt
'ሸ:ት -ግ- መ'ጎዳት [ጎ'ዳ] ፣ ማቁሰል [አቆ 'ሰለ]
husband
'ሽዝበንድ -ስ- ባል ፣ ባለቤት (ተባዕት)
hush
'ሻሽ -ስ- ፀ'ጥታ ፣ (ትእዛዝ ፣ ፀ'ጥ በል)

husk
ˀሽሰከ -ሱ- ሸፋን (የእህል) ፣ ል'ጣጭ (የፍራፍሬ)

husky
ˀሽሰኪ -ቅ- ወፍራም ጠንካ'ራ (ለሰው)
voice
-ቅ- ወፍራም ድምፅ

hustle
ˀሽሰል -ግ- በፍጥነት መሄድ [ሄደ]

hut
ˀሽት -ሱ- ጎ'ጆ

hutch
ˀሽች -ሱ- የትን'ንሽ እንሰሳት ማስቀ'መጫ ሣጥን (ባንድ በ'ኩል የሽቦ ወንፊት ያ'ል'በት)

hybrid
ˀሀይብሪድ -ሱ- ከ'ልስ (ለእንሰሳት ፣ ለእትክልት)

hydrophobia
ˀሀይድሪ'ፈውቢየ -ሱ- የው'ሻ በ'ሽታ ፣ ውሃ የ'ማያስጠ'ጣ ፣ ውሃ የ'ሚያስፈ'ራ በ'ሽታ

hyena
ሀ'ይና -ሱ- ጅብ

hygiene
ሀይ'ጂይን -ሱ- የጤና አ'ጠባበቅ ትምህርት ፣ የንጽሕ'ና መሠረታዊ ልምዶ'ች ፣ ንጽሕ'ና

hygienic
ሀይ'ጂይኒክ -ቅ- ጤና'ማ ፣ ንጹሕ ፣ ለጤና አ'ጠባበቅ ተስማሚ

hymn
ˀሂመ -ሱ- መዝሙር (መንፈሳዊ) ፣ ማሕሌት

hyphen
ˀሃይፈን -ሱ- አግድም ሠረዝ (—)

hypnotise
ˀሂፕኖታይዝ -ግ- ማደንዘዝ [አደነ'ዘዘ] ፣ አእምሮ መሰ'ወር [ሰ'ወረ] ፣ ማፍዘዝ [አፈ'ዘዘ]

hypocrisy
ሂ'ፖክረሲ -ሱ- ግ'ብዝ'ነት ፣ መ'መሰያሸት

hypocrite
ˀሂፐክሪት -ቅ- ግ'ብዝ ፣ ተመጻዳቂ

hypothesis
ሃይ'ፖ'ቧሲስ -ሱ- መላ ምት ፣ የምናልባት ሐ'ሳብ

hysterical
ሂስ'ቴረከል -ቅ- አንድ ነገር አእምሮውን ያ'ና'ወጠው ፣ ግ'ልፍተ'ኛ

I

ibis
ˀአይቢስ -ሱ- ጋጋኖ

ice
ˀአይስ -ሱ- በረዶ (የረ'ጋ ውሃ)

icecream
ˀአይስክሪይም -ሱ- አይስ ክሪም ፣ ጂላ'ቲ (ከበረዶ የተሠ'ራ ጣፋጭ ምግብ)

icy
ˀአይሲ -ቅ- በጣም ብርዳም

idea
አይ'ዲየ -ሱ- ሐ'ሳብ

ideal
አይ'ዲየል -ቅ- የ'ሚስማ'ማ ፣ ፍ'ጹም የሆነ ፣ እንከን የሌ'ለ'በት

identical
አይ'ዴንተክል -ቅ- ተመሳሳይ ፣ በምን'ም ሁናቴ ል'ዩ'ነት የ'ማያሳ'ይ

identify
አይ'ዴንተፋይ -ግ- ለ'ይቶ ማወቅ [ዐ'ወቀ]

identity
አይ'ዴንተቲ -ሱ- መ'ታወቂያ

idiom
ˀኢድየም -ሱ- ያ'ንጋር ዘየ ፣ ያ'ገላለጽ መን ገድ (ያንድ ቋንቋ)

idiot
ˀኢድየት -ሱ- ደ'ደብ ሰው

idiotic
ኢድ'ዮቲክ -ቅ- ደንቆሮ ፣ ደ'ደብ

idle
ˀአይደል -ቅ- ሥራ ፈ'ት ፣ ሰነፍ ፣ እሥራ ላይ ያልዋለ

idleness
ˀአይደልኔስ -ሱ- ሥራ ፈ'ት'ነት

idol
ˀአይደል -ሱ- ጣኦት

idolize
ˀአይደላይዝ -ግ- ከ'ሚ'ኮ'ባው በላይ መውደድ ፣ ማድነቅ'ና ክብር መስጠት [ሰ'ጠ]

if
ˀኢፍ -መ- በ . . . ፣ ከ . . .

ignite
ኢግ'ናይት -ግ- መለ'ኩስ [ለ'ኰሰ] ፣ ግ'ቃ ጠል [አ'ቃ'ጠለ]

ignition
ኢግ'ኒሽን -ሱ- መለ'ኮስ ፣ ግ'ቃጠል
engine
-ሱ- ሞቶር ማስነ'ሻ

ignoble
ኢግ'ንውብል -ቅ- ወ'ራ'ዳ ፣ ክብር የሌ'ለው

ignominy
ˀኢግ'ኖሚ -ሱ- ውርደት (በሕዝብ መካ'ከል) ፣ የ'ሚያሳ'ፍር ሥራ

ignorance
ˀኢግ'ረንስ -ሱ- ድንቁር'ና ፣ አለማወቅ

ignorant
ˀኢግ'ረንት -ቅ- ደንቆሮ ፣ አላዋቂ

ignore
ኢግ'ኖ፡ -ግ- ˀቸል ማለት [አለ]

ill
ˀኢል -ግ- መ'ታመም [ታ'መመ]

illegal
ኢ'ሊይገል -ቅ- ሕ'ጎ ወ'ጥ

illegible
ኢ'ሌጀበል -ቅ- የ'ማይ'ነ'በብ

illegitimate
ኢለ'ጂተመት -ቅ- ዲቃላ ፣ ሕ'ጋዊ ያልሆነ

illicit
ኢ'ሊሲት -ቅ- ሕ'ጋዊ ያልሆነ ፣ የ'ማይ'ፈ'ቀድ

illiteracy
ኢ'ሊተረሲ -ሱ- ማንበብ'ና መጻፍ አለመቻል

illiterate
ኢ'ሊተረት -ቅ- ማንበብ'ና መጻፍ የ'ማይችል

illness
ˀኢልነስ -ሱ- ሕመም ፣ በ'ሽታ

ill-tempered
ኢል'ቴምፐር -ቅ- የ'ማይ'ታ'ገሥ ፣ በቀ'ላሉ የ'ሚ'ቆጣ ፣ ግ'ልፍተ'ኛ

illuminate
ኢል'ዩ፡መኔይት -ግ- ማብራት [አበ'ራ]

illusion
ኢ'ሉ፡ዠን -ሱ- ለዓይን የ'ሚመስል ነገር (ነገር ግን እውነት ያልሆነ) ፣ ምትሀት

illustrate
ˀኢለስትሬይት -ግ- በሥዕላ ሥዕል ማስጌጥ [አስጌጠ] (ለመጽሐፍ)
use examples
-ግ- በም'ሳሌ ማስረ'ዳት [አስረ'ዳ]

illustration
ኢለስት'ሬይሽን -ሱ- ሥዕል
example
-ሱ- ም'ሳሌ

illustrious
ˈማ: -ግ- ማ'በላሸት [አ'በላ'ሸ] ፣ ማጥፋት [አጠ'ፋ] ፣ ማፈራረስ [አፈራ'ረሰ]
marble
ˈማ:በል -ስ- እብነ በረድ
march
ˈማ:ች -ግ- በሰልፍ መ'ጓዝ [ተጓዘ]
March
ˈማ:ች -ስ- መ'ጋቢት (የወር ስም)
mare
ˈሜየ -ስ- ሴት ፈረስ ፣ ባዝራ
margin
ˈማ:ጂን -ስ- ሕ'ዳግ (የመጽሐፍ ወዘተ) ፣ ጻር (የሐይቅ ወዘተ)
marine
መ'ሪይን -ስ- የጦር መርከበ'ኛ
-ቅ- የባሕር
marital
ˈማሪተል -ቅ- የ'ጋብ'ቻ
maritime
ˈማሪታይም -ስ- የባሕር ንግድ
mark
ˈማ:ክ -ግ- ም'ልክት ማድረግ [አደ'ረገ]
-ስ- ም'ልክት
market
ˈማ:ክት -ስ- ገበያ
market-place
ˈማ:ክትፕሌይስ -ስ- ገበያ
marksman
ˈማ:ክስመን -ስ- ጥሩ አ'ነጣጣሪ ፣ ተ'ኩሶ የ'ማይስት
maroon
መ'ሩን -ቅ- ወደ ቀ'ይ'ነት የ'ሚያደላ ቡ'ና'ማ ቀለም
leave stranded
-ግ- ሰውን በች'ግር ላይ ጥሎ መሄድ [ሄደ] (ም'ሳሌ ፣ ሰው በሌ'ሰ'በት ደሴት ወዘተ)
marquee
ማ:ኪይ -ስ- ጸ'ሰ ፣ ት'ልቅ ድንኳን
marriage
ˈማሪጅ -ስ- ጋብ'ቻ
married
ˈማሪድ -ቅ- ያ'ገ'ባ ፣ ባልትዳር
marrow
ˈማሪው -ስ- ጻ'ባ ፣ መትኒ'መቅን (የቅልጥም) ፣ ቅልጥም
marry
ማሪ -ግ- ማ'ገባት [አ'ገ'ባ]
marsh
ˈማ:ሽ -ስ- ረግረግ
marshal
ˈማ:ሸል -ስ- ሰልፍ መ'ሳቂ ፣ ሰልፍ ተቆጣጣሪ
mart
ˈማ:ት -ስ- ገበያ ፣ ሕ'ሪጅ የ'ሚ'ሰል'በት ሴት
martial
ˈማ:ሸል -ቅ- የወ'ታ'ደር ፣ ወ'ታ'ዶራዊ
martyr
ˈማ:ተ -ስ- ሰማዕት
marvel
ˈማ:ቭል -ግ- መ'ደነቅ [ተደ'ነቀ] ፣ መ'ደናገር [ተደና'ገረ] (በመ'ደሰት)
marvellous
ˈማ:ቭለስ -ቅ- አስደ'ናቂ ፣ ግሩም (በመ'ደሰት)
masculine
ˈማስክዩሊን -ስ- ተባዕት ፣ ወንድ
mash
ˈማሽ -ግ- ማድቀቅ [አደ'ቀቀ] ፣ መደፍጠጥ [ደፈ'ጠጠ] (ለወተ ምግቦች)
mask
ˈማ:სክ -ስ- ሽፋን (የፊት መሸ'ሸጊያ'ና ሌላ ቅርፅ የ'ሚሰጥ)
mason
ˈሜይሰን -ስ- ደንጊያ ጠራቢ
masquerade
ˈማስክሬይድ -ቅ- ማ'ታለል ፣ እውነት ያልሆነ
mass
ˈማስ -ስ- ክብደት
religious service
-ስ- ቅ'ዳሴ
majority
-ስ- ይበልጡ ሕዝብ ፣ ባንድ ቦታ የተከ ማ'ቸ ሕዝብ

massacre
ˈማሰከ -ግ- መ'ፃደል [ጎ'ደለ] ፣ መፍጀት [ፈ'ጀ] (ለሰው)
massage
ˈማሳ:ጅ -ግ- ማሸት [አ'ሸ] (ለው'ነት)
massive
ˈማሲቭ -ቅ- በጣም ት'ልቅ'ና ከ'ባድ
mast
ˈማ:ስት -ስ- የመርከብ ተራዳ
master
ˈማ:ስተ -ስ- ጌታ ፣ መ'ሪ ፣ አ'ዛዥ
masterful
ˈማ:ስተፉል -ቅ- ጎ'ደለ'ኛ (ገጸ'ባ) ፣ ሥልጣኑን በሌ'ሎች ላይ መ'ጠ'ጋት የ'ሚወ'ድ ፣ የ'ሚ ችል ፣ ታ'ላቅ ችሎታ ያ'ለው
masticate
ˈማስቲኬይት -ግ- ማ'ኘክ [አ'ኘከ] ፣ ማ'ላመጥ [አ'ላመጠ]
mat
ˈማት -ስ- ሰሌን (የወለል ምንጣፍ)
match
ˈማች -ስ- ክብሪት
resemble
-ግ- መ'መሳሰል [ተመሳ'ሰለ]
sport
-ስ- ግጥሚያ (ስ'ፖርት)
match-maker
ˈማች ሜይክ -ስ- አ'ባባይ ፣ አ'ማጭ (ለጋብ'ቻ)
mate
ˈሜይት -ስ- የሥራ ጓ'ደ'ኛ ፣ ጓ'ደ'ኛ ፣ ሚስት ፣ ባል
material
መ'ቲሪየል -ስ- ጨርቃ ጨርቅ ፣ አንድ ዕቃ የ'ሚ'ሠራ'በት ነገር
materialize
መ'ቲሪየላይዝ -ግ- እ'ዳማ ማድረስ [አደ'ረሰ] ፣ እሥራ ላይ ማዋል [አዋለ]
maternal
መ'ተ:ነል -ቅ- የእ'ናት ፣ እ'ናታዊ
maternity
መ'ተ:ነቲ -ስ- እ'ናት'ነት
mathematics
ማ፧'ማቲክስ -ስ- የሒሳብ ትምህርት ፣ የሒ ሳብ ዕውቀት

matriculation
መትረክዩ'ሌይሽን -ስ- የሁሰ'ተ'ኛ ደረጃ ትም ህርት ቤት መልቀቂያ ፈተና
matrimony
ˈማትረመኒ -ስ- ጋብ'ቻ
matron
ˈሜይትረን -ስ- በትጸር ብዙ ጊዜ የኖረ'ች ሴት ፣ ያገድ ድር'ጅት ኀላፊ የሆነ'ች ሴት (በሆ ስፒታል ወዘተ)
matter
ˈማተ -ስ- ነገር ፣ ጉ'ዳይ
matter-of-fact
ማተረ'ፋክት -ቅ- ተራ (ሁናቴ) ፣ ደንታ የሌ 'ለው ፣ እውነቱ ብ'ቻ የ'ሚገ'ደው
matting
ˈማቲንግ -ስ- ሳጣራ ፣ ሰሌን ወዘተ
mattress
ˈማትረስ -ስ- ፍራሽ
mature
መ'ቹወ -ቅ- የበ'ሰለ (ለሰው)
maturity
መ'ቹሪቲ -ስ- እድ'ገት ፣ መብሰል (ለፅድሚ)
maul
ˈሞ:ል -ግ- መቦጫጨቅ [በጫ'ጨቀ] ፣ የጭ'ካ ኔ ተግባር መፈ'ጸም [ፈ'ጸመ]
mauve
ˈመውቭ -ቅ- ጠቆ'ር ያለ ሰማያዊ
May
ˈሜይ -ስ- ግንቦት
may
ˈሜይ -ግ- መ'ቻል [ቻለ] ፣ ፈቃድ መ'ቀበል [ተቀ'በለ] (እንደ ረ'ዳት ግ'ሥ ዋር'ማሬን ፣ ም 'ኞትን'ና ፈቃድን ይገልጣል)
maybe
ˈሜይቢ -ተግ- ሊሆን ይች'ላል ፣ ምናልባት
mayor
ˈሜየ -ስ- ከን'ቲባ ፣ የከተማ ገ'ዥ
maze
ˈሜይዝ -ስ- መጣቢያ'ና መውጫው የ'ማይ' ታ'ወቅ መንገድ፤ የተወሳ'ሰበ ጉ'ዳይ፣ሐ'ሳብ
me
ˈሚይ -ተስ- እኔን ፣ ለኔ
meadow
ˈሜደው -ስ- መስክ

meagre
ˈሚገ ፡ -ቅ- ት'ንሽ ፡ የ'ማይበቃ (ምግብ ወዘተ)
meal
ˈሚይል ፡ -ስ- ምግብ (የተዘጋ'ጀ)
mean
ˈሚይን ፡ -ቅ- ንብጋ'ባ ፡ ቆጥቋጣ (ለንጉዘብ ወዘተ) ፡ አስቀ'ያሚ ፤ የ'ማይ'ነ'ባ (ለጠባይ)
meaning
ˈሚይኒንግ ፡ -ስ- ትርጉም ፡ ፍ'ች
means
ˈሚይንዝ ፡ -ስ- መንገድ ፡ ብልጎት
meantime
ˈሚይን'ታይም ፡ -ተግ- ወዲያው'ም በ'ዚያው'ም ጊዜ ፡ በ'ዚህ'ም መካ'ከል
meanwhile
ሚይን'ዋይል ፡ -ተግ- ወዲያ'ው'ም ፡ በ'ዚያው'ም ፡ በ'ዚህ'ም መካ'ከል
measles
ˈሚይዘልዝ ፡ -ስ- ኩ'ፍ'ኝ
measure
ˈሜዠ ፡ -ግ- መለ'ካት [ለ'ካ]
meat
ˈሚይት ፡ -ስ- ሥጋ
mechanic
ሚ'ካኒክ ፡ -ስ- ሜካኒክ
medal
ˈሜደል ፡ -ስ- ኒሻን ፡ ሊሻን
meddle
ˈሜደል ፡ -ግ- ጥ'ል'ት ማለት [አለ] (በሰው ጉ'ዳይ)
mediate
ˈሚይዲይይት ፡ -ግ- መሸምገል [ሸመ'ገለ] (ለማ ስታረቅ)
medical
ˈሜዲካል ፡ -ቅ- የመድኃኒት
medication
ሜዲ'ኬይሽን ፡ -ስ- መድኃኒት ፡ ሕ'ክም'ና
medicinal
መ'ዲሰንል ፡ -ቅ- መድኃኒት'ነት ያ'ለው
medicine
ˈሜደሰን ፡ -ስ- መድኃኒት
medieval
ሚ'ዲይቭል ፡ -ስ- ማእከላዊ ዘመን (ከ፭ኛ፻፭ እስከ ፲፭ኛ፻ ዓ ም ገደማ ያ'ለው የአውሮ'ፓ ታሪክ)
meditate
ˈሜዲቴይት ፡ -ግ- አጥልቆ ማ'ሰብ [አ'ሰበ] ፡ ከል'ብ ማ'ሰላሰል [አ'ሰላ'ሰለ]
medium
ˈሚይዲየም ፡ -ቅ- መካ'ከለ'ኛ ፡ ደልዳ'ሳ (ለቁ መት)
meek
ˈሚይክ ፡ -ቅ- ትሑት ፡ ታ'ዛዥ ፡ መከራን ታ'ጋሽ
meet
ˈሚይት ፡ -ግ- መ'ገናኘት [ተገና'ኘ]
meeting
ˈሚይቲንግ ፡ -ስ- ስብሰባ ፡ መ'ገናኘት
melancholy
ˈሜላንኮሊ ፡ -ስ- ጥልቅ ሐዘን ፡ ጭንቅ
mellow
ˈሜለው ፡ -ቅ- የበ'ሰለ ፡ ለስላ'ሳ'ና ጣፋጭ ፡ ዕድሜ ያስተማረው ፡ የተዝና'ና
melodious
መ'ለውዲየስ ፡ -ቅ- ጣዕመ ዜማ ያ'ለው
melody
ˈሜለዲ ፡ -ስ- ጣዕመ ዜማ
melon
ˈሜለን ፡ -ስ- ከርቡሽ ፡ በ'ጢሽ
melt
ˈሜልት ፡ -ግ- መቅለጥ [ቀ'ለጠ] ፡ ማቅለጥ [አቀ'ለጠ]
member
ˈሜምበ ፡ -ስ- አባል
membrane
ˈሜምብሬይን ፡ -ስ- ሥሥ ሽፋን (የሰውን ፡ የእንሰሳን ሥጋ የ'ሚያ'ገና'ኝ ፡ የ'ሚሸ'ፍን)
memento
መ'ሜንተው ፡ -ስ- የማስታወሻ ዕቃ (ያንዱን ሰው የተለ'የ ሁናቴ የ'ሚያስታ'ውሰ'በት)
memoir
ˈሜምዋ ፡ -ስ- የራስ ታሪክ ፡ የሰው ታሪክ (ያ'ዩት በመጽሐፍ መልክ)
memorable
ˈሚመረበል ፡ -ቅ- የ'ሚታ'ወስ ፡ የ'ማይረ'ሳ

memorial
መ'ሞ'ሪየል ፡ -ስ- መ'ታሰቢያ (የመ'ቃ'ኑት ፡ የታ'ላቅ ሰዎ'ች)
memorize
ˈሚመራይዝ ፡ -ግ- ማስታወስ [አስታ'ወሰ] ፡ በቃል ማጥናት [አጠ'ና]
memory
ˈሚመሪ ፡ -ስ- ት'ዝታ
menace
ˈሜነስ ፡ -ግ- መዛት [ዛተ] ፡ ማስፈራራት [አስ ፈራ'ራ]
menacing
ˈሜነሲንግ ፡ -ስ- አስፈ'ሪ ፡ የ'ሚዝት
menagerie
ሞ'ናጀሪ ፡ -ስ- የዱር እንሰሳት ማኖሪያ ቦታ (በተለ'ይ ካገር አገር እ'የተዘዋ'ወሩ ለሰው የ'ሚ ታ'ዩ)
mend
ˈሜንድ ፡ -ግ- መጠ'ገን [ጠ'ገነ]
menial
ˈሚይኒየል ፡ -ቅ- ወ'ራ'ዳ (ሥራ) ፡ -ስ- የቤት አገልጋይ
menstruation
ሜንስትሩ'ዌይሽን ፡ -ስ- አደፍ ፡ እንግዳ (የሴት ደም)
mental
ˈሜንተል ፡ -ቅ- የአእምሮ
mentality
ሜን'ታሉቲ ፡ -ስ- አእምሮ ፡ አስተሳሰብ
mention
ˈሜንሽን ፡ -ግ- መጥቀስ [ጠ'ቀሰ]
mercantile
ˈመ:ከንታይል ፡ -ቅ- የንግድ ፡ የ'ጋዴ
mercenary
ˈመ:ሰነሪ ፡ -ስ- በገንዘብ የተገ'ዛ ወ'ታ'ደር *greedy* ፡ -ቅ- ስለገንዘብ ብ'ቻ የ'ሚያ'ስብ ፡ ቆጥ ቋ'ጣ
merchandise
ˈመ:ቸንዳይዝ ፡ -ስ- የንግድ ዕቃ
merchant
ˈመ:ቸንት ፡ -ስ- ነ'ጋዴ
merciful
ˈመ:ሲፉል ፡ -ቅ- መሐሪ ፡ ርኅሩኅ
mercury
ˈመ:ክዩሪ ፡ -ስ- ባዜቃ
mercy
ˈመ:ሲ ፡ -ስ- ምሕረት
mere
ˈሚየ ፡ -ቅ- ተጨ'ማሪ'ም ፡ ተቀ'ናሽ'ም የሉ'ለ'በት ፡ ቀ'ላል (ብ'ቻ)
merely
ˈሚየሊ ፡ -ተግ- እንዲያው ፡ ብ'ቻ ፡ በቀ'ላሉ
merge
ˈመ:ጅ ፡ -ግ- መ'ደባለቅ [ተደባ'ለቀ]
merger
ˈመ:ጀ ፡ -ስ- የሁለ'ት ድር'ጅቶ'ች መ'ዋሐድ (የን ግድ)
merit
ˈሜሪት ፡ -ስ- ሽ'ልማት የማግኘት ተገቢ'ነት ፡ የመ'መስገን ተገቢ'ነት
mermaid
ˈመ:ሜይድ ፡ -ስ- ጀራቱ የወሚ የተቀ'ረው ሰው'ነቱ ግን የሰው ቅርፅ ያ'ለው ፍጡር
merriment
ˈሜሪሜንት ፡ -ስ- ደ'ስታ
merry
ˈሜሪ ፡ -ቅ- ደ'ስተ'ኛ
mesh
ˈሜሽ ፡ -ስ- መረብ ፡ መርበብ (ዐሣ ማጥመጃ)
mess
ˈሜስ ፡ -ስ- ዘረክራ'ካ'ነት ፡ የንጽሕ'ና ጉድለት አለመ'ስተር
message
ˈሜሰጅ ፡ -ስ- መልእክት
messenger
ˈሜሰንጀ ፡ -ስ- መልእክተ'ኛ ፡ ተላላኪ
metal
ˈሜተል ፡ -ስ- ብረታ ብረት
metallic
ሜ'ታሊክ ፡ -ቅ- ብረት መ'ሰል ፡ የብረት ፡ ብረት ያ'ለ'በት
meter
ˈሚይተ ፡ -ስ- መቁጠሪያ (የኤሌትሪክ ፡ የውሃ ወዘተ)
method
ሜ'ዐድ ፡ -ስ- መንገድ (የአ'ሠራር)

methodical
ሜ'ቲዲከል -ቅ- ሥርዓት ጠ'ባቂ ፣ በደምብ'ና በሥርዓት የተሠ'ራ

meticulous
ሜ'ቲኩለስ -ቅ- ለጥቃ'ቅን ነገር ሠ'ሱ የ'ሚ 'ጠ'ቀ'ች ፣ በጣም ጥንቁቅ

metre
'ሚይተ -ስ- ሜትር (መለ'ኪያ)

metropolis
ሜት'ሮፐሊስ -ስ- ዋ'ና ከተማ ፣ መዲና

metropolitan
ሜትሪ'ፖሊተን -ቅ- የዋ'ና ከተማ ፣ የሊቀ ጳ'ጳሳት ወይን'ም የሰብከተ ሀገሩ

mettle
'ሜተል -ስ- ጉብዝ'ና፣መክራን መቻል (ሰሰው ፣ ለፈረስ)

microbe
'ማይክረውብ -ስ- ሚክሮብ ፣ ረቂቃን ነፍሳት

microscope
'ማይክረስኩፕ -ስ- ሚክሮስኮ'ፕ ፣ ጥቃ'ቅን ነገር'ች አጉልቶ የ'ሚያሳ'ይ መነ'ጽር

midday
ሚድ'ዴይ -ስ- ቀትር ፣ ተሲዓት

middle
'ሚደል -ቅ- መካ'ከለ'ኛ

middleman
'ሚደልማን -ስ- ጅምላ ነ'ጋዴ ፣ አማካ'ኝ ሰው (እንደ ደ'ላላ ያ'ለ)

middling
'ሚድሊንግ -ቅ- መካ'ከለ'ኛ (ለዓይነት ፣ ለመ ጠን)

midge
'ሚጅ -ስ- ት'ንሻ

midget
'ሚጀት -ስ- ድንክ

midnight
'ሚድናይት -ስ- እ'ኩለ ሌሊት

midst
'ሚደስት -ስ- መካ'ከል

midsummer
ሚድ'ሰመ -ስ- የበጋ አ'ጋማሽ

midwife
'ሚድዋይፍ -ስ- አ'ዋላጅ

might
'ማይት -ስ- ኀይል

mighty
'ማይቲ -ቅ- ኀይለ'ኛ ፣ ት'ልቅ

migrant
'ማይግረንት -ስ- ስ'ደተ'ኛ (ወደ ሌላ አገር የ'ሚሄድ)

migrate
ማይ'ግሬይት -ግ- አገሩን ለ'ቆ ወደሌላ አገር መሄድ (ሄደ) (ለመናር)

mild
'ማይልድ -ቅ- ለስላ'ሳ ፣ ጥን'ካሬ የሌ'ለው ፣ ቀ'ላል (ቅጣት ወዘተ)

mildew
'ሚልድዩው -ስ- አጣቆ

mile
'ማይል -ስ- ማይል (የርቀት መለ'ኪያ)

milestone
'ማይልስተውን -ስ- የመንገድ ርቀት መንገ ሪያ ደንጊያ (አልፎ አልፎ በመንገድ ዳር የተ ተ'ከለ)

militant
'ሚሊተንት -ቅ- ተጣይ ፣ ተዋጊ (ለእምነት ወዘተ)

military
'ሚሊተሪ -ቅ- ወ'ታ'ደራዊ

milk
'ሚልክ -ስ- ወተት

milkmaid
'ሚልክሜይድ -ስ- ወተት አላቢ ሴት

milky
'ሚልኪ -ስ- ወተት የ'ሚመስል (ፈሳሽ)

mill
'ሚል -ስ- ወፍጮ

millennium
ሚ'ሌኒየመ -ስ- አንድ ሺህ ዓመት ፣ ከምዕ ኣት በኋላ ክርስቶስ በመሬት ላይ የ'ሚነግሥ 'በት ዘመን ፣ የሰላም'ና የደኅን'ነት ዘመን

miller
'ሚለ -ስ- ባለወፍጮ ፣ በወፍጮ ቤት የ'ሚ ሠራ

millet
'ሚሊት -ስ- የዳጉ'ሳ'ና የጤፍ ዓይነት እህል

milliner
'ሚሊነ -ስ- የሴት ባርኔጣ ሠሪ'ና ሻጭ

million
'ሚልየን -ስ- ሚሊዮን ፡ እልፍ አእላፋት

millstone
'ሚልስተውን -ስ- የወፍጮ ደንጊያ

mimic
'ሚሚክ -ግ- ሰው መቀ'ጸል [ቀ'ጸለ] ፣ ሰው መቀንጠጥ [ቀነ'ጠጠ] ፣ የሰው አ'ነጋገር አስ መ'ስሎ መ'ናገር [ተና'ገረ]

mimicry
'ሚሚክሪ -ስ- ሰውን ቅ'ጸላ (ለአ'ነጋገር) ፣ ቅንጠጣ

mince
'ሚንስ -ግ- መክተፍ [ከ'ተፈ]

mincing machine
'ሚንሲንግ ፣ መ'ሺይን -ስ- የሥጋ መፍጫ መኪና

mind
'ማይንድ -ስ- አእምሮ ፣ አንጉል ፣ አስተሳሰብ -ግ- መ'ቃወም [ተቃ'ወመ] ፣ መ'ጠን ቀቅ [ተጠን'ቀቀ]

mine
'ማይን -ተስ- የኔ

mineral
'ሚነረል -ስ- የማዕድ'ን ቦታ (የተቆ'ፈረ) ፣ ማዕ'ድን

mingle
'ሚንገል -ግ- መ'ደባለቅ [ተደባ'ለቀ] ፣ ማ'ደ ባለቅ [አ'ደባ'ለቀ]

miniature
'ሚኒቾ -ስ- በጣም ት'ንሽ ሥዕል ፣ ያንድ ቅር ፅ ት'ንሽ ምስል

minimize
'ሚኒማይዝ -ግ- ማሳ'ነስ [አሳ'ነሰ]

minimum
'ሚኒመም -ቅ- በተቻለ መጠን ያ'ነሰ

mining
'ማይኒንግ -ስ- የማዕ'ድን ሥራ

minister
'ሚኒስተ -ግ- ማገልገል [አገለ'ገለ] ፣ መርዳት [ረ'ዳ]
-ስ- ሚኒስትር ፣ ካህን

ministerial
ሚኒስ'ቲሪየል -ቅ- የሚኒስትር ፣ የሚኒስቴር

ministry
'ሚኒስትሪ -ስ- ሚኒስቴር (መሥሪያ ቤት)

minor
'ማይነ -ቅ- ዝ'ቅተ'ኛ ፣ ያ'ነሰ ፣ ዋጋ የሌ'ለው -ስ- ከሃያ ዓመት በታ'ች ያ'ል ሰው

minority
ማይ'ኖራቲ -ስ- ጥቂቶ'ች ፣ በቁጥር ያ'ነሱ

minstrel
'ሚንስትረል -ስ- አ'የዞረ የ'ሚዘፍን አዝማሪ

mint
'ሚንት -ስ- ገንዘብ የ'ሚ'ሠ'ራበት ቦታ
herb
-ስ- ሜንታ

minus
'ማይነስ -ቅ- ያ'ነሰ ፣ የተቀ'ነሰ'ለት

minute
'ሚኒት -ስ- ደቂቃ ፣ ቃለ ጉባኤ

minute
ማይን'ዩ:ት -ቅ- በጣም ት'ንሽ ፣ ደ'ቃቅ

miracle
'ሚረከል -ስ- ተአ'ምር ፣ የ'ሚያስደ'ንቅ ነገር ያልተለ'መደ ነገር

miraculous
ሚ'ራክዩለስ -ቅ- አስገ'ራሚ ፣ ታአ'ምራዊ

mire
'ማየ -ስ- ጭቃ ፣ አፅንቃ ፣ ቆሻሻ

mirror
'ሚረ -ስ- መስታዎት (ማያ)

mirth
'ም:ዝ -ስ- መ'ደሰት ፣ ሣቅ

misapprehension
ሚሳፕረ'ሄንሽን -ስ- በትክ'ክል አለመ'ረዳት

misbehave
ሚስቢ'ሄይቭ -ግ- አመልቢስ መሆን [ሆነ] ፣ መጥፎ አመል ማሳየት [አሳ'የ] ፣ መባለግ [ባ 'ለገ]

miscalculate
ሚስ'ካልክዩሌይት -ግ- ስሕተት ማድረግ [አ ደ'ረገ] (ባ'ሰበት ፣ በገ'መቱት ነገር)

miscarriage
'ሚስካረጅ -ስ- ማስወ'ረድ (ፅንስ)

miscarry
ሚስ'ካሪ -ግ- እፍ'ጻሜ አለመድረስ [-ደ'ረሰ]፡ ማስወ'ረድ [አስወ'ረደ] (ለእርግዝ'ና)

miscellaneous
ሚሰ'ሌይኒየስ -ቅ- ል'ዩ ል'ዩ ፣ ድብልቅልቅ
mischief
'ሚስቺፍ -ስ- አ'ዋኪ'ነት ፣ ክልፍልፍ'ነት ከፋት ፣ በተባጭ'ነት
mischievous
'ሚስቺቭስ -ቅ- ቅልብልብ ፣ አ'ዋኪ ፣ በተ ባጭ
misdemeanour
ሚስደ'ሚይነ -ስ- መጥፎ ሥራ ፣ ተሳላፊ'ነት (ሕ'ግን)
miserly
'ማይዘሊ -ቅ- ሥ'ሥታም ፣ ንብ፣ን'ባ ፣ ቆጥ ቋ'ጣ
miserable
'ሚዝረበል -ቅ- በጣም ያልተደ'ሰተ ፣ መከራ ያጠ'ቃው ፣ መከረ'ኛ
misery
'ሚዘሪ -ስ- መከራ ፣ ች'ግር
misfortune
ሚስ'ፎቹን -ስ- መጥፎ ዕ'ድል
misgiving
ሚስ'ጊቭ'ንግ -ስ- ጥር'ጣሬ ፣ ፍርሀት
mishap
'ሚስሀፕ -ስ- ድንገተ'ኛ አደጋ (ቀለ'ል ያለ)
mislay
ሚስ'ሌይ -ግ- ዕቃ ያኖሩ'በትን ቦታ ማጣት [አ'ጣ] ፣ ለጊዜው ማጣት [አ'ጣ]
mislead
ሚስ'ሊይድ -ግ- ማ'ታለል [አ'ታለለ] ፣ ማ'ሳ ሳት [አ'ሳሳተ]
misplace
ሚስፕ'ሌይስ -ግ- ያለቦታው ማስቀ'መጥ [አ ስቀ'መጠ]
misrepresentation
ሚስሬፕሪዘን'ቴይሽን -ስ- አ'ያ'ወቁ የ'ሚያቀር ቡት ማ'ሳሳያ ፣ ትክ'ክል ያልሆነ ወሬ
miss
'ሚስ -ግ- ለመድረስ ፣ ለመምታት ፣ ለማግ ኘት ወዘተ አለመቻል [-ቻለ]
Miss
'ሚስ -ስ- ወይዘሪት
missile
'ሚሳይል -ስ- ተወርዋሪ የጦር መ'ሣሪያ ፣ ተስፈንጣሪ መ'ሣሪያ
missing
'ሚሲንግ -ቅ- የጠ'ፋ
mission
'ሚሽን -ስ- ተግባር ፣ መልእክት ፣ መልእክተ 'ኞ'ች ፣ በሕይወት ሙሉ የ'ሚፈ'ጸም ተግባር
religious
-ስ- ሚሰዮን (የሃይማኖት ስብክት ድር 'ጅት)
missionary
'ሚሽነሪ -ስ- የወንጌል መልእክተ'ኛ ፣ ሚሲ ዮናዊ ሰው
mist
'ሚስት -ስ- ጭጋግ
mistake
ሚስ'ቴይክ -ግ- መ'ሳሳት [ተሳሳተ]
mistaken
ሚስ'ቴይከን -ቅ- የተሳሳተ
Mister
'ሚስተ -ስ- አቶ
mistress
'ሚስትረስ -ስ- ው'ሽማ (ሴት) ወዳጅ
employer
-ስ- እ'መቤት
mistrust
ሚስት'ረስት -ግ- አለማመን [-አ'መነ] ፣ መ'ጠ ራጠር [ተጠራ'ጠረ]
misunderstanding
ሚሰንደስ'ታንዲንግ -ስ- አለመግባባት
misuse
ሚስ'ዩ:ዝ -ግ- ማ'ባላሸት [አ'በላ'ሸ] ፣ ያለ ቦታው ማዋል [አዋለ]
misuse
ሚስ'ዩ:ስ -ስ- ማ'ባላሸት ፣ አንድ ነገር በ'ሚ 'ገባው ቦታ አለማዋል
mite
'ማይት -ስ- በጣም ት'ንሽ ነገር ፣ ት'ንሽ ሕፃን
mitigate
'ሚቲጌይት -ግ- ማ'ሻሻል [አ'ሻሻለ] ፣ ማለ 'ዘብ [አለ'ዘበ]
mitten
'ሚተን -ስ- የሱፍ እ'ጅ ሹ'ራብ (አራ'ቱን ጣት ለዳ'ቻ አውራ ጣት ለብ'ቻ የ'ሚሸ'ፍን)

mix
'ሚክስ -ግ- መደባለቅ [ደባ'ለቀ] ፣ መ'ደባለቅ [ተደባ'ለቀ]
mixture
'ሚክስቸ -ስ- የተደባ'ለቀ ነገር ፣ ማ'ደባለቅ
mix-up
'ሚክሰፕ -ስ- አለመግባባት ፣ መ'ሳሳት
moan
'መውን -ግ- ማቃሰት [አቃ'ሰተ] (ከሥቃይ የተነ'ሣ)
moat
'መውት -ስ- በቤት ዙሪያ ያ'ለ የውሃ አጥር (ለመ'ከላከያ)
mob
'ሞብ -ስ- ሕ'ዝ መ'ጥ ሰም'ች ፣ የተሰበ'ሰቡ ሰም'ች (ብጥ'ብጥ ለማንሣት ፣ እንድ ሁኖቴ ለመ'መልከት)
mobile
'መውባይል -ቅ- የ'ሚንቀሳ'ቀስ
mock
'ሞክ -ግ- ማፌዝ [አፈዘ]
mockery
'ሞከሪ -ስ- ፌዝ
mode
'መውድ -ስ- ያ'ያዥረግ መይን'ም ያ'ሠራር መን ገድ ፣ ዘዴ ፣ ሞድ (የልብስ)
model
'ሞደል -ስ- ያንድ ነገር ት'ንሽ ቅርፅ ፣ እንደ ም'ሳሌ የ'ሚ'ገለ'በተ ነገር ፣ ሞድ የ'ምታ'ይ ሴት ልጅ ፣ ጥሩ ም'ሳሌ (ሊ'ገለ'በተ የ'ሚ'ገ 'ባው)
moderate
'ሞደረት -ቅ- መካ'ከለ'ኛ
modern
'ሞደን -ቅ- ዘመናዊ ፣ እ'ዲስ ሐ'ሳብ ያ'ለው
modest
'ሞደስት -ቅ- ትሑት ፣ ጭ'ምት
modification
ሞዲፊኬይሽን -ስ- ማ'ሻሻል ፣ ት'ንሽ ለውጥ
modify
'ሞዲፋይ -ግ- ማ'ሻሻል [አ'ሻሻለ] ፣ ት'ንሽ ለውጥ ማድረግ [አደ'ረገ]
moist
'ሞይስት -ቅ- እርጥብ ፣ ዝናማም
moisten
'ሞይሰን -ግ- ማርጠብ [አረ'ጠበ]
moisture
'ሞይስቸ -ስ- እርጥበት
mole
'መውል -ስ- ፍልፈል ፣ ማርያም የሳመ'ችው ምል'ክት (በሰው'ነት ላይ)
molest
'መሌስት -ግ- ተ'ልቶ ማሰት [አሰ] (በሰው ሥራ) ፣ ማ'ወክ [አ'ወከ] (አ'ያ'ወቁ)
molten
'ሞልተን -ቅ- የቀ'ለጠ (ለብረታ ብረት)
moment
'መውመንት -ስ- ቅጽበት ፣ አፍታ
momentary
'መውመንትሪ -ቅ- አንድ አፍታ የቆ'የ
momentous
መ'ሚንተስ -ቅ- በጣም አስፈ'ላጊ
monarch
'ሞነክ -ስ- የበላይ ገ'ዥ ፣ ንጉሥ
monarchy
'ሞነኪ -ስ- ንጉሣዊ አ'ገዛዝ ፣ ማዛቁ በአንድ ከ'ፍተ'ኛ ሥልጣን ሥር ያ'ለ መንግሥት
monastery
'ሞነስትሪ -ስ- ገዳም
Monday
'መንዲይ -ስ- ሰ'ኞ
monetary
'መነትሪ -ቅ- የገንዘብ
money
'መኒ -ስ- ገንዘብ
mongrel
'ሞንግረል -ስ- መጢቃ ፣ ዘሩ የተደባ'ለቀ እንሰሳ (ው'ሻ ፣ ወዘተ)
monitor
'ሞኒተ -ስ- መክሪ ፣ አስጠንቃቂ ሰው ፣ የትም ህርት ክፍል አለቃ (ተማሪ)
monk
'መንክ -ስ- መነኩሴ
monkey
'መንኪ -ስ- ዝንጀሮ
monopoly
መ'ኖፖሊ -ስ- አንድ ዓይነት ንግድ ያለ ተወ ዳዳሪ መያዝ

monotonous
መ'ናተኑስ -ቅ- አሰልቺ
monster
'ሞንስተ -ስ- ታ'ላቅ አስፈ'ሪ ፍጡር ወይን'ም ትልቅ ተክል
monstrous
'ሞንስትረስ -ቅ- በጣም ትልቅ ፣ አስደንጋጭ፣ አስፈ'ሪ
month
'መን -ስ- ወር
monument
'ሞንዩመንት -ስ- ሐውልት
mood
'ሙ:ድ -ስ- አ'ኳኋን ፣ ስ'ሜት
moody
'ሙ:ዲ -ቅ- አመለ'ኛ ፣ ነጭ'ጫ ፣ አመለዚስ
moon
'ሙ:ን -ስ- ጨረቃ
moonlight
'ሙ:ንላይት -ስ- የጨረቃ ብርሃን
moor
'ሞ: -ስ- ሰ'ፊ ጠፍ ሜዳ ፣ ቁርክ ፣ (የቁርክ አገር ሰው)
-ግ- ጀልባ እወንዝ ዳር ማሠር [አ'ሠረ]
moot
'ሙ:ት -ቅ- አ'ጠራጣሪ ፣ አ'ከራከሪ
-ግ- ለመ'ነጋገር ማቅረብ [አቀ'ረበ] (አንድ ጉዳ'ይ)
mop
'ሞፕ -ስ- ወለል መጥረጊያ ፣ ብት'ቶ (በን ጨት ላይ የታ'ሠረ)
mope
'መውፕ -ግ- ስላንድ አ'ከል ግ'ስላስል [አ'ሰ ላ'ሰለ]
moral
'ሞረል -ቅ- ጥሩ ፣ የተቀ'ጣ ፣ ግብረ ገ'ባዊ ፣ ባለ ምግባር
morale
መ'ራ:ል -ስ- ውስጣዊ ስ'ሜት (ስለ ድፍረት ፣ መ'ተማመን)
morals
'ሞረልዝ -ስ- ግብረ ገ'ብ'ነት
morality
መ'ራሊቲ -ስ- ግብረ ገ'ብ'ነት
morbid
'ሞ:ቢድ -ቅ- አእምሮው ያልተተነ'ከለ ፣ የታ'መመ ፣ በሰው ሥቃይ የ'ሚ'ደ'ሰት
more
'ሞ: -ቅ- ተጨ'ማሪ ፣ ይበልጥ
moreover
ሞ'ረውቭ -ተግ- ከ'ዚህ በላይ
morning
'ሞ:ኒንግ -ስ- ጧት ፣ ንጋት
morose
መ'ረውስ -ቅ- ጭፍግ'ግ ያለው ፣ ሊ'ደ'ሰት የ'ማይቻ ፣ የማይጠጻው ፣ አይጠጼ
morsel
'ሞ:ሰል -ስ- ቁ'ራሽ (ምግብ)
mortal
'ሞ:ተል -ቅ- መዋቲ
mortar
'ሞ:ተ -ስ- የተደባ'ለቀ ሲሚንቶ
military
-ስ- አ'ጻፍኔ (የጦር መ'ሣሪያ ዓይነት)
utensil
-ስ- መፋ'ጫ
mortgage
'ሞ:ጊጅ -ስ- ንብረትን ዋስ በማድረግ ገንዘብ መ'በደር
mortify
'ሞ:ቲፋይ -ግ- በሰው ፊት ማሳ'ፈር [አሳ'ፈረ]፣ ሰው ማሳ'ዘን [አሳ'ዘነ] ፤ ሰው'ነት በጾም በጸሎት ማድከም [አደ'ከመ]
mortuary
'ሞ:ትዩወሪ -ስ- ፈሳ እስኪ'ቀ'በር የ'ሚ'ቀ'መ ጥ'በት ቦታ (በሐኪም ቤት ግ'ቢ) ፣ የፈሳ ቤት
mosque
'ሞስክ -ስ- መስጊድ (የእስላሞ'ች ቤተ መቅ ደስ)
mosquito
ሞስ'ኪቶው -ስ- ቢምቢ ፣ የወባ ትን'ኝ
moss
'ሞስ -ስ- የደንጊያ ፣ የእንጨት ገበት (በደን ጊያ ፣ በእንጨት ወይን'ም በርጥብ ቦታ ላይ የ'ሚበቅል አረንጓዴ ወይን'ም ብጫ ተክል)
most
'መውስት -ቅ- የ'ሚበልጥ

mostly
'መውስትሊ -ተግ- ይበልጡን
moth
'ሞፒ -ስ- ብል ፣ ቋንቋን
mother
'መፐ -ስ- እ'ናት
mother-in-law
'መፐሪንሎ: -ስ- እማት (የባል ወይን'ም የሚ ስት እ'ናት)
motion
'መውሽን -ስ- እንቅስ'ቃሴ
motive
'መውቲቭ -ስ- የ'ሚያ'ነሣ'ሣ ምክንያት (አን ድ ነገር ለማድረግ)
motor
'መውተ -ስ- ሞቶር
motor-car
'መውተ'ካ: -ስ- መኪና ፣ አውቶሞቢል
mottled
'ሞተልድ -ቅ- ል'ዩ ል'ዩ ቀለም በገላው ላይ የጣለ'በት
motto
'ሞተው -ስ- አ'ጭር ም'ሳሌያዊ አ'ነጋገር (የ ጠባይን ሕ'ግጋት የ'ሚ'ና'ገር) ፣ ሕይወት የ'ሚ 'መ'ራ'በት ም'ሳሌ
mould
'ሞልድ -ግ- ቅርጸ መስጠት [ሰ'ጠ] ፣ መልክ መስጠት [ሰ'ጠ]
moult
'ሞልት -ግ- የላባ መርገፍ [ረ'ገፈ] (አዲስ ለማ ብቀል)
mound
'ማውንድ -ስ- ት'ንሽ የደንጊያ ፣ የእፈር ቁ'ልል
mount
'ማውንት -ግ- መውጣት [ወ'ጣ] (አንድ ነገር ላይ)
mountain
'ማውንቴን -ስ- ተራራ
mountainous
'ማውንተነስ -ቅ- ተራራ'ማ
mourn
'ሞን -ግ- ማልቀስ [አለ'ቀሰ] (ለሞተ ሰው)
mourner
'ሞ:ነ -ስ- አልቃሽ
mournful
'ሞ:ንፉል -ቅ- ያ'ዘነ
mourning
'ሞ:ኒንግ -ስ- ልቅሶ ፣ ለቅሶ
mouse
'ማውስ -ስ- አይጥ
mousetrap
'ማውስትራፕ -ስ- ያይጥ ወጥመድ
moustache
መስ'ታ:ሽ -ስ- ፊዝ
mouth
'ማውዅ -ስ- አፍ
mouthful
'ማውዅፉል -ስ- አፍ ሙሉ
mouthpiece
'ማውዅፒይስ -ስ- ዋቢ ፣ ጠበቃ ፣ የሌላውን ሐሳብ የ'ሚገልጽ ሰው ፣ ጋዜጣ ወዘተመደአፍ የ'ሚ'ደ'ረገው የመዚቃ መሣሪያ (ዋሽንት) ወዘተ ክፍል
movable
'መ:ቨበል -ቅ- የ'ሚንቀሳ'ቀስ
move
'መ:ቭ -ግ- ማንቀሳቀስ [አንቀሳ'ቀሰ]፣ መንቀ ሳቀስ [ተንቀሳ'ቀሰ]
movement
'መ:ቭመንት -ስ- እንቅስ'ቃሴ
moving
'መ:ቪንግ -ቅ- ተንቀሳቃሽ
mow
'መው -ግ- ማጨድ [አ'ጨደ]
much
'መች -ቅ- ብዙ ፣ አ'ያሌ
muck
'መክ -ስ- ቆሻሻ ፣ ጉድፍ
mucus
'ምዩከስ -ስ- ንፍጥ
mud
'መድ -ስ- ጭቃ
muddle
'መደል -ስ- ሥርዓት የሌ'ለው ፣ ዝብርቅርቅ ነገር

muddy
ˈመጺ ቅ- ጭቃ'ማ

muffin
ˈመፊን ብ- ቂ'ጣ (ጠቃጠቆ ያ'ል'በት)

muffle
ˈመፈል ግ- ማ'ፈን [አ'ፈነ] ፣ ማድከም [አደ'ከመ] (ድምፅ) ፣ መ'ሸፋፈን [ተሸፋ'ፈነ]

muffler
ˈመፍለ ብ- ሻል (ወፍራም)

mug
ˈመግ ብ- ኩ'ባ'ያ

mule
ˈምዩል ብ- በቅሎ

multiple
ˈመልቲፐል ቅ- ል'ዩ ል'ዩ ከፍል ያ'ለው ፣ ብዙ

multiplication
መልቲፐሊ'ኬይሸን ብ- ማብዛት ፣ ማ'ባዛት

multiply
ˈመልቲፕላይ ግ- ማብዛት [አበ'ዛ] ፣ ማ'ባዛት [አ'ባ'ዛ]

mumble
ˈመምበል ግ- ማንብነብ [አነበ'ነበ] ፣ ንግ'ግርን ግልጽ አድርጎ አለመ'ናገር [-ተና'ገረ]

mummy
ˈመሚ ብ- በመድኃኒት እንዳይፈርስ'ና እንዳይበሰ'ብስ የተደ'ረገ አስከሬን

mumps
ˈመምፕስ ብ- ጆሮ ደ'ግፍ

munch
ˈመንች ግ- አጥብቆ ማ'ላመጥ [አ'ላ'መጠ] ፣ ማ'ኘክ [አ'ኘከ]

municipal
ምዩ'ኒሲፐል ቅ- ከከተማ አስተዳደር ጋር ግ'ን'ኙነት ያ'ለው

municipality
ምዩኒሲ'ፓሊቲ ብ- ማ'ዘጋጃ ቤት

munitions
ምዩ'ኒሽንዝ ብ- የጦር መ'ሣሪያ መደ'ብር (የተ'ይት ወዘተ)

mural
ምዩረል ብ- እግድግ'ዳ ላይ የተሣለ ሥዕል ቅ- የግድግ'ዳ

murder
ˈመ፡ደ ግ- መግደል [ገ'ደለ] (ሰው) ብ- ነፍስ ማ'ጥፋ

murderer
ˈመ፡ደረ ብ- ነፍሰ ገዳይ

murky
ˈመ፡ኪ ቅ- ጥቁር ፣ ያልጠ'ራ ፣ የደበ'ዘዘ

murmur
ˈመ፡መ ግ- ማጉረምረም [አጉረመ'ረመ]

muscle
ˈመሰል ብ- ሙንጭ

muscular
ˈመስከዩለ ቅ- ሙንጭ'ማ ፣ የሙንጭ

museum
መዩ'ዚየም ብ- ቤተ መዘ'ክር (ታሪካዊ ቅርሶች ና'ሚ'ቀ'መጡ'በት'ና ለሕዝብ የ'ሚ'ታ'ዩ'በት ቤት)

mushroom
ˈመሹሩም ብ- እንጉዳይ

music
ምዩዚክ ብ- ሙዚቃ

musket
ˈመስኩት ብ- መስኪ'ቶ (ጠመንጃ)

muslim
ˈመዝሊም ቅ- እስላም

muslin
ˈመሣሊን ብ- ቀ'ጭን የተተ ጨርቅ

must
ˈመስት ግ- መ'ገባት [ተገ'ባ]

mustard
ˈመስተድ ብ- ሰናፍ'ጭ

muster
ˈመስተ ግ- መሰብሰብ [ሰበ'ሰበ] (ወ'ታ'ደር ወዘተ ለቁ'ጥር)

musty
ˈመስቲ ቅ- የሸ'ገተ ፣ የሻ'ጋታ ሽ'ታ ያ'ለው

mutation
ምዩ'ቴይሽን ብ- ለውጥ ፣ ል'ዩ'ነት

mute
ምዩት ቅ- ድዳ

mutilate
ምዩ'ቲሌይት ግ- የሰው አካል መቆራረጥ [ቆራ'ረጠ] አካለ ስንኩል ማድረግ [አደ'ረገ]

mutiny
ምዩ'ቲኒ ብ- ብጥ'ብጥ ፣ አድማ (የመርከብ ሞ'ች ፣ የጦር ሠራዊት)

mutter
ˈመተ ግ- ማንብነብ [አነበ'ነበ] ፣ ማጉራም ረም [አጉረመ'ረመ]

mutton
ˈመተን ብ- የበግ ሥጋ

mutual
ምˈቹ'ዬወል ቅ- የወል ፣ የጋራ ፣ የርስበርስ

muzzle
ˈመዘል ብ- አፍ'ና አፍንጫ (የው'ሻ ፣ የቀ በር ወዘተ) ፣ አፈ መዝ (የጠመንጃ)

my
ˈማይ ተስ- የኔ

myself
ማይ'ሰልፍ ተስ- (እኔ) ራሴ

mysterious
ሚስ'ቲሪየስ ቅ- ምስጢራዊ ፣ የተሸ'ሸገ ፣ መፍ ትሔ የሌ'ለው ሊ'ረ'ዱት የ'ማይ'ቻል

mystery
ˈሚስተሪ ብ- ምስጢር ፣ ድብቅ ፣ ሊ'ረ'ዱት የማ'ይቻል ነገር

myth
ˈሚዝ ብ- የጥንት ታሪክ ፣ አፈ ታሪክ

mythical
ˈሚዲከል ቅ- ል'ብ ወ'ለድ'ነት ያ'ለው (የጥ ንት ታሪክ) ፣ አፈታሪካዊ

N

nag
ˈናግ ግ- መጨቅጨቅ [ጨቀ'ጨቀ] ፣ መነዘ ነዝ [ነዘ'ነዘ]

nail
ˈኔይል ብ- ምስማር ፣ ሚስማር ፣ ችንካር
finger- ብ- ጥፍር (የእ'ጅ)

naive
ና'ይቭ ቅ- ቂላቂል ፣ ጅል ፣ ሞ'ኝ ፣ ደ'ጋጆ'ማ

naked
ˈኔይከድ ቅ- ራቁት ፣ የተራ'ቆተ ፣ ዕርቃኑን ያለ ፤ ያልተሸ'ፈነ

name
ˈኔይም ብ- ስም

namely
ˈኔይምሊ ተግ- ማለት ፣ ይኸው'ም

namesake
ˈኔይምሴይክ ክ- ሞክሼ

nanny
ˈናኒ ብ- ልጅ እሳ'ዳጊ ፣ ምግዚት (ሴት)

nanny-goat
ˈናኒጎት ብ- ሴት ፍ'የል

nap
ˈናፕ ₍ብ- ት'ንሽ እንቅልፍ ፣ ሸለብታ

nape
ˈኔይፕ ብ- ማጅራት

napkin
ˈናፕኪን ብ- የገበታ ፎጣ ፣ አፍ መጥረጊያ ፎጣ

narcotic
ና'ኮቲክ ቅ- የ'ሚያደነ'ዝዝ ፣ የ'ሚያሰተ'ኛ መድኃኒት

narrate
ነ'ሬይት ግ- ታሪክ ማውራት [አወ'ራ] ፣ መ ተ'ረክ [ተ'ረከ]

narration
ነ'ሬይሽን ብ- ታሪክ ፣ መተ'ረክ (ያንድ እገር ወይ'ንም መንግሥት)

narrative
ˈናሪቲቭ ብ- ታሪክ

narrator
ነ'ሬይተ ብ- አውሪ ፣ ተረት ተ'ራች

narrow
ˈናረው ቅ- ጠ'ባብ

nasal
ˈኔይዘል ቅ- የአፍንጫ

niggard
ንፇድ ቅ- ሥሥታም ፣ ንብጋ'ባ
nigger
ንኀገ -ስ- ጥቁር በኍ'ማ (ቀለም) ፣ ጠጽራ (የጥ ቁ'ቻ መ'ጠሪያ)
night
ን'ናይት -ስ- ሌሊት ፣ ጭ'ለማ
nightcap
ን'ናይትካፕ -ስ- የመ'ኝታ ቆብ ፤ ከመ'ኝታ በፊት የ'ሚ'ጠ'ጣ መጠ'ጥ
nightfall
ን'ናይትፎ:ል -ስ- ም'ሽት
nightmare
ን'ናይትሜየ -ስ- ቅዠት
nil
ን'ኤል ቅ- ምን'ም ፣ ዜሮ
nimble
ን'ኽምበል ቅ- ፈ'ጣን ፣ ንቁ (በቶሱ የ'ሚገ ባው)
nine
ን'ናይን ቅ- ዘጠ'ኝ
nineteen
ናይን'ቲይን ቅ- ዐሥራ ዘጠ'ኝ
nineteenth
ናይን'ቲንፀ ቅ- ዐሥራ ዘጠነ'ኛ
ninetieth
ን'ናይንቲየፀ ቅ- ዘጠና'ኛ
ninth
ን'ናይንፀ ቅ- ዘጠነ'ኛ
ninety
ን'ናይንቲ ቅ- ዘጠና
nip
ን'ኒፕ -ግ- መቆንጠጥ [ቆነ'ጠጠ] ፤ መንከስ [ነ'ከሰ]
nipple
ን'ኒፐል -ስ- የጡት እፍንጫ ፣ የጡት ጫፍ
no
ን'ነው ተ- አይደ'ለም ፣ የ'ለም
nobility
ነ'ቢሊቲ -ስ- ባለክብር'ነት ፤ መሳፍንት
noble
ን'ውበል ቅ- የተከ'በረ ፣ ንዑዝ ፣ የ'ሚ'ደ'ነቅ፣ ከ'ፍ ያለ ማዕረግ ያ'ለው
nobody
ን'ነውቦዲ ቅ- ማን'ም
nod
ን'ኖድ ቅ- ራስ መነቅነቅ [ነቀ'ነቀ] (ለመስ ማማት ፤ ሰላምታ ለመስጠት)
noise
ን'ኖይዝ -ስ- ዋከታ
nominal
ን'ኖሚነል ቅ- ለስሙ ያህል ፣ በጣም ት'ንሽ
nominate
ን'ኖሚኔይት ቅ- መሰ'የም [ሰ'የመ]
nominative
ን'ኖሚነቲቭ ቅ- ሳቢ (በሰዋስው)
nominee
ኖሚ'ኒይ -ስ- በምርጫ ላይ የ'ሚደ'ግፉት ፣ ለመ'መረጥ የታ'ጨ
nonchalant
ን'ናንሸለንት ቅ- የ'ማይን'ደው ፣ ግ'ዴ'ለሽ ፣ ስ'ሜቱ የቀዘ'ቀዘ
non-commital
ኖንከ'ሚተል ቅ- እ'ሺ'ም እም'ቢ'ም የ'ማ ይል ፣ አስተያየቱን የ'ሚሸ'ሽግ ፣ ከማ'ን'ኛው ም ወገን ያልሆነ (በተል)
none
ን'ነን ተ- ማን'ም
nonsense
ን'ናንሰንስ -ስ- ትርክ ምርኪ ፣ የ'ማይረባ
nook
ን'ኑክ -ስ- ረ'ቅ ያለ ቦታ (ገለ'ል ብለው የ'ሚ'ቀ 'መጡ'በት)
noon
ን'ኑን -ስ- ቀትር
noose
ን'ኑስ -ስ- ሽምቀ'ቆ (የሰው መስቀያ)
nor
ን'ኖ: -መማ- ወይ'ም ፣ ወይን'ም
normal
ን'ኖ:መል ቅ- የተለመ'ደ ፤ ያለመ'መው ፣ ያል ተበላ'ሸ (ለእእምሮ)
north
ን'ኖ:ፀ -ስ- ሰሜን
northern
ን'ኖ:ዘን ቅ- ሰሜናዊ

nose
ን'ነውዝ -ስ- እፍንጫ
nosegay
ን'ነውዝጌይ -ስ- ያበባ እ'ቅፍ
nostalgia
ናስ'ታልጀየ -ስ- ያገር ናፍቆት ፣ ያ'ለፈ ሁናቴ ት'ዝታ
nostril
ን'ናስትረል -ስ- ያፍንጫ ቀዳዳ
not
ን'ኖት -ተ- አይደ'ለም
notable
ን'ነውተበል ቅ- የታ'ወቀ
notch
ን'ኖች -ስ- የተፋሪ ነገር (በሰንጠ) ፣ ስርጉዳት
note
ን'ነውት -ስ- ማስታወሻ (አ'ጭር ጽሑፍ) -ግ- ጠንቅቆ ማስተዋል [አስተዋለ]
note-book
ን'ነውትቡክ -ስ- ማስታወሻ መጻፊያ ደብተር
noted
ን'ነውተድ ቅ- የታ'ወቀ ፣ ዝ'ነ'ኛ
notepaper
ን'ነውትፔይፐ -ስ- ረቂት ማውጫ ወረቀት ፣ ደብዳ'ቤ መጻፊያ ወረቀት
nothing
ን'ሲንግ -ተግ- ምን'ም
notice
ን'ነውቲስ -ግ- ማስተዋል [አስተዋለ] -ስ- ማስታወቂያ
noticeable
ን'ነውቲሰበል ቅ- በቀ'ላሉ የ'ሚ'ታ'ይ ፣ ጉ ልህ
notify
ን'ነውቲፋይ -ግ- ማመልከት [አመል'ከተ] ፣ ማስታወቅ [አስታ'ወቀ]
notion
ን'ነውሽን -ስ- ሐ'ሳብ ፣ አስተያየት
notoriety
ነውተ'ሪየቲ -ስ- መጥፎ ዝ'ና
notorious
ነ'ቶሪየስ ቅ- በመጥፎ ተግባር የታ'ወቀ
notwithstanding
ኖትዊስ'ታንዲንግ -ተግ- ቢሆን'ም ፣ ሆኖ'ም

nought
ን'ኖት -ስ- ምን'ም ነገር ፣ ዜሮ
noun
ን'ናውን -ስ- ስም ፣ ነ'ባር ፣ ዘር
nourish
ን'ነሪሽ -ግ- መመ'ገብ [መ'ገበ]
novel
ን'ኖቭል -ስ- ረ'ጅም ል'ብ ወለ'ድ ታሪክ (በስ 'ድ ጽሑፍ የተጻፈ) ቅ- አ'ዲስ'ና አስገ'ራሚ
novelty
ን'ኖቭልቲ -ስ- አ'ዲስ'ነት
November
ን'ኼምበ -ስ- ኅዳር
novice
ን'ኖቪስ ቅ- ልምድ የሌ'ለው ፣ ጀ'ማሪ -ስ- በተባሕትም ብዙ ጊዜ ያልቆ'የ(ች)
now
ን'ናው ተግ- አሁን
nowadays
ን'ናወዲይዝ ተግ- ባሁኑ ጊዜ ፣ ባሁኑ ዘመን
nowhere
ን'ነወየ ተግ- የት'ም
noxious
ን'ናክሸስ ቅ- መርዛም ፣ የ'ሚጎዳ ፣ ጎጂ
nozzle
ን'ኖዘል -ስ- የቧ'ጌ መጨ'ረሻ (ውኃ የ'ሚፈ 'ስ'በት) ፣ የቧ'ጌ አፈ መ'ዝ
nucleus
ን'የክለየስ -ስ- የአቶም እምብርት ፣ ያንድ ነገር መሠረ (እምብር'ቱ)
nude
ን'ዩ:ድ ቅ- ራቁት
nudge
ን'ጅ -ግ- መኮ'ንተል [ኮን'ተለ] ፣ ብክርን ን'ስም ማድረግ [አደ'ረገ]
nudity
ን'ዩ:ዲቲ -ስ- ራቁት'ነት
nuisance
ን'ዩሰንስ -ስ- አ'ዋኪ ፣ በጥባጭ ሰው
null
ን'ል ቅ- የጋ ዜሰ

numb
ˀነም -ቅ- የደነˀዘዘ
-ግ- ማደንዘዝ [አደነˀዘዘ]
number
ˀነምበ -ስ- ቁጥር
numeral
ንˀየመረል -ስ- አኀዝ
numerical
ንየˀሚሪከል -ቅ- የቁጥር
numerous
ንˀየመረስ -ቅ- ብዙ ፣ አˀያሌ
nun
ˀነን -ስ- መነኩሲት
nunnery
ˀነነሪ -ስ- የመነኩሳዩያት ገዳም
nuptial
ˀነፕሸል -ቅ- የሠርግ ፣ የጋብ'ቻ
nurse
ˀነስ -ግ- ማስታመም [አስታˀመመ]
nursemaid
ˀነሰሜይድ -ስ- ልጅ አሳ'ዳጊ (ሴት)
nurture
ˀነቸ -ግ- ማሳ'ደግ [አሳ'ደገ] (ለሕፃን)
nut
ˀነት -ስ- ለውዝ
nutriment
ንˀዩትሪመንት -ስ- ምግብ (ለጤና ተስማሚ)
nutrition
ንዩትˀሪሸን -ስ- ምግብ
nutshell
ˀነትሼል -ስ- የለውዝ ቅር'ፊት
nutty
ˀነቲ -ቅ- የለውዝ ጣዕም ያˀለው
nuzzle
ˀነዝል -ግ- ባፍንጫ መˀታከክ [ታˀከከ] (በተ ለˀይ ለእንሰሳት)

O

oaf
ˀኦውፍ -ቅ- ባለጌ ፣ ያልሠለጠነ ፣ ጅላጅል ፣ ሞኝ ሞኝ
oak
ˀኦውክ -ስ- ዓˀሎጥ (የዛፍ ዓይነት)
oar
ˀኦ፡ -ስ- መቅዘፊያ
oasis
ˀኦሄይሲስ -ስ- የምድረ በዳ ኩሬ ውኃ
oath
ˀኦውዟ -ስ- መሐላ ፣ ስድብ ፣ እርግማን
oatmeal
ˀኦውትሚይል -ስ- የአˀዝ ዱቄት
oats
ˀኦውትስ -ስ- አˀዝ
obdurate
ˀኦብጆሬት -ቅ- ችˀኮ ፣ መንጆˀካ
obedient
ˀኦቢይዲየንት -ቅ- ታˀዛዥ
obeisance
ኦˀቤይሰንስ -ስ- በአክብሮት አˀጅ መንሣት ፣ መˀታዘዝ
obelisk
ˀኦበሊስክ -ስ- ከደንጊያ ተጠርቦ የተሠˀራ አራˀት ማዕዘን ያˀለው ሐውልት
obese
ኦˀቢይስ -ቅ- በጣም ወፍራም (ለሰው)
obesity
ኦˀቢይሲቲ -ስ- ያለመጠን ውፍረት
obey
ˀዖቤይ -ግ- መˀታዘዝ [ታˀዘዘ]
obituary
ˀዖቢቹሪ -ስ- የሙት ታሪክ (በጋዜጣ መጠተ)
object
ˀኦብጀክት -ግ- መˀቃወም [ተቃˀወመ]
object
ˀኦብጀክት -ስ- ነገር ፣ ዕላማ

objection
ˀኦብˀጀክሸን -ስ- መˀቃወም
objectionable
ˀኦብˀጀክሸነብል -ቅ- የˀማያስደˀስት ፣ የˀሚ ˀቃˀወሙት
objective
ˀኦብˀጀክቲቭ -ስ- ግብ ፣ ዕላማ
obligation
ኦብሊˀጌሽን -ስ- ግˀዴታ
obligatory
ˀኦብሊጌቶሪ -ቅ- አስገዳጅ ፣ ግˀዴታዊ
oblige
ˀኦብላይጅ -ግ- ውለታ መዋል [ዋለ] ፣ ማስገ ˀደድ [አስገˀደደ]
oblique
ˀኦብሊይክ -ቅ- ሠˀያፍ (መሥመር) ፣ ቀˀጥ ተˀኝ ያልሆነ ፣ ዘንበˀል ያለ ፣ ያዘˀመመ
obliterate
ˀኦብሊተሬይት -ግ- መደምሰስ [ደመˀሰሰ] ፣ መፋቅ [ፋቀ]
obliteration
ˀኦብሊተˀሬይሽን -ስ- መደምሰስ ፣ ድምሰሳ ፣ መፋቅ
oblivion
ˀኦብˀሊቪየን -ስ- መˀረሳት ፣ መˀዘንጋት
oblivious
ˀኦብˀሊቪየስ -ቅ- የረˀሳ ፣ የዘነˀጋ ፣ ዝንጉ
oblong
ˀኦብሎንግ -ቅ- አራት ማዕዘን (ሁለˀት ጎˀኑ በርዝመት የˀሚˀመሳˀሰል) ፣ ሞላላ
obnoxious
ˀኦብˀኖክሸስ -ቅ- የˀሚያስጠˀላ ፣ ደˀስ የˀማያ ˀሰˀኝ (ለጠባይ)
obscene
ˀኦብˀሲይን -ቅ- ባለጌ ፣ አስቀˀያሚ ፣ ስለፈቃደ ሥጋ በይፋ የˀሚˀናˀገር ፣ ነውር የˀማያውቅ
obscenity
ˀኦብˀሴኑቲ -ስ- ብልግና ፣ አስቀˀያሚˀነት ፣ ነውር አለማወቅ
obscure
ˀኦብስክˀዩወ -ቅ- ግልጽ ያልሆነ ፣ የተሠወረ
obsequious
ˀኦብˀሲይክዊየስ -ቅ- ተለማማጭ
observant
ˀኦብˀዘ፡ቨንት -ስ- ተመልካች ፣ አስተዋይ ፣ ታˀዛቢ
observation
ኦብዘˀቬይሸን -ስ- መˀመልከት ፣ ማስተዋል
observe
ˀኦብˀዘ፡ቭ -ግ- መˀመልከት [ተመለˀከተ] ፣ ማስ ተዋል [አስተዋለ]
observer
ˀኦብˀዘ፡ቨ -ስ- ተመልካች ፣ ታˀዛቢ
obsession
ˀኦብˀሴሽን -ስ- ሐሳብን መˀማረክ (ከፍርሃት ፣ ትክክል ላልሆነ ሐሳብ የተነˀሣ)
obsolete
ˀኦብሰሊይት -ቅ- ዘመናዊ ያልሆነ ፣ ያረጀ ፣ አሥራ ላይ የˀማይውል
obstacle
ˀኦብስተክል -ስ- መሰናክል ፣ ዕንቅፋት
obstinate
ˀኦብስቲነት -ቅ- ችˀኮ ፣ በአንድ ሐሳብ ችˀክ የˀሚል
obstruct
ኦብስትˀረክት -ግ- ማˀደናቀፍ [አˀደናˀቀፈ] ፣ እንቅፋት መሆን [ሆነ]
obtain
ኦብˀቴይን -ግ- ማግኘት [አገˀኘ]
obtrusive
ኦብትˀሩዚቭ -ቅ- ልˀታይ ባይ ፣ ሥˀሉተ
obtuse
ኦብˀትዮስ -ቅ- ፈዛዛ ፣ ደˀደብ ፣ ቆሎ የˀማይ ጣባው
obverse
ˀኦብቨስ -ስ- የንˀሥ መልክ ፣ ዘውድ ያˀለበት የመሐˀሉት መልክ ፣ ዘውድ (የመሐˀሉቅ)
obvious
ˀኦብቪየስ -ቅ- ግልጽ
occasion
ኦˀኬይዠን -ስ- ጊዜ (ትˀልቅ) ፣ በዐል
occasionally
ኦˀኬይዠንሊ -ተግ- አልፎ አልፎ
occult
አˀከልት -ቅ- የአስማት
occupant
ˀኦክዩፐንት -ስ- ነዋሪ ፣ ያˀዥ (ሥፍራ)

occupation
አክዖፔይሽን -ስ- ተግባር ፣ ሥራ
occupy
'አክፂፓይ -ግ- መያዝ [ያዘ] ፤ መውረር [ወ'ረረ] (ላገር)
occur
አ'ከ፡ -ግ- መሆን [ሆነ] ፤ መድረስ [ደ'ረሰ] (ለነገር) ፥ ት'ዝ ማለት [አለ]
ocean
'ኧውሽን -ስ- ውቅያኖስ
octagon
'ኦክተጎን -ስ- ስ'ምንት ጎ'ን ያ'ለው ቅርፅ
October
ኦክ'ተውበ -ስ- ጥቅምት
oculist
'ኦክዩሊስት -ስ- ያይን ሐኪም
odd
'ኦድ -ቅ- ለሁለ'ት የ'ማይ'ከ'ፈል (ለሒሳብ) ፣ ጥንድ ያልሆነ ፤ ያልተለ'መደ ፣ እንግዳ (ለሁናቴ)
oddment
ኦድመንት -ስ- ርዝ'ራዥ ፣ ቁርጥራጭ
odds
'ኦድዝ -ስ- ል'ዩ'ነት ፣ አለመ'መጣጠን ፤ ዕድል (የጥሩ ወይ'ንም የመጥፎ)
ode
'ኧውድ -ስ- ረዘ'ም ያለ ግጥም (ረጃጅም'ና አጫ'ጭር ስን'ኞች ያ'ሉት)
odious
'ኧውዲየስ -ቅ- የ'ሚ'ጠ'ላ
odour
'ኧውደ -ስ- ሽ'ታ ፣ መዓዛ
of
'ኦቭ -መዋ- የ . . .
off
'ኦፍ -ተግ- ወዲያ ፣ ወደው'ጭ
offal
'ኦፈል -ስ- ሆድቃ (የእንስሳት)፤ ቁሻሻ ፣ ው'ጭ
offence
ኦ'ፈንስ -ስ- ሕ'ግ መጣስ
offend
ኦ'ፈንድ -ስ- ግስቀ'የም [አስቀ'የመ] ፣ መስደብ [ሰ'ደበ]
offensive
ኦ'ፈንሲቭ -ቅ- አ'ናዳጅ ፣ አሳ'ዛኝ ፣ አስቀ'ያሚ
offer
'ኦፈ -ግ- ለስጠታ ማቅረብ [አቀ'ረበ] ፤ ለመ ሸጥ ማስማማት [አስማ'ማ] ፤ መሥዋዕት ማቅረብ [አቀ'ረበ]
offering
'ኦፈሪንግ -ስ- መሥዋዕት
alms
-ስ- ለምጽዋት የወ'ጣ ገንዘብ
offhand
አፍ'ሀንድ -ቅ- ያለመ'ዘጋጀት ፣ ላያ'ስብ የድ ፍረት ንግግር የ'ሚያደርግ
careless
-ቅ- ግ'ዴ'ለሽ ፣ የ'ማይ'ጠ'ቀቅ
office
'ኦፊስ -ስ- ሥራ ፣ ተግባር
building
-ስ- ቢሮ ፣ መሥሪያ ቤት
officer
'ኦፊሰ -ስ- ባለ ሥልጣን
military
-ስ- የጦር መኰ'ንን
official
ኦ'ፊሸል -ስ- ሹም ፣ ባለሥልጣን
-ቅ- ይፋ ፣ የመንግሥት
offshoot
'ኦፍሹ፡ት -ስ- ቅርንጫፍ
offspring
'ኦፍስፕሪንግ -ስ- ልጆ'ች
often
'ኦፈን -ተግ- ሁልጊዜ ፣ ዘወትር
Oh
'ኧው -ቃለ- እንዴ! ወይጉድ!
oil
'ኦይል -ስ- ዘይት
oilcan
'ኦይልካን -ስ- የዘይት ማንቆርቆርያ ቆርቆ'ር (ባለጉት)
oilcloth
'ኦይልክሎ፲ -ስ- ውሃ የማይዘልቀው ጨርቅ
oily
'ኦይሊ -ቅ- በቅባት የተበ'ከለ

ointment
'ኦይንትመንት -ስ- ቅባት
old
'ኦልድ -ቅ- እርጌ ፣ ሽማግ'ሌ
old-fashioned
ኦልድ'ፋሽን'ድ -ቅ- ዘመናዊ ያልሆነ ፣ ጊዜ ያ'ለፈ'በት ፣ ባህልን ተከ'ታይ
olive
'ኦሊቭ -ስ- ወይራ ፤ ወደ ብጫ'ነት ያዘነ'በለ አረንጓዴ ቀለም
omen
'ኧውመን -ስ- ጎ'ድ ፣ ምል'ክት (መጪውን ውናቴ የ'ሚያሳ'ይ)
ominous
'ኦሚነስ -ቅ- ;ደጋ ሊያመጣ የ'ሚችል
omission
ኦ'ሚሽን -ስ- መግደፍ ፣ ማድፈት
omit
ኦ'ሚት -ግ- መተው [ተወ] ፤ መግደፍ [ገ'ደፈ]
omnibus
'ኦምኒበስ -ስ- አውቶቡስ
ominipotent
ኦም'ኒፐተተንት -ቅ- ሁ'ሉን የ'ሚችል ፣ ከሃሌ ሉያ (ለእግዚአብሔር)
omniscient
ኦም'ኒሲየንት -ቅ- ሁ'ሉን የ'ሚያውቅ (ለእግ ዚአብሔር)
on
'ኦን -መዋ- በ . . . ላይ ፣ በ
once
'ወንስ -ተግ- አንድ ጊዜ ፣ አንዲት ጊዜ
one
'ወን -ቅ- አንድ ፣ አንዲት
onerous
'ኦነረስ -ቅ- አስቸ'ጋሪ ፣ አ'ዋኪ (ለሥራ)
oneself
ወን'ሰልፍ -ተስ- ራስ
onion
'ኦንየን -ስ- ሽንኩርት
onlooker
'ኦንሉከ -ስ- ተመልካች
only
'ኧውንሊ -ቅ- ብ'ቻ ፣ የተለ'የ ፣ መ'ሰል የሌ 'ለው
onslaught
'ኦንስሎ፡ት -ስ- ከ'ባድ ማጥቃያ (ለጠላት)
onus
'ኧውነስ -ስ- ኀላፊ'ነት ፣ ሸክም
onward
'ኦንወድ -ተግ- ወደፊት
onyx
'ኦኒክስ -ስ- መረግድ
ooze
'ኡ፡ዝ -ግ- ማገ'ት [አ'ዝ]
opaque
ኦ'ፔይክ -ቅ- በውስጡ የ'ማያሳ'ይ ፣ ብርሃን የ'ማያስገ'ባ ፣ ጥቅጥቅ ያለ
open
'ኧውፐን -ግ- መክፈት [ከ'ፈተ]
opening
'ኧውፕኒንግ -ስ- ቀዳዳ
operate
'ኦፐሬይት -ግ- መሥራት [ሠ'ራ] ፤ ማ'ሠ'ራት [አ'ሠ'ራ]
-on
-ግ- መቅደድ [ቀ'ደደ] (ሕ'ክም'ና)
operation
ኦፐ'ሬይሽን -ስ- ሥራ
medical
-ስ- ኦፕራሲዮን ፣ ሰው'ነትን ለሀ'ክም'ና መቅደድ
operative
'ኦፐሪቲቭ -ቅ- ሠሪ
-ስ- ሠ'ራተ'ኛ (ይበልጡን የፋብሪካ ፣ ሜካኒክ)
opinion
ኦ'ፒንየን -ስ- አስተያየት ፣ ፍርድ ፣ እምነት ፣ ግ'ምት
opponent
ኦ'ፖውነንት -ስ- ጠላት ፣ ተቃዋሚ ፣ ባላንጣ
opportune
'ኦፐቹ፡ን -ቅ- ተስማሚ
opportunity
ኦፐ'ቹ፡ኒቲ -ስ- ም'ቹ ጊዜ (ሥራ ለመሥራት)
oppose
ኦ'ፖውዝ -ግ- መ'ቃወም [ተቃ'ወመ]

opposite
'አፐሲት -ቅ- ፊት ለፊት የሆነ ፣ ተቃራኒ ፣ የ'ማይስማማ ፣ አቅጣ'ጫው የተለያየ

opposition
አፐ'ዚሽን -ስ- መ'ቃወም ፣ ተቃቀሚ ክፍል

oppress
ኧፕ'ሬስ -ግ- መጨ'ቆን [ጨ'ቆነ]

oppressive
ኧፕ'ሬሲቭ -ቅ- ጨ'ቋኝ

oppressor
ኧፕ'ሬሰ -ስ- ጨ'ቋኝ (ሰው)

optical
'ኦፕቲክል -ቅ- የዓይን

optician
ኦፕ'ቲሽን -ስ- መነ'ጥር ሠ'ራተ'ኛ (መነ'ጽር ሠ ራተ'ኛ)

optimist
'ኦፕቲሚስት -ስ- በጥሩ ተ'ምኔት የ'ሚያምን ሰው ፣ ሁኔቱም'ችን ሁሉ በቅን የ'ሚያይ ሰው

option
'ኦፕሽን -ስ- የፈ'ስትኩን የመምረጥ መብት

or
'ኦ፡ -መ- ወይን'ም ፣ ወይ'ም

oral
'ኦረል -ቅ- የቃል ፣ የአፍ

orange
'ኦረንጅ -ስ- ብርቱቱን

oration
ኦ'ሬይሽን -ስ- ንግ'ግር (በሕዝብ ፊት)

orator
'ኦረተ -ስ- ንግ'ግር ወዋቂ ፣ እንይበተ ርቱኣ ፣ ዋሩ ተ'ናጋሪ

oratory
'ኦረተሪ -ስ- ንግ'ግር የማድረግ ሀብት

orb
'ኦ፡ብ -ስ- ሉል (ንጉ፥ሥ በ'ጂ የ'ሚይዘው ፣ መስቀል ያ'ለ'በት) ፣ ከ'ዛ ነገር (ም'ሳሌ ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ከከብ ፣ ምድር)

orbit
'ኦ፡ቢት -ግ- እንደን ነገር መዞር [ዞረ] (በፈ,ለክ)
-ስ- እንድ ፈለክ በሰላው ዙሪያ የ'ሚያ ደርገው መዞር ፣ ዑደት

orchard
'ኦቾድ -ስ- የፍሬ'ፍሬ ተክል ቦታ

orchestra
'ኦ፡ከስትሪ -ስ- የሙዚቃ ጓ'ድ

ordain
ኦ፡ዴይን -ግ- ከህነት መስጠት [ሰ'ጠ] ፣ መክነ [ክነ] ፣ ማዘዝ [አ'ዘዘ]

ordeal
ኦ፡ዲይል -ስ- አ'ዋኪ የኑብዝ'ና መል'ዚያ ፈተና

order
'ኦ፡ደ -ግ- ማዘዝ [አ'ዘዘ]
instruction
-ስ- ሥርዓት
sequence
-ስ- ቅደም ተከ'ተል

orderly
'ኦ፡ደሊ -ቅ- ጥሩ ሥርዓት ያ'ለው ፣ የተሽ'ከረ፣ የተ'ሰ'ተረ
servant
-ስ- የሆስፒታል ተ'ላላኪ ፣ ያንድ መኩ ን'ን ተ'ላላኪ

ordinance
'ኦ፡ዲንስ -ስ- ትእዛዝ ፣ ሕ'ግ ፣ ወዋጅ ፣ ሃይማ ኖታዊ ክብረ በዓል

ordinary
'ኦ፡ደንሪ -ቅ- ተራ ፣ የተለ'መደ ፣ መና'ኛ

ordination
ኦ፡ዲ'ኔይሽን -ስ- መ'ሾም ፣ መሾም (መንፈ ሳዊ)

ordnance
'ኦ፡ደንስ -ስ- መድፈ'ኛ ክፍል ፣ የጦር መ'ሣ ሪያ'ና የምግብ መደ'ብር (የወ'ታ'ደር)

ore
'ኦ፡ -ስ- የብረታ ብረት አፈር (ገና ያልነ'ጠረ)

organ
'ኦ፡ጋን -ስ- የሰው'ነት ክፍል
musical
-ስ- አር,ጋኖን (እንደ ፒያኖ ያ'ለ የሙዚቃ መ'ሣሪያ)

organic
ኦ፡'ጋኒክ -ቅ- የሰው'ነት ፡ የእክል ፣ ሕይወት ያ'ለው

organization
ኦ፡ጋናይ'ዜሽን -ስ- ደር'ጅት

organize
'ኦ፡ጋናይዝ -ግ- ማ'ደራጀት [አ'ደራ'ጀ] ፡ መ ልክ መስጠት [ሰ'ጠ]

orgy
'ኦ'ጂ -ስ- መ'ሳከር ፡ ቅጥ ማጣት (በታ'ላቅ ግብኖ ላይ) ፡ መፈንጠዝ

Orient
'ኦ፡ሪዬንት -ስ- ምሥራቃዊ የዓለም ክፍል

orientate
'ኦ፡ሪዬንቴይት -ግ- ማልመድ [አለ'መደ] ፡ አ ንድ ነገር ማ'ወቅ [አሳ'ወቀ]

orifice
'ኦሪፊስ -ስ- ቅ'ንሽ ቀዳዳ ፡ የቀ'ሻ አፍ ወዘተ

origin
'ኦሪጂን -ስ- መጀ'መሪያ ፡ ምንጭ ፡ ትው ል'ድ

original
አ'ሪጂነል -ቅ- የመጀ'መሪያ ፡ ለመጀ'መሪያ ጊዜ የተሠ'ራ ፡ አዲ'ስ ፡ አንቂ

originate
አ'ሪጂኔይት -ግ- ማስገ'ኘት [አስገ'ኘ] ፡ ሥሩ ጠር [ፈ'ጠረ]

ornament
'ኦ፡ናመንት -ስ- ጌጣጌጥ

ornate
ኦ'፡ኔይት -ቅ- ያጌጠ

orphan
'ኦ፡ፈን -ስ- እንስ ማውታ ፡ የሙት ልጅ

orphanage
'ኦ፡ፈኒጅ -ስ- የሙት ልጆች የ'ሚ'ረ'ዱ'በት ድር'ጅት

orthodox
ኦ፡ሲዶክስ -ቅ- በእስተያየቱ ትክ'ክለ'ኛ ፡ እም ነቱ ያልተቃ'ወሰ
church
-ስ- አር,ቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን

orthography
ኦ፡ሶግራፊ -ስ- ትክ'ክለ'ኛ አ'ጻጻፍ (ፊደራ ያልተሳሳተ)

oscillate
'ኦሲሌይት -ግ- መ'ወዛወዝ [ተወ'ወዘ] ፡ ማ'ወዛወዝ [አ'ወዛ'ወዘ]

ostensible
አስ'ቴንሲብል -ቅ- እውነተ'ኛውን ምክንያት ለመሸ'ፈን የቀ'ረበ (ምክንያት)

ostentation
አስቴን'ቴይሽን -ስ- ል'ታይ ል ታይ ማለት ፡ ል'ታወቅ ል'ታወቅ ማለት

ostracize
'አስትሪሳይዝ -ግ- ለ'ይቶ ማስቀ'ረት [አስ ቀ'ረ] ፡ ማ'ገዝ [አ,ገዘ] (ማውት)

ostrich
'አስትሪች -ስ- ሰጎን

other
'አዥ -ቅ- ሌላ ፡ ል'ዩ ፡ ተጨ'ማሪ

otherwise
'አዥዋይዝ -ተ- አለበለ'ዚያ

our
'አወ -ቅ- የ'ኛ

ours
'አወዝ -ተ- የ'ኛ

ourselves
አወ'ሌልቭ'ስ -ተ- (እ'ኛ) ራሳ'ችን

oust
'አውስት -ግ- ማስወ'ጣ [አስወ'ጠ] ፡ ወደ ውጪ ማ'ባረር [አ'ባ'ረረ]

out
'አውት -ተ- አው'ጭ ፡ ወደ ው'ጭ

outburst
'አውት'በ'ስት -ስ- ስ'ሜት ለመግለጽ መጣን ፈል

outcast
'አውት'ካ'ስት -ስ- የተ'ሰ'ሳ ፡ የተባረ'ረ ፡ ከማኅበራዊ ኑሮ ው'ጭ የሆን

outcome
'አውትከም -ስ- ው'ጤት

outcry
'አውት'ክራይ -ስ- አቤቱታ ፡ ጩኸት (የብዙ ሰዎ'ች)

outdoor
አውት'ዶ፡ -ቅ- የው'ጭ (ከቤት)

outer
'አውተ -ቅ- የው'ጭ

outfit
'አውትፊት -ስ- ለተለ'የ ነገር የ'ሚውል ሙሉ ልብስ ፡ መ'ሣሪያ
organization
-ስ- ድር'ጅት ፡ ን'ድ ፡ ሠ ርዘ'ኛ

outhouse
'አውትሀውስ -ስ- ከዋ'ናው ቤት የተለ'የ ፣ የዕቃ ፣ የእንስሳት ቤት
outing
'አውቲንግ -ስ- ሽ'ር'ሽር
outlandish
አውት'ላዲሽ -ቅ- እንግዳ የ'ሚመስል ፣ ያል ተለ'መደ
outlaw
'አውትሎ: -ስ- ሽፍታ ፣ ወንበዴ ፣ ደመ ክልብ
outlay
'አውትሌይ -ስ- ወጭ (ገንዘብ)
outlet
'አውትሌት -ስ- መውጫ ፣ መፍሰሻ (ለፈሳሽ ነገር)
outline
'አውትላይን -ስ- የ'ና የ'ናውን ሐ'ሳብ መግ ለጫ አ'ጭር ጽሑፍ
outlook
'አውትሉክ -ስ- ካንድ ቦታ የ'ሚ'ታ'ይ ትእ 'ይንት ፣ ወይፌት የ'ሚ'ፈ'ጸም ፣ የ'ሚሆን ነገር፤ ያስተሳሰብ መንገድ
outnumber
አውት'ንምበ -ግ- በቁጥር መብለጥ [በ'ለጠ] ፣ በብዛት ማ'ጣፋት [አ'ጣ'ፋ]
outpost
'አውትፐውስት -ስ- ፈን'ጠር ያለ መንደር ፣ ከሥል'ጣኔ ራ'ቅ ያለ መንደር ፣ ራቅ ያ'ለ ት'ንሽ የጦር ሠፈር
output
'አውትፑት -ስ- ው'ጤት (ከፋብሪካ ወዘተ የ'ሚ'ገ'ኝ)
outrage
'አውትሬይጅ -ስ- ታ'ላቅ ወንጀል ፣ ታ'ላቅ የጭ'ከኔ ተግባር
outrageous
አውት'ሬይጀስ -ቅ- አ'ሠ'ቃቂ ፣ አስደንጋጭ
outset
'አውትሴት -ስ- መጀ'መሪያ
outside
አውት'ሳይድ -ስ- ው'ጭ
-ቅ- የው'ጭ
outsider
አውት'ሳይደ -ስ- ያንድ ግኅበር አባል ያል ሆነ ፣ ብዙ ተስፋ የሌ'ለው ሰው (በውድ'ድር)
outskirts
'አውትስከርትስ -ስ- የከተማ ዳር'ቻ
outspoken
አውትስ'ፖውከን -ቅ- ግልጽ ፣ አውነት ተና ጋሪ ፣ የ'ማይደ'ብቅ
outstanding
አውትስ'ታንዲንግ -ቅ- በጣም ጥሩ ፣ መ'ሰል የሌ'ለው ፣ ገና ያልተደ'ጸመ ፣ ያላ'ለቀ
unpaid
-ቅ- ያልተከ'ፈለ (ዱቤ ወዘተ) ፣ ው'ዝፍ (ሒሳብ)
outstretched
አውትስት'ሬችድ -ቅ- የተዘረ'ጋ
outward
'አውትወድ -ተግ- ወደ ው'ጭ
outwit
አውት'ዊት -ግ- ከ'ፍ ባለ ብልኀት ማ'ዘ'ነፍ [አ'ዘ'ነፈ]
oval
'አውቭል -ቅ- የእንቁላል ቅርፅ ያ'ለው ፣ ጀሙ ልሙል
oven
'አቨን -ስ- ምድ'ጃ
over
'አውቨ -ተግ- በ . . . ላይ
-ቅ- ያ'ለፉ ፣ የተፈ'ጸመ
overall
አውቨ'ሮ:ል -ቅ- ጠቅላ'ላ ፣ አ'ጠቃላይ
garment
-ስ- የሥራ ልብስ ፣ ቁ'ታ
overcast
አቨ'ካ:ስት -ቅ- በደ'መና የተሸ'ፈነ ፣ የጨለ 'ጣ
overcoat
'አውቨኮውት -ስ- ካ'ፖርት
overcome
አውቨ'ከም -ግ- ማ'ሸ'ነፍ [አ'ሸ'ነፈ]
overcrowded
አውቨክ'ራውደድ -ቅ- የተጣ'በበ (በሰዎ'ች)፡ መ'ፈናፈኛ የሌ'ለው
overdraft
'አውቨርድራ:ፍት -ስ- የባንክ አ'ላፊ አዳ ፣ ካስ ቀ'መጡት በላይ ያወ'ጡት ገንዘብ (ከባንክ)

overdue
አውቨደ'ዩ: -ቅ- የዘገ'የ ፣ በጊዜው ያልተከ'ፈለ (ው'ዝፍ አዳ)
overflow
አውቨፍ'ለው -ግ- ሞልቶ መፍሰስ [ፈ'ሰሰ]
overgrown
አውቨግ'ረውን -ቅ- አለመጠን ያ'ደገ ፣ ያረ'ጀ (ለአትክልት ወዘተ) ፣ በልምላሜ የተሸ'ፈነ ፣ ያለ ዕድሜው በጣም የረ'ዘመ (ለልጅ)
overhang
አውቨ'ሀንግ -ግ- ግንጠልጠል [አንጠለ'ጠለ]
overhaul
አውቨ'ሆ:ል -ግ- ማ'ደስ [አ'ደሰ] ፣ መቅደም [ቀ'ደመ] (በሩ'ጫ)
overload
አውቨ'ለውድ -ግ- ያለመጠን መጫን [ጫነ]
overlook
አወቨ'ሉክ -ግ- ቸ'ል ማለት [አለ] ፣ ትይ'ዩ መሆን [ሆነ]
overpower
አውቨ'ፓወ -ግ- ማ'ሸ'ነፍ [አ'ሸ'ነፈ] ፣ ከሥ ልጣን ሥር ማድረግ [አደ'ረገ]
overrun
አውቨ'ረን -ግ- መውረር [ወ'ረረ] (በፍጥነት)
overseas
አውቨ'ሲይዝ -ስ- ባሕር ማዶ
overseer
'አውቨሲየ -ስ- ተቆጣጣሪ (የሠ'ራተ'ኞች)
oversight
'አውቨሳይት -ስ- ግድፈት ፣ ስሕተት
oversleep
አውቨስ'ሊይፕ -ስ- ከተ'መ'ደበው የሥራ ጊዜ በላይ ያ'ለፈ የሥራ ጊዜ ፣ ለ'ዚህ ጊዜ የ'ሚ'ከ 'ፈል ገንዘብ
overture
'አውቨቸ -ስ- ለኦፔራ ወይን'ም ለትያትር መቅ ድም የ'ሚሆን ሙዚቃ
overturn
አውቨ'ተ:ን -ግ- መገልበጥ [ገለ'በጠ]
overweight
አውቨ'ዌይት -ቅ- ብዙ ክብደት ያ'ለው
-ስ- ከመጠን በላይ የሆነ ሙንት
overwhelm
አውቨ'ዌልም -ግ- ማ'ሸ'ነፍ [አ'ሸ'ነፈ] (ተ ወዳዳሪ በሌ'ለው ኀይል) ፤ ማተለትለት [አተለ ተ'ለተ]
owe
'አው -ግ- ባለዳ መሆን (ሆነ)
owl
'አውል -ግ- ጉ'ጉት (የወፍ ዓይነት)
own
'አውን -ግ- መ'ገናዘብ [ተገና'ዘበ] ፣ ባለቤት መሆን (ሆነ)
owner
'አውነ -ስ- ባለቤት ፣ ባለመብት
ownership
'አውነ፪ት -ስ- ባለቤት'ነት
ox
'አክስ -ስ- በሬ
oyster
'አይስተ -ስ- አይስተር (የ'ሚ'በ'ላ ደንጊያ ለ'በሰ ወግ)

P

pace
'ፔይስ -ስ- ፍጥነት (የርምጃ'ና'ሩጫ)፡እርምጃ
pacific
ፐ'ሲፊክ -ቅ- ጸ'ጥ ያለ ፣ ሰላማዊ

Pacific
ፐ'ሲፊክ -ቅ- ፓ'ሲፊክ (የውቅያኖስ ስም)
pacify
'ፓሲፋይ -ግ- ጸ'ጥ ማድረግ [አደ'ረገ]

pack
'ፓክ -ስ- እሥር ፣ ረብጣ
-ግ- ዕቃ ለጉዞ ማዛመር [አማ'ሠረ]
package
'ፓኮጅ -ስ- ት'ንሽ እሥር ፣ ረብጣ
packet
'ፓከት -ስ- ት'ንሽ እሥር ፣ ፓ'ኮ
packing
'ፓኪንግ -ስ- ማሠሪያ ጉዝንዝ ፣ ማ'ሸጊያ ጉዝንዝ
packed
'ፓክድ -ቅ- የታ'ሠረ ፣ የታ'ሸገ (ዕቃ)
pad
'ፓድ -ስ- ዕቃ እንዳይ'ን'ዳ ለጉዝንዝ የ'ሚሆን ለስላ'ሳ ጨርቅ ፣ ገበር
padding
'ፓዲንግ -ስ- የማ'ሸጊያ ጉዝንዝ (ዕቃ እንዳ ይ'በላ'ሽ)
paddle
'ፓደል -ግ- ጥልቀት በሌ'ለው ወንዝ በማር መሄድ [ሄደ] ፣ መቅዘፍ [ቀ'ዘፈ]
-ስ- መቅዘፊያ
paddock
'ፓደክ -ስ- የፈረሶ'ች ማሠልጠኛ ወይን'ም መኖሪያ መስክ
padlock
'ፓድሎክ -ስ- ዝ-ን'ቮር ቁልፍ
paediatrics
ፔዲ'ያትሪክስ -ስ- የሕፃናት በ'ሽታ'ና የሕ'ክም'ናው ጥናት
pagan
'ፔይገን -ስ- አረመኔ ፣ በብዙ አማልክት የ'ሚ ያምን ሰው
page
'ፔይጅ -ስ- ገ'ጽ (የመጽሐፍ)
servant
-ስ- ተላላኪ ፣ አሽከር (በሆቴል ፣ በክ በብ ዘዘተ)
pageant
'ፓጀንት -ስ- የበዓል ሰልፍ (የጥንት ባህል የ'ሚያሳ'ይ)
pail
'ፔይል -ስ- ባልዲ ፣ ሸንከ'ሎ
pain
'ፔይን -ስ- ሕማም ፣ ሥቃይ (የሰው'ነት)
painful
'ፔይንፉል -ቅ- የ'ሚያ'ም ፣ የ'ሚያ'ሠቃ'ይ
painstaking
'ፔይንዝቴይኪንግ -ቅ- ጥንቁቅ (በሥራ) ፣ ባተሌ
paint
'ፔይንት -ግ- መቀ'ባት [ቀ'ባ] (ለቀለም) ፣ መሣል [ሣለ] (ለሥዕል)
-ስ- ቀለም (የቤት ወዘተ)
painter
'ፔይንተ -ስ- ቀለም ቀ'ቢ ፣ ሥዕል ሠዓሊ
painting
'ፔይንቲንግ -ስ- ሥዕል
pair
'ፔየ -ስ- ሁለ'ት ፣ ጥንድ
pal
'ፓል -ስ- የቅርብ ጓ'ኛ
palace
'ፓለስ -ስ- ቤተ መንግሥት
palatable
'ፓለተብል -ቅ- የ'ሚጥም ፣ የ'ሚጣ'ፍጥ (ለ ጣዕም ፣ ለአእምሮ)
palate
'ፓለት -ስ- ት'ናጋ
pale
'ፔይል -ቅ- የገረ'ጣ
-ስ- የሾለ ረ'ጅም የአጥር እንጨት
paling
'ፔይሊንግ -ስ- የንጨት አጥር
palisade
ፓሊ'ሳይድ -ስ- በሾለ እንጨት ወይን'ም የብ ረት ዘንግ የታ'ጠረ አጥር
pall
'ፖ:ል -ግ- መሰልቸት [ሰለ'ቸ]
-ስ- ግምጃ (የሬሳ መሸ'ፈኛ)
pallid
'ፓሊድ -ቅ- የገረ'ጣ
palm
'ፓ:ም -ስ- መዳፍ ፣ ዘምባባ
palmist
'ፓ:ሚስት -ስ- ጠንቋይ (መዳፍ ተመልክቶ የ'ሚነግር)

palpable
'ፓልፐብል -ቅ- በቀ'ላሉ ሊ'ዳ'ሰስ የ'ሚችል ፣ ለአእምሮ ጉልህ የሆነ
palpitation
ፓልፒ'ቴይሽን -ስ- የል'ብ በፍጥነት መም ታት
palsy
'ፖ:ልዚ -ስ- የእ'ጅ እንቅ'ቃጤ (በ'ሽታ)
paltry
'ፖ:ልትሪ -ቅ- ዋጋ ቢስ
pamper
'ፓምፐ' -ግ- ማንቀባረር [አንቀባ'ረረ]
pamphlet
'ፓምፍለት -ስ- ት'ንሽ መጽሐፍ
pan
'ፓን -ስ- መጥበሻ ፣ ድስት (ወዘተ)
pancake
'ፓንኬይክ -ስ- ከጻቄት ከዘይት'ና ከወተት የ'ሚ'ሠራ ኬክ (ት'ኩሱን የ'ሚበላ)
pancreas
'ፓንክሪያስ -ስ- ጣ'ፊያ
pander
'ፓንደ' -ግ- ማ'ቃጠር [አ'ቃ'ጠረ] (ለሴት) ፣ ማ'በረታታት [አ'በረታ'ታ] (ክፉን ሰው)
pane
'ፔይን -ስ- መስተዋት (የመስኮት ፣ አንድ ክፍል)
panel
'ፓንል -ስ- የግድግ'ዳ አንዱ ክፍል ፣ እራ'ት ማእዘን የሆነ እንጨት ፣ ለመፍረድ የተጠ'ሩ (በእንግሊዝ አገር) ሰዎ'ች የሰም ዝርዝር ፤ በው ይ'ይት የ'ሚ'ካ'ፈሉ ሰዎ'ች
pang
'ፓንግ -ስ- ውታት ፣ ድንገተ'ኛ ሕማም
panic
'ፓኒክ -ስ- መ'ሸበር ፣ ሽ'ብር (ከፍርሃት የተ ነ'ሣ)
panorama
'ፓነራ:መ -ስ- ጠቅላ'ላ የመሬት አ'ቀማመጥ ፣ ትእ'ይንት
pant
'ፓንት -ግ- ማለክለክ [አለከ'ለከ]
panther
'ፓንሰ -ስ- ግ'ሥ'ላ
pantry
'ፓንትሪ -ስ- ማጀት ፣ የምግብ ቤት መ'ጣሪያ የ'ሚ'ቀመ'ጡበት ክፍል
pants
'ፓንትስ -ስ- የውስጥ ሱ'ሪ
paper
'ፔይፐ -ስ- ወረቀት
news
-ስ- ጋዜጣ
par
'ፓ: -ስ- የዋጋ መ'ተካከል
parable
'ፓረበል -ስ- ም'ሳሌ
parachute
'ፓረሹት -ስ- ጀንጥላ (ከአውሮ'ፕላን የ'ሚ 'ወ'ረድ'በት)
parade
ፐ'ሬይድ -ግ- በሰልፍ መ'ንገ [ተ'ንፀ]
-ስ- ሰልፍ
paradise
'ፓረዳይስ -ስ- ገ'ነት
paradox
'ፓረዶክስ -ስ- ለመጀ'መሪያ ሲሰሙት እው ነት የ'ማይመስል ነገር ግን እውነት ሲሆን የ'ሚ ችል
paraffin
'ፓረፊን -ስ- ናፍታ
paragraph
'ፓረግራፍ -ስ- አንቀጽ (በጽሑፍ)
parallel
'ፓረሌል -ቅ- ጎ'ን ለጎ'ን የተ'ኰሰ'ኰሱ ትይ'ዩ (መሥመር)
paralyse
'ፓረላይዝ -ግ- ማስለል [አስ'ለለ] ፣ ሽባ ማድ ረግ [አደ'ረገ] ፣ አቅም ማሳ'ጣት [አሳ'ጣ]
paralysis
ፐ'ራለሲስ -ስ- ሽባ'ነት ፣ መስለል
paramount
'ፓረማውንት -ቅ- በጣም አስፈ'ላጊ ፣ ላ'ቅ ያለ
parapet
'ፓረፔት -ስ- በጣራ ፣ በመንገድ ፣ በድልድይ ዳር'ና ዳር ያ'ለ ግንብ

paraphrase
ˈፓረፍሬይዝ -ግ- አንድ ጽሑፍ በቀ'ላል አ'ነጋገር ፈ'ቶ መ'ናገር [ተና'ገረ]
parasite
ˈፓረሳይት -ስ- ሰው'ነት የሚበሉ ተባዮ'ች ፣ ለሰው ሽከም ሆኖ የ'ሚኖር ሰው
parasol
ˈፓርሰል -ስ- ጃንጥላ (ለፀሐይ መ'ከላከያ)
parcel
ˈፖ:ሰል -ስ- እሥር ፣ ረብጣ
parched
ˈፖ:ችድ -ቅ- ቦና ፣ ደረቅ
parchment
ˈፖ:ችመንት -ስ- ብራ'ና
pardon
ˈፖ:ደን -ግ- ይቅር ማለት [አለ]
-ስ- ይቅር'ታ
pare
ˈፔየ -ግ- መፋቅ [ፋ'ቀ] (እንጨት) ፣ መከር ከም [ከ'ከመ] ፣ መላጥ [ላጠ]
parent
ˈፔረንት -ስ- ወላጅ'ች (አ'ባት ወይን'ም እ'ናት)
parenthesis
ፐ'ሬንሲሲስ -ስ- ቅ'ንፍ (በጽሑፍ)
parenthood
ˈፔረንትሁድ -ስ- ወላጅ'ነት
paring
ˈፔሪንግ -ስ- ቁ'ራጭ ፣ ፍቅ'ፋቂ
parish
ˈፓሪሽ -ስ- ሰበካ (ያንድ ቄስ)
parity
ˈፓራቲ -ስ- እ'ኩል'ነት (የማዕረግ)
park
ˈፖ:ክ -ግ- መኪና ቦታ አስይዞ ማቆም [አቆመ]
place
-ስ- መ'ናፈሻ ቦታ
parley
ˈፓ:ሊ -ስ- የእርቅ ድር'ድር (በሁለ'ት መሪዎ'ች መካ'ከል)
parliament
ˈፓ:ለመንት -ስ- የምክር ቤት (ያንድ መንግ ሥት)
parlour
ˈፓላ -ስ- ል'ዩ የእንግዳ መ'ቀበያ ክፍል
parochial
ፐ'ሮውኪየል -ቅ- ሐ'ሳበ ው'ሱን ፣ ጠ'ባብ አስተያየት ያ'ለው
parole
ፐ'ሮል -ግ- ቃል በመ'ቀበል እሥረ'ኛ መፍ ታት [ፈ'ታ]
-ስ- ቃል መስጠት
parrot
ˈፓረት -ስ- በቅበ'ቃ (የወፍ ዓይነት)
parry
ˈፓሪ -ስ- መመ'ከት [መ'ከተ] (ለበ'ትር)
parsimonious
ፓ:ሲ'መውኒየስ -ቅ- ሥ'ሥታም ፣ ንብ፣'ባ (ገንዘብ) ፣ ንፋግ
parson
ˈፓ:ሰን -ስ- ካህን
part
ˈፓ:ት -ስ- ክፍል
partake
ፓ:'ቴይክ -ግ- መ'ሳተፍ [ተሳ'ተፈ]
partial
ˈፓ:ሸል -ቅ- በከፊል የሆነ ፣ ያልተፈ'ጸመ ፣ አ'ጻፁ ፣ አድልዎ የ'ሚያደርግ
participate
ፓ'ቲሲፔይት -ግ- መ'ካፈል [ተካ'ፈለ] (ለ ሥራ)
particle
ˈፓ:ቲክል -ስ- ት'ንሽ ቁ'ራጭ ፣ ስብርባሪ ፣ አ'ንባብ (ለሞስሙ)
particular
ፐ'ቲክዩለ -ቅ- ል'ዩ ፣ የተለ'የ
fussy
-ቅ- በጣም ጥንቁቅ
parting
ˈፓ:ቲንግ -ስ- መለያየት
partisan
ˈፓ:ቲዛን -ስ- ነጭ ለባ'ሽ ፣ ተዋጊ ፣ አርበ'ኛ
partition
ፓ:'ቲሽን -ስ- መከፈያ ፣ መከፈል ፣ ሁለ'ት ክፍሎ'ች የ'ሚለ'ይ ግድግ'ዳ ፣ ማንቃ ወዘተ
partly
ˈፓ:ትሊ -ተግ- በከፊል

partner
ˈፓ:ትነ -ስ- የሥራ ባ'ደ'ኛ ፣ ሽርካ
party
ˈፓ:ቲ -ስ- ግብ'ዣ
political
-ስ- የፖሊቲካ ማኅበር
pass
ˈፓ:ስ -ግ- ማለፍ [አ'ለፈ]
a law
-ግ- ሕ'ግ ማውጣት [አወ'ጣ]
give
-ግ- ማቀ'በል [አቀ'በለ]
ticket
-ስ- በነጻ የመግቢያ መ'ታወቂያ ወረ ቀት
passage
ˈፓስጅ -ስ- መ'ተላለፊያ
fare
-ስ- የጉዞ ዋጋ (የመርከብ)
passenger
ˈፓሰንጀ -ስ- መንገደ'ኛ
passer-by
ˈፓ:ስ'ባይ -ስ- ተላላፊ ፣ መንገደ'ኛ
passion
ˈፓሽን -ስ- ታ'ላቅ ስ'ሜት ፣ ጥልቅ ስ'ሜት ፣ ፍ'ላጎት
passive
ˈፓሲቭ -ቅ- የ'ማይሠራ ፣ ተጉበሮ (ሰዋሰው)
passport
ˈፓ:ስፖ:ት -ስ- የይለፍ ወረቀት
past
ˈፓ:ስት -ቅ- ያ'ለፈ
-ስ- ያ'ለፈ ጊዜ
paste
ˈፔይስት -ስ- መጣብቅ ፣ ማ'ሸጊያ
pasteboard
ˈፔይስትቦ:ድ -ስ- ነ'ጭ ወፍራም ወረቀት ፣ ከርታስ
pastime
ˈፓ:ስታይም -ስ- የጊዜ ማ'ሳ'ለፊያ ሥራ (ለመ 'ደስ'ይ ፣ ለመዝናኛ)
pastoral
ˈፓስተረል -ቅ- ከከብት እ'ረ'ኝ'ና ከሕይወቱ ጋር ግን'ኙ'ነት ያ'ለው ፣ የጸ'ጸስ
pastry
ˈፔይስትሪ -ስ- ኬክ
pasture
ˈፓ:ስቸ -ስ- የከብት ማሞያ መስክ ፣ የግመ'ሽ ቦታ
pat
ˈፓት -ግ- መጠብጠብ [መበ'ጠበ] (ሕፃናትን)
patch
ˈፓች -ስ- መ'ጣፊያ (ጨርቅ)
patchy
ˈፓቺ -ቅ- ጥሩ'ነቱ ሙሉ ያልሆነ ፣ በመጠን'ም ሆነ በዓይነት ያልተስተካ'ከለ
patent
ˈፔተንት -ስ- አንድ ነገር ባንድ ሰው ፣ ባንድ ኩ'ባንያ የተሠ'ራ የተፈለ'ሰፈ መሆኑን ማ'ረ ጋገጫ ሰነድ
paternal
ፐ'ተ:ነል -ቅ- አ'ባታዊ
path
ˈፓ:ዝ -ስ- የግር መንገድ ፣ የግረ'ኛ መንገድ ፣ ስርጥ መንገድ
pathetic
ፐ'ሴቲክ -ቅ- አሳ'ዛኝ
pathos
ˈፔይሲስ -ስ- የሐዘን ስ'ሜት የ'ሚቀሰ'ቅስ ነገር ፣ ሀ'ናቴ
pathway
ˈፓ:ዝዌይ -ስ- መ'ተላለፊያ ፣ ጠ'ባብ መንገድ
patient
ˈፔይሸንት -ስ- ሕመምተ'ኛ
-ቅ- ቻይ ፣ ትዕግሥተ'ኛ
patriotic
ፓትሪ'ዮቲክ -ቅ- ያገር ፍቅር ያ'ለው ፣ ለሀገሩ ተቆርቋሪ
patrol
ፐት'ሮውል -ግ- መፈ'ተሽ [ፈ'ተሸ] (አንድ ቦታ በመ'ታ'ደር) ፤ ዘብ መቆም [ቆመ]
patron
ˈፔይትረን -ስ- ጠ'ባቂ ፣ ተከላካይ ፣ ረ'ዳት
customer
-ስ- ደምበ'ኛ (የንግድ)

patronize
'ፓትሮናይዝ -ግ- በዝ'ቅተ'ኛ መንፈስ እ'የተ መለ'ከቱ መርዳት [ረ'ዳ] ፣ የበላይ ተጠባቂ መሆን [ሆነ] (የድር'ጅት ወዘተ)
a shop
-ግ- ደምበ'ኛ መሆን [ሆነ] (የሱቅ)

patter
'ፓተ -ስ- የመንጠብጠብ ድምፅ ፣ የፈ'ጣን እርምጃ ድምፅ ፣ ፈ'ጣን አ'ንጋገር (ያ'ሥቂ'ኛ ሰው)

pattern
'ፓተን -ስ- ሐረግ ፣ አንድ ነገር ለመሣል የ'ሚ'ገለ'በት ቅርፅ ፣ መንገድ ፣ ዓይነት ፣ ም'ሳሌ ወዘተ

paunch
'ፖ:ንች -ስ- ቦርጭ

pauper
'ፖፐ -ስ- ድሃ ፣ በተራድኦ ገንዘብ የ'ሚኖር ድሃ ሰው

pause
'ፖ:ዝ -ግ- ለጥቂት ጊዜ ማረፍ [ዐ'ረፈ]

pave
'ፔይቭ -ግ- መደልደል [ደለ'ደለ] (መንገድ)

pavement
'ፔይቭመንት -ስ- በመኪና መንገድ ዳር'ና ዳር ያ'ለ የእግረ'ኛ መሄጃ ፣ የግረ'ኛ መንገድ

pavilion
ፐ'ቪልየን -ስ- ጻስ

paving
'ፔይቪንግ -ስ- ንጣፍ ደንጊያ (የመንገድ)

paw
'ፖ: -ስ- መዳፍ (የእንስሳት)

pawn
'ፖ:ን -ስ- መያዣ ዕቃ (ለገንዘብ ብ'ድር)
chess
-ስ- ወ'ታ'ደር (በሰንጠረጅ ጨዋታ)
agent
-ስ- መ'ሣሪያ (ለክፉ ሥራ ፣ ለሰው)

pawnbroker
'ፖ:ንብረውከ -ስ- ገንዘብ አበ'ዳሪ (መያዣ ተቀ'ብሎ)

pay
'ፔይ -ግ- መክፈል ፣ [ከ'ፈለ]
salary
-ስ- ደመወዝ

payment
'ፔይመንት -ስ- ክፍ'ያ ፣ መክፈል

pea
'ፒይ -ስ- አተር

peace
'ፒይስ -ስ- ሰላም ፣ እር'ጋታ ፣ ፀ'ጥታ

peaceful
'ፒይስፉል -ቅ- ሰላማዊ ፣ ፀ'ጥ ያለ

peach
'ፒይች -ስ- ኮክ

peak
'ፒይክ -ስ- የተራራ ጫፍ

peal
'ፒይል -ግ- በጣም መደ'ወል [ደ'ወለ]
-ስ- ከፍተ'ኛ የደወል ድምፅ

peanut
'ፒነት -ስ- ለውዝ

pearl
'ፐ:ል -ስ- ሉል

peasant
'ፔዘንት -ስ- ገበሬ ፣ ባላገር

pebble
'ፔበል -ስ- ጠጠር

peck
'ፔክ -ግ- መጠቅጠቅ [ጠቀ'ጠቀ] (ለዶሮ ፣ ለወፍ)

peculiar
ፐኪ'ዩሊያ -ቅ- ያልተለ'መደ ፣ እንግዳ (ለሁ ናቴ) ፣ የተለ'የ (ጠባይ)

peculiarity
ፐኪዩሊ'ያሪቲ -ስ- ል'ዩ ጠባይ

pecuniary
ፔኩ'ኒየሪ -ቅ- የገንዘብ

pedal
'ፔደል -ስ- በእግር እንዲሠራ የ'ሚ'ደ'ረግ (መወጣወሻ ፣ ፍሬሰ.ዮን ወዘተ)

pedantic
ፐ'ዳንቲክ -ቅ- ሀዋቂ ነ'ኝ ባይ ፣ ለጥቃ'ቅን ነገር ል'ጠንቀቅ ባይ ፣ ለ'ዛ የሉ'ለው (በዋቂ) ፣ ዋራዝ ነ'ጠቅ

pedestal
'ፔደስተል -ስ- ፀምድ ፣ ሐውልት ወዘተ የ'ሚ ቆም በት መሠረት

pedestrian
ፐ'ዴስትሪየን -ስ- እግረ'ኛ
-ቅ- አሰልቺ

pedigree
'ፔዲግሪይ -ስ- ትውል'ድ ፣ የትውል'ድ ሐረግ

pedlar
'ፔድለ -ስ- ሱቅ በደረቴ ፣ ከቦታ ወደ ቦታ የ'ሚ'ዘዋ'ወር'ና ዕቃ የ'ሚሸ'ጥ ነ'ጋዴ

peel
'ፒይል -ስ- ል'ጣጭ (የፍራፍሬ)

peep
'ፒይፕ -ግ- በቀዳዳ ውስጥ መ'መልከት [ተመ ለ'ከተ] ፣ ማሾ'ለቅ [አሾ'ለቀ]

peer
'ፒየ -ግ- ቀረብ ብሎ ማየት [አ'የ]
noble
-ስ- ከ'ፍ ያለ ማዕረግ ያ'ለው ሰው

peevish
'ፒይቪሽ -ቅ- በቀ'ላሉ የ'ሚ'ቆ'ጣ ፣ በት'ንሹ የ'ሚ'ና'ደድ

peg
'ፔግ -ስ- ማንጠልጠያ (በግድግ'ዳ ላይ የተ ሰ'ካ)

pelican
'ፔሊከን -ስ- ይብራ

pellet
'ፔለት -ስ- ት'ንሽ ፣ ክ'ብ ቁ'ራጭ
shotgun
-ስ- የረሽ ፍን'ጣቂ

pelt
'ፔልት -ስ- አን.ጋ'ሬ ፣ ቆዳ

pen
'ፔን -ስ- ብዕር
enclosure
-ስ- ጋጥ ፣ ጉረ'ኖ

penal
'ፒይነል -ቅ- የወንጀል

penalize
'ፒይነላይዝ -ግ- መቅጣት [ቀ'ጣ] (መ'ቀጮ በመጣል)

penalty
'ፔነልቲ -ስ- መ'ቀጫ ፣ መ'ቀጮ

penance
'ፔነንስ -ስ- የን'ሥሐ ቅጣት

pencil
'ፔንሰል -ስ- እርሳስ (መጻፊያ)

pendant
'ፔንደንት -ስ- ያንገት ጌጥ (በድሪ ላይ የተን ጠለ'ጠለ)

pending
'ፔንዲንግ -ቅ- የተንጠለ'ጠለ (ውሳኔ ያልሳ'ጣ)

pendulum
'ፔንዱዩለም -ስ- ወዲያ'ና ወዲህ የ'ሚ'ወዛ 'ወዝ መ'ሣሪያ (የሰዓት)

penetrate
'ፔኔትሬይት -ግ- መግባት [ገ'ባ] ፣ መ'ነሳነስ [ተነሳ'ነሰ]

peninsular
ፐ'ነንሰለ -ስ- ል'ሳነ ምድር (ከብዙ ወገን በውሃ የተከ'በበ የብስ)

penis
'ፒይነስ -ስ- የወንድ አባል ፣ የወንድ ሐፍረተ ሥጋ (ቁሳ)

penitence
'ፔኒተንስ -ስ- ን'ሥሐ

penitent
'ፔኒተንት -ቅ- ተነ'ሣሒ

penitentiary
ፔኒ'ቴንሸሪ -ስ- እሥር ቤት (በተለ'ይ እሥረ 'ኛው ወደ በ'ጎ ተግባር እንዲ'መ'ለስ የ'ሚ'ደ 'ከም'በት)

pen-knife
'ፔንናይፍ -ስ- ሰንጢ

pennant
'ፔነንት -ስ- ጠ'ባብ'ና ረ'ጅም ሦስት ማዕዘን ያ'ለው ለን'ደት ሀላማ

penniless
'ፔኒለስ -ቅ- በጣም ደሀ ፣ መንጻ'ካ ደሀ

pension
'ፔንሽን -ስ- የጡረታ አበ'ል ፣ ኪራይ ተከ ፍሎ የ'ሚ'ታ'ደ'በት ቤት

pensive
'ፔንሲቭ -ቅ- ያ'ዘነ ፣ ሐ'ሳብ የ'ባው

pentagon
'ፔንተጎን -ስ- አ'ምስት ማዕዘን ያ'ለው ቅርፅ

pentecost
'ፔንተኮስት -ስ- በዓለ ኀምሳ ፣ ጰንጠቆስጤ

penultimate
ፔን'ልቲመት -ቅ- ከመጨ'ረሻ በፊት ያ'ለ (ነገር)

penury
'ፔንዩሪ -ስ- ከል'ክ ያ'ለፈ ች'ግረ'ኛ'ነት

people
'ፒይፐል -ስ- ሕዝብ

pepper
'ፔፐ -ስ- በርበ'ሬ ፡ ቁንዶ በርበ'ሬ

peppermint
'ፔፐሚንት -ስ- ፔፕርሚንት

perambulator
ፐ'ራምብዩሌይተ -ስ- የሕፃናት ጋሪ (ሕፃና ት ማንሸራሸሪያ)

perceive
ፐ'ሲይቭ -ግ- ማስተዋል [አስተዋለ] ፡ ማየት [አ'የ] ፡ መ'ረዳት [ተረ'ዳ]

perch
'ፐ:ች -ስ- የወር'ች መሥሪሪያ አግድም ብረት፡ እንጨት
roost
-ግ- ግሪፍ [ወ'ረፈ] (ለወፍ)

percent
ፐ'ሰንት -ተግ- ከመቶ ፡ በመቶ

perdition
ፐ'ዲሽን -ስ- ጥፋት (በሰው ላይ የ'ሚመጣ) ፡ ዘለዓለማዊ ኩነኔ

peremptory
'ፐርምፕሪ -ቅ- እም'ቢታ የ'ማይ'ቀ'በል ፡ ፀመ'ኛ

perennial
ፐ'ሬኒየል -ቅ- ካመት ዓመት የ'ሚቆ'ይ ፡ ብዙ ዓመታት የ'ሚቆ'ይ (አትክልት)

perfect
'ፐ:ፈክት -ቅ- ፍ'ጹም ፡ እንከን የሌ'ለው

perfection
ፐ'ፈክሽን -ስ- ፍ'ጹም'ነት ፡ እንከን የ'ለሽ 'ነት

perfidious
ፐ'ፊዲየስ -ቅ- እምነተቢስ ፡ ከሓዲ (እምነት አጉዳይ)

perfidy
'ፐ:ፊዲ -ስ- ክሕደት

perforate
'ፐ:ፈሬይት -ግ- መሸንቆር [ሸነ'ቆረ] (በተራ ብዙ 'ሽንቁሮ'ች)

perform
ፐ'ፎ:ም -ግ- መሥራት [ሠ'ራ] ፡ ማድረግ [አደ 'ረገ]

perfume
'ፐ:ፍዩም -ስ- ጥሩ ሽ'ታ
liquid
-ስ- ሽ'ቶ

perfunctory
ፐ'ፈንክተሪ -ቅ- ጥን'ቃቄ ያ'ነሰው ፡ ለግብር ይውጣ የተሠ'ራ

perhaps
ፐ'ሀፕስ -ተግ- ምናልባት

peril
'ፐረል -ስ- ከ'ባድ አደጋ ፡ ከ'ባድ መከራ

period
'ፒሪየድ -ስ- ጊዜ ፤ ነጥብ (ዐረፍተ ነገር ማቆ ሚያ)
menstruation
-ስ- የአደፍ ጊዜ

periodical
ፒሪ'ዮዲከል -ስ- መጽሔት
-ቅ- በተወ'ሰነ ጊዜ የ'ሚወጣ

periodically
ፒሪ'ዮዲከሊ -ተግ- በ'የጊዜው

periphery
ፐ'ሪፈሪ -ስ- ዳር ፡ ዳር'ቻ

perish
'ፔሪሽ -ግ- መጥፋት [ጠ'ፋ] ፡ መሞት [ሞተ]

perjury
'ፐ:ጀሪ -ስ- የሐ'ሰት ፡ የመዋሸት መንጀል (በ ምስ'ክር'ነት)

perky
'ፐ:ኪ -ቅ- ንቁ ፡ እምነቱን'ና በጉዳ'ዩ አ'ሳቢ መሆኑን የ'ሚያሳ'ይ ፡ በራሱ የ'ሚ'ተማ'መን

permanent
'ፐ:መነንት -ቅ- ቀዋሚ ፡ ነዋሪ ፡ የ'ማይ'ለ 'ወጥ

permeate
'ፐ:ሚዬይት -ግ- መስፋፋት [ተሰፋ'ፋ] ፡ መግ ባት [ገ'ባ] (ለውሃ)

permission
ፐ'ሚሽን -ስ- ፈቃድ

permit
ፐ'ሚት -ግ- ፈቃድ መስጠት [ሰ'ጠ]

permit
'ፐ:ሚት -ቅ- ፈቃድ

pernicious
ፐ'ኒሸስ -ቅ- በጣም የ'ሚጎዳ ፡ አደገ'ኛ ፡ ክፉ

perpendicular
ፐ:ፐን'ዲክዩለ -ቅ- ቀ'ጥ ያለ (መሥመር ወዘተ)

perpetual
ፐ'ፔቹዌል -ቅ- ዘለዓለማዊ ፡ ነዋሪ ፡ መጨ 'ረሻ የሌ'ለው ፡ ተደጋጋሚ

perplex
ፐ'ፕ'ሌክስ -ግ- ግ'ደናገር [አ'ደና'ገረ] ፡ የ'ሚ ያደርጉትን ግሳ'ጣት [አሳ'ጣ]

persecute
'ፐ:ሲክዩት -ግ- ግ'ሳደድ [አ'ሳ'ደደ] (ለሃይ ማኖት ወዘተ)

persevere
ፐሲ'ቪየ -ግ- መቀ'ጠል [ቀ'ጠለ] (ተስፋ ባለ መቁረጥ)

Persian
'ፐ:ሸን -ቅ- የፋርስ ፡ የኢራን ፡ ኢራናዊ

persist
ፐ'ሲስት -ግ- በሐ'ሳብ መጽናት [ጸ'ና]

person
'ፐ:ሰን -ስ- ሰው

personal
'ፐ:ሰነል -ቅ- የግል

personnel
ፐሰ'ኔል -ስ- ሠ'ራተ'ኞ'ች (የመሥሪያ ቤት)

perspiration
ፐስፐ'ሬይሽን -ስ- ማላብ ፡ ላብ

persuade
ፐስ'ዌይድ -ግ- ግሳ'መን [አሳ'መነ] ፡ በመ'ወ ያየት ወይን'ም በክር'ክር ሐ'ሳብ እንዲ'ቀ'በ ሱ ማድረግ [አደ'ረገ]

pert
'ፐ:ት -ቅ- ደ'ፋር ፡ አክብሮት የ'ማያሳ'ይ

pertinent
'ፐ:ቲነንት -ቅ- ከጉ'ዳዩ ጋር የተያያዘ ፡ ጉ'ዳ ዩን የ'ሚነካ

perturbed
ፐ'ተ:ብድ -ቅ- የታ'ወከ ፡ የተጨ'ነቀ

peruse
ፐ'ሩ:ዝ -ግ- በጥን'ቃቄ ማንበብ [አነ'በበ]

pervade
ፐ'ቬይድ -ግ- መስፋፋት [ተሰፋ'ፋ] (አደጋ ፡ ሥል'ጣኔ ወዘተ)

pervert
ፐ'ቭ:ት -ግ- ግ'ጣመም [አ'ጣመመ] (ደ'ጉን ነገር) ፤ የሰው አእምሮ ከትክ'ክለ'ኛ መንገዱ ማውጣት [አወ'ጣ] ፡ ማዛባት [አ'ዛ'ባ] ፡ ለክፉ ማዋል (አዋለ)

pervert
'ፐ:ቭ:ት -ስ- ከሰው የተለ'የ ጠባይ ያ'ለው ፤ ሴሰ'ኛ ፡ ከተፈጥሮ ው'ጭ የሆነ ሥራ የ'ሚሠራ (ለግብረ ሥጋ)

pessimist
'ፔሰሚስት -ቅ- ውልጊዜ ክፉ ነገር ይመ ጣል ብሎ የ'ሚያምን

pest
'ፔስት -ስ- አ'ዋኪ ነገር
animals
-ስ- የ'ሚጎዱ ነፍሳት ፡ ትን'ንሽ እንሰ ሳት ፤ መቅሠፍት ፤ ብዛባዥ ፡ ሁከተ'ኛ ሰው ወይ'ም ነገር

pet
'ፔት -ስ- ለ'ማዳ ት'ንሽ እንሰሳ
person
-ስ- በተለ'ይ የ'ሚ'ወደድ (ተማሪ ወ ዘተ)
caress
-ግ- ማሻሸት [አሻ'ሸ] (ሴት)

petal
'ፔተል -ስ- ያበባ ቅጠል (ከአበባው አንዷ ቅጠል)

petition
ፐ'ቲሽን -ስ- ይግባ'ኝ ፡ አቤቱታ

petrol
'ፔትረል -ስ- ቤንዚን

petticoat
'ፔቲከውት -ስ- ቡ'ፍ ያለ የሴት የውስጥ ልብስ ፡ ቡ'ፋንት

petty
'ፔቲ -ቅ- ጥቃ'ቅን (የታ የሌ'ለው)

phantasy
'ፋንተሲ -ስ- እውነት'ነት የሌ'ለው ታሪክ ፣ ሕልም የ'ሚመስል ሐ'ሳብ ፣ እንደሕልም ያ'ለ ነገር

phantom
'ፋንተም -ስ- ረቂቅ ፍጡር ፣ የማይ'ዳ'ሰስ ቅርፅ ፣ እውነት'ነት የሌ'ለው

pharmaceutical
ፋ:መሰ'ዩቲከል -ቅ- የመድኃኒት ቅ'መማ

pharmacy
'ፋ:መሲ -ስ- መድኃኒት ቅ'መማ

phase
'ፈይዝ -ስ- ባንድ ተመላልሶ በ'ሚ'ደ'ረግ ሁናቴ ውስጥ የአደገት ወይን'ም የለውጥ ጊዜ

philanthropist
ፈ'ላንሪ'ፒስት ቅ- የሰውን ልጅ ወ'ዳጅ ፣ በጎ አድራጊ ፣ ሰብአዊ ፍቅር ያ'ደረ'በት

philology
ፊ'ሎለጂ -ስ- የቋንቋዎ'ች ትምህርት

philosophy
ፊ'ሶሰፊ -ስ- ፍልስፍ'ና

phlegmatic
ፈሌግ'ማቲክ -ቅ- በቀ'ላሉ የ'ማይ'ሽ'በር

phonetic
ፈ'ኔቲክ -ቅ- እንዳ'ነባበቡ የተጻፈ ፣ የድምፅ

photograph
'ፈውተግራፍ -ስ- ፎቶግራፍ

phrase
ፍ'ሬይዝ -ስ- ሐረግ (ሰዋሰው)

physician
ፊ'ዚሽን -ስ- ሐኪም

physics
'ፊዚክስ -ስ- ፊዚክስ (የኃይል'ና የጥንተ ነገሮ'ች ጠባይ ጥናት)

physiognomy
ፊዚ'ዮንሚ -ስ- መልክ ፣ የመልክ ቅርፅ'ና ጠቅላ'ላ ሁኔታው

physique
ፊ'ዚይክ -ስ- የሰው'ነት ቅርፅ

piano
ፒ'ያኑው -ስ- ፒያኖ

pick
'ፒክ -ግ- መልቀም [ለ'ቀመ]
choose
-ግ- መምረጥ [መ'ረጠ]
tool
-ስ- መቆ'ፈሪያ ፣ ዶማ

pickaxe
'ፒክአክስ -ስ- ዶማ

picnic
'ፒክኒክ -ስ- የሽር'ሽር ቦታ (ምግብ ተይዞ የ'ሚ'ኬድ'በት)

picture
'ፒክቸ -ስ- ሥዕል

picturesque
ፒክቸ'ሬስክ -ቅ- ያማረ (ትእ'ይንት ፣ ለመሣል የ'ሚስማ'ማ)

pie
'ፓይ -ስ- ከሥጋ ወይን'ም ከፍራፍሬ'ና ከሊጥ የተሰ'ራ ምግብ (የተጋ'ገረ)

piece
'ፒይስ -ስ- ቁራ'ጭ ነገር

piecemeal
'ፒይስሚይል -ተግ- ት'ንሽ በት'ንሽ ፣ በተባ ታ'ተነ ሁናቴ

pierce
'ፒየስ -ግ- መውጋት [ወ'ጋ] (በመ'ሣሪያ)

piety
'ፓየቲ -ስ- ሃይማኖተ'ኛ'ነት

pig
'ፒግ -ስ- ዐሣማ

pigeon
'ፒጀን -ስ- እርግብ

pigtail
'ፒግተይል -ስ- በስተጎላ የወ'ረደ የጠጉር ጉን ጉን

pike
'ፓይክ -ስ- ዶማ

pile
'ፓይል -ስ- ዐሣ የ'ሚበላ ዐሣ
-ግ- መከ'መር [ከ'መረ] ፣ መቆ'ለል [ቆ'ለለ]

pilfer
'ፒልፈ -ግ- መስረቅ [ሰ'ረቀ] (ለጥቃ'ቅን ነገር)

pilgrim
'ፒልግሪም -ስ- የተቀ'ደሱ ቦታዎ'ች ለመ'ሳለም የ'ሚ'ዓዝ ሰው ፣ ተሳላሚ (ም'ሳሌ ፣ ኢ'የሩሳሌም ፣ መ'ካ)

pilgrimage
'ፒልግሪሚጅ -ስ- ወደተቀ'ደሱ ቦታዎ'ች የ'ሚ'ደ'ረግ ጉዞ

pill
'ፒል -ስ- ክኒን ፣ እንክብ'ል (መድኃኒት)

pillage
'ፒለጅ -ግ- መዝረፍ [ዘ'ረፈ]

pillar
'ፒለ -ስ- ዐምድ

pillar-box
'ፒለርክስ -ስ- ዐምድ መ'ሰል የፖስታ ማስገ'ቢያ ሣጥን (በመንገድ ዳ'ር የቆመ)

pillion
'ፒለየን -ስ- መ'ፈናጠጫ ወምበር (በሞቶር ቢስክሌት ኋላ)

pillow
'ፒለው -ስ- ትራስ

pillow-case
'ፒለውኬይስ -ስ- የትራስ ልብስ

pilot
'ፓይለት -ስ- መርከብ ነጂ ፣ አውሮ'ፕላን ነጂ

pimp
'ፒምፕ -ግ- ማ'ቃጠር [አ'ቃ'ጠረ] (ሴት ለወንድ)

pimple
'ፒምፕል -ስ- ብጉር

pin
'ፒን -ግ- በስርቪ ማ'ያያዝ [አ'ያያዘ] (መረ ቀት)
straight
-ስ- ስርቪ
safety-
-ስ- መርፌ ቁልፍ

pinafore
'ፒነፎ: -ስ- ሽ'ርተ (የሕፃናት ፣ ልብሳ'ቸው እንዳይቆ'ሽሽ)

pincers
'ፒንሰዝ -ስ- ጉጠት

pinch
'ፒንች -ግ- መቆንጠጥ [ቆን'ጠጠ]

pine
'ፓይን -ግ- መድከም [ደ'ከመ] (ከ'ሽ'ታ'ከል ዘን የተነ'ሣ) ፤ የጋስ ፍ'ላጎት መኖር [ኖረ] (ለንድ ነገር ለማድረግ)

pineapple
'ፓይናፕል -ስ- አናናስ

pinion
'ፒንየን -ግ- እ'ጅ ማሰር [እ'ሰረ] (ከሰው'ውነት ጋር)
-ስ- የወፍ ክንፍ

pink
'ፒንክ -ቅ- ከፍት ቀ'ይ

pinnacle
'ፒንከል -ስ- ጫፍ (የቤትየተራራ ወዘተ) ፣ ቁንጮ

pioneer
ፓየ'ኒየ -ስ- አንዱን ያ'ል'ማ አገር ለማልማት ከጄዱ ሰዎ'ች አንዱ ፤ ያንድ ዕ'ቅድ መሪ ፣ ያን ድ ሥራ ጀ'ማሪ

pious
'ፓየስ -ቅ- የይማኖታዊ ፣ ጊዜውን ለሃይማ ኖት ተግባር የሰ'ጠ

pip
'ፒፕ -ስ- ፍሬ (የፍራፍሬ)

pipe
'ፓይፕ -ስ- ቧንቧ
smoking
-ስ- ፒ'ፓ (የትምባሆ ማጤሻ)
flute
-ስ- ዋሽ'ንት

pirate
'ፓይረት -ስ- የባሕር ወንበዴዎ'ች ፣ መርከብ ዘራፊዎ'ች

pistol
'ፒስተል -ስ- ሽ'ጉጥ

piston
'ፒስተን -ስ- ፒስቶን

pit
'ፒት -ስ- ጉድጓድ

pitch
'ፒች -ስ- የድምፅ ከ'ፍተ'ኛ'ነት'ና ዝ'ቅተ'ኛ 'ነት
tar
-ስ- ሬንጅ
throw
-ግ- መወርወር [መረ'ወረ]
sport
-ስ- የስፖርት ሜዳ
a tent
-ግ- ድንኳን መትከል [ተ'ከለ]

pitcher
'ፒቸ -ስ- እንሥራ

piteous
'ፒትየስ -ቅ- አሳ'ዛኝ

pitfall
'ፒትፎ:ል -ስ- የአውሬ ማተመጃ ጉድጓድ ፣ የተደ'በቀ አደጋ

pith
'ፒሀ -ስ- ከል'ጣጭ በታች ያ'ለው ሥሥ ሽፋን (የፍራፍሬ ወዘተ)
importance
-ስ- ቁም ነገር (የንግ'ግር)
vigour
-ስ- ጥን'ካሬ ፣ ጎይል

pity
'ፒቲ -ስ- ሐዘን ፣ ርኅራኄ

pivot
'ፒቮት -ስ- መሽከርከሪያ ዘል መ'ሣሪያ

placard
ፕ'ላካ:ድ -ስ- ሕዝብን ለማስታወቅ የተጻፈ ጽሑፍ

placate
ፕለ'ኬይት -ግ- ማ'ረጋጋት [አ'ረጋጋ] ፣ ቁ'ጣ ማብረድ [አበ'ረደ]

place
ፕ'ሌይስ -ስ- ቦታ

placenta
ፕለ'ሰንተ -ስ- የእንግዴ ልጅ

placid
ፕ'ላሲድ -ቅ- ጸ'ጥ ያለ

plague
ፕ'ሌይግ -ስ- ጎይለ'ኛ ተላላፊ በ'ሽታ ፣ ቸነ ፈር
disturb
-ግ- ማ'ወክ [አ'ወክ] ፣ መበጥበጥ [በጠ'በጠ]

plain
ፕ'ሌይን -ስ- ል'ጥ ያለ ቦታ ፣ ሜዳ
undecorated
-ቅ- ጌጣጌጥ የሌ'ለ'በት
understandable
-ቅ- ግልጽ

plaintiff
ፕ'ሌይንቲፍ -ስ- ከሳሽ

plaintive
ፕ'ሌይንቲቭ -ቅ- የ'ሚያሳ'ዝን (ድምፅ)

plan
ፕ'ላን -ግ- ማ'ቀድ [ዐ'ቀደ]
-ስ- ዕ'ቅድ

plane
ፕ'ሌይን -ቅ- ጠፍጣ'ፋ
aero-
-ስ- አውሮ'ፕላን
tool
-ስ- መላጊያ

planet
ፕ'ላነት -ስ- ፈለክ (ከፀሐይ ብ፟ፍሮ'ች አንዱ)

plank
ፕ'ላንክ -ስ- ጠርብ

plant
ፕ'ላንት -ስ- ተክል

plantation
ፕላን'ቴይሽን -ስ- አትክልት

plaque
ፕ'ላክ -ስ- የደንጊያ ፣ የሸክላ ጽ'ላት (በማድ ማ'ጃ ላይ እንደጌጥ የ'ሚንጠለ'ጠል)

plaster
ፕ'ላ:ስተ -ስ- ፕላስተር ፣ እቁስል ላይ የ'ሚ'ለ 'ጠፍ መድኀኒት'ነት ያ'ለው መለ'ጠፊያ
of Paris
-ስ- ጅፕሰ
a wall etc.
-ግ- መ'ረግ [መ'ረገ] (ባጭ ቃ)

plastic
ፕ'ላስቲክ -ስ- ፕላስቲክ
-ቅ- በቀ'ላሉ የ'ሚ'ለ'መተ ፣ ቅርፁ የ'ሚ 'ለ'ውጥ

plate
ፕ'ሌይት -ስ- ዝርግ ሳሕን ፣ ሥሥ'ና ዝርግ የብረት ፣ የብ'ር ወዘተ ዕቃ

plateau
ፕ'ላቱው -ስ- በጸ,ጋ አነር ላይ ሜዳ'ማ ቦታ

platform
ፕ'ላትፎ:ም -ስ- ከ'ፍ ያለ የተናጋሪ መቆሚያ ቦታ

plausible
ፕ'ሎ:ዚበል -ቅ- አውነት የ'ሚመስል ፣ የ'ሚ ያሳ'ምን ፣ ሊ'ታ'መን የ'ሚችል

play
ፕ'ሌይ -ግ- መ'ጫወት [ተ'ጫ'ወተ]
theatrical
-ስ- ቴያትር (ጽሑፍ)

plea
ፕ'ሊይ -ስ- ል'መና ፣ ማመAከቻ

plead
ፕ'ሊይድ -ግ- ምክንያት ለዳ'ኛ ማቅረብ [አተ 'ረበ] (ከ'ስ ሲያቀርቡ)
beseech
-ግ- መ'ለማመን [ተለማ'መነ]

pleasant
ፕ'ሌዝንት -ቅ- አስደ'ሳች

pleasantry
ፕ'ሌዝንትሪ -ስ- አስደ'ሳች ቁው'ውት

please
ፕ'ሊይዝ -ግ- መ'ደሰት [ተ'ደ'ሰተ]
-ተግ ፣ ቃአ- አባ'ክዎን ፣ አባ'ክህን

pleasure
ፕ'ሌዠ -ስ- ደ'ስታ

pleat
ፕ'ሊይት -ስ- ሽንሽን (የልብስ)

pledge
ፕ'ሌጅ -ግ- ቃል መግባት [ገ'ባ]
-ስ- ውሊታ መግባት (አንድ ዕቃ አሰው ዘንድ በማስቀ'መተ የገ'ባውን ውሊታ ሲፈ'ጽም ዕቃውን ለመውሰድ)

plenty
ፕ'ሌንቲ -ስ- ብዛት ፣ መትረፍረፍ

pliable
ፕ'ላየብል -ቅ- በቀ'ላሉ የ'ሚ'ታ'መጡ
mind
-ቅ- በቀ'ላሉ የሰውን ሐ'ሳብ የ'ሚ'ቀ 'በል

pliers
ፕ'ላየዝ -ስ- የተጠት ዓይነት መ'ሣሪያ

plight
ፕ'ላይት -ስ- አ'ዋኪ ፣ አሳ'ዛኝ ሁኔቴ
promise
-ግ- ተስፋ መስጠት [ሰ'ጠ] (ሊጋብ'ቻ)

plimsolls
ፕ'ሊምሶልዝ -ስ- የላስቲክ ሶል ያ'ለው የሸራ ጫ'ማ (የስፖርት)

plinth
ፕ'ሊንቧ -ስ- ያንድ ሐውልት መቆሚያ ደን 'ጊያ

plod
ፕ'ሎድ -ግ- እየተ'ተቱ መ'ራመድ [ተራ'መ ደ] ፣ መሥራት [ሠ'ራ] (ለዕረፍት)

plot
ፕ'ሎት -ግ- መ'ሸ'መቅ [ሸ'መቀ]
-ስ- ሽ'መቃ
story
-ስ- ያንድ መጽሐፍ ታሪክ ፍሬ ነገር
land
-ስ- ትንሽ ቁ'ራጭ መሬት

plough
ፕ'ላው -ግ- ማረስ [አ'ረሰ]
-ስ- ማረሻ

pluck
ፕ'ለክ -ግ- መልቀም [ለ'ቀመ] (ፍራፍሬ ከዛፍ)፣ መ'ቅጠፍ [ቀጠ'ፈ] (አበባ) ፣ መንቀል]ነ'ቀለ] [ነቀ]
-ስ- ጉ'ልበት

plug
ፕ'ለግ -ስ- ውታፍ ፣ የኤሌክትሪክ መሰ'ኪያ

plumage
ፕ'ሉሚጅ -ስ- የወፍ ላባ

plumber
ፕ'ለመ -ስ- ቧ'ምቧ ሠ'ራተ'ኛ

plumbing
ፕ'ለሚንግ -ስ- በቤት ውስጥ ያ'ለ የውሃ ቧ'ና የውሃ ጋን

porter
'ፖ፦ተ -ስ- ተሸ'ክሚ ፣ ከሲ ፣ በ'ረ'ኛ (በሥቱል እንግዳ ከው'ጭ የ'ሚ'ቀ'በል)
portion
'ፖ፦ሸን -ስ- ድርሻ ፣ ክፍ'ያ ፣ ቁ'ራ'ሽ
portly
'ፖ፦ትሊ -ቅ- ወፍራም ፣ ግዙፍ (በተለ'ይ ለ'ቁማ'ሎ'ች)
portrait
'ፖ፦ትሬይት -ስ- የሰው ፣ የእንስሳ ሥዕል
pose
'ፕወ፦ዝ -ግ- ለ'ው'ነት ማስተካከል [እስተ ካ'ከል] (ለፎቶግራፍ እንዚ)
pretend
-ግ- መምሰል [መ'ሰል] (ሌላ ሰው)
set (question)
-ግ- ተ'ያቂ ማቅረብ [እቀ'ረበ]
position
ፕ'ዚሸን -ስ- ቦታ ፣ ሁናቴ
positive
'ፖዘቲቭ -ቅ- እርግጠ'ኛ ፣ የ'ማያ'ጠራ'ጥር
possess
ፕ'ዜስ -ግ- መ'ገዝ'ዘበ [ተገና'ዘበ]
possessive
ፕ'ዜሲ.ቭ -ቅ- ሰውን ፣ ማ'ና'ቹውን'ም ነገር የራሱ ለማድረግ የ'ሚተር ፣ እ'ንናዛቢ (ሰዋ ሰው)
possible
'ፖሲበል -ቅ- የ'ሚ'ቻል ፣ ሊሆን የ'ሚችል
post
'ፕውስት -ስ- እመራት ላይ የተተ'ከለ እን ጨት
mail
-ስ- ፖስታ ፣ ደብዳ'ቤ
appointment
-ስ- ሹመት (የሥራ)
despatch
-ግ- ደብዳ'ቤ በፖስታ መላክ [ላክ]
postcard
'ፕውስትካ፦ድ -ስ- ፖስትካርድ
poster
'ፕውስተ -ስ- የተለ'ጠፈ ማስታወቂያ
posterior
ፖስ'ቲሪየ -ስ- ኋላ ፣ ጻ'ሌ ፣ ቂጥ
-ቅ- በተራ ፣ በጊዜ የኋለ'ኛ የሆነ
after in time
-ቅ- በኋላ ያ'ለ ፣ ያ'ለፈ
posterity
ፖስ'ቴሪተ -ስ- መጪ ትውል'ድ ፣ የልጅ ልጅ
posthumous
'ፖስትዩመስ -ቅ- ከሞት በኋላ ፣ ከደራሲው ሞት በኋላ የታ'ተመ
postman
'ፕውስትመን -ስ- ፖስታ አ'ዳይ
postmaster
'ፕውስትማስተ -ስ- የፖስታ ቤት ሹም
postmortem
ፕውስት'ሞ፦ተም -ስ- በበድን ላይ የ'ሚ'ደ'ረግ የሕ'ክም'ና ምርመራ (ያ'ሟሟቱን ሁናቴ ለማ 'ረጋገጥ)
post-office
'ፕውስትኦፊስ -ስ- የፖስታ ቤት
postpone
ፕስ'ፐውን -ግ- ማስተላለፍ [አስተላ'ለፈ] (ነ ገር ፣ ጉ'ዳይ)
postscript
'ፕውስክሪፕተት -ስ- ደብዳ'ቤ ከተጻፈ'ና ከተ ፈ'ረመ በኋላ የ'ሚ'ጻፍ ተጨ'ማሪ ጽሑፍ ፣ ተ'ያቂ
postulate
'ፖስት፝ዩሌይት -ግ- ሐ'ሳብ ማቅረብ [አቀ'ረበ] (ለክር'ክር ፣ ለውይ'ይት)
posture
'ፖስቸ -ስ- የሰው'ነት አ'ቋቋም (ቀ'ጥ ያለ ፣ ያዘነ'በለ ወዘተ)
posy
'ፕውዚ -ስ- ያበባ እ'ቅፍ
pot
'ፖት -ስ- ማሰሮ
potato
ፕ'ቴይተው -ስ- ድ'ን'ች
potent
'ፕወ፦ተን -ቅ- ችሎታ ያ'ለው ፣ ጎይለ'ኛ
potential
ፕ'ቴን'ሸል -ስ- ወደፊት ሊሆን ፣ ሊ'ደ'ረግ የ'ሚችል ነገር ወይን'ም ሁናቴ

potion
'ፕውሸን -ስ- መድኃኒት'ነት ያ'ለው ፣ መር ዝ'ነት ያ'ለው ወይን'ም አስካሪ መጠ'ጥ
potter
'ፖተ -ስ- ሸክላ ሠሪ
pottery
'ፖተሪ -ስ- የሸክላ ዕቃ
pouch
'ፓውች -ስ- የቆዳ ከረጢት ፣ ቦርሳ
